# የእይታና የትውና ጥበባት



## የተማሪ መጽሐፍ

# ስድስተኛ ክፍል

የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል መንግሥት ትምህርት ቢሮ





# የእይታና የትወና ጥበባት

## የተማሪ መጽሐፍ

## 6ኛ ክፍል


**አዘጋጅ:-** ፍቃዱ ደጀኔ, ወርቃአፈራው ኡቴ, ቲና አሰሌ, ታምራት አብራሃም

**አርትኦት:-** ታርኳ ተሰማ, ርብቃ ፀጋዬ

**ሰዓሊ:-** ፍቃዱ ደጀኔ

**የጥራት ተቆጣጣሪዎች:-** ተዋበ ታደሰ

**Panellists:-** ተከለማሪያም ጥላሁን

**ኖታ ቀረጻ:-** ወርቃአፈራው ኡቴ
**ትየባ:-** ቲና አሰሌ

**አፅዳቂዎች (Validators):-** ሜላት መካሻ, አሰጋኸኝ ጉየ, አረጋ አሰፋ, ስምስም ደግፌ



የደ/ብ/ብ//ሕ/ክ/መ ትምህርት ቢሮ

# © የቅጂ መብት

ይህ መጽሐፍ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ተዘጋጅቶ በደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦች ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት በኩል በተገኘ የገንዘብና የቴክኒክ ድጋፍ ተዘጋጅቶ አጠቃላይ የሕትመት ወጪው በደቡብ ብሔሮችና ብሔረሰቦች ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ተሸፍኗል።

የመጽሃፉ ሕጋዊ ቅጂ ባለቤት © 2015 ዓ.ም የደቡብ ብሔሮችና ብሔረሰቦች ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ ነው።

# ማውጫ


መግቢያ ........................................ i

## ምዕራፍ አንድ ........................................ 1

1.የስነጥበብ መሰረቶች ........................................ 1

## ምዕራፍ ሁለት ........................................ 21

2.የስነጥበብ መሰረቶች ........................................ 21

## ምዕራፍ ሦስት ........................................ 68

3.የእይታና የትወና ጥበብ ታሪካዊና ባህላዊ አውድ ........................................ 68

## ምዕራፍ አራት ........................................ 86

4.የእይታ እና የትወና ጥበባትን በመጠቀም ሀገር በቀል እውቀቶችን ማድነቅና መግለጽ ................ 86

## ምዕራፍ አምስት ........................................ 101

5.የእይታ እና የትወና ጥበባት ከሌሎች የትምህርት ዓይነቶች ጋር ያለው መስተጋብር ................ 101

ዋቢ መጽሐፍት ........................................ 119

# መግቢያ

በዚህ የ6ኛ ክፍል የትውንና እና የእይታ ጥበባት መጽሐፍ ውስጥ አምስት ምዕራፎች አሉ። እነዚህን ምዕራፎች ተማሪዎች በጥበብ ክህሎት እንዲታነጹ ተጠንተው የተሰሩ ናቸው። ምዕራፎቹ በተከታታይ ተያያዥነት ያላቸው ሲሆኑ የተማሪዎችን ንቃተ-ህሊና ከፍ በማድረግ ለአካባቢያቸው አውንታዊ አስተዋጾዖ ማድረግ እንዲችሉ የሚረዳቸው ነው።

የመጀመሪያው ምዕራፍ ሥነ-ጥበባዊ ምልከታ ነው። በዚህ ምዕራፍ ተማሪዎች ለአካባቢያቸው ለባህላቸው እና ለሃገራቸው ያላቸው ሥነ-ጥበባዊ ግንዛቤ እንዲ ጠነክር ተብሎ የተሰራ ነው።

በሁለተኛው ምዕራፍ ደግሞ በመጀመሪያው ምዕራፍ በምልከታ ካገኟቸው ሃሳቦች ጋር ተያይዘው ሃሳባቸውን ሊገልጹ የሚችሉበት ተግባራዊ ክህሎቶችን በመለማመድ ፈጠራዊ የአገላለጽ ችሎታቸውን የሚያዳብሩበት ነው። በዚህ ክፍል የተሻለ ተግባራዊ ልምምድ የሚያደርጉበት ሲሆን የፈጠራ ክህሎታቸውን የሚያዳብሩበት ነው።

ሦስተኛው ምዕራፍ ሥነ-ጥበባትን ታሪካዊ እና ባህላዊ አውድ የሚመለከት ነው። በዚህ ክፍል በምዕራፍ አንድ እና ሁለት ያገኙትን ሃሳባዊ እና ትግባራዊ እውቀት ከታሪክ እና ባህል አውድ አንጻር በማየት የአካባቢያቸውን እና የሃገራቸውን ባህል እና ታሪክ የሚገልጹበት ነው።

ምዕራፍ አራት የሚያተኩረው ደግሞ ስነውበታዊ እሴቶች ላይ ሲሆን በዚህ ክፍል በአካባቢያችን የሚገኙ በማህበረሰቡ ትልቅ ቦታ ይዘው የሚገኙ እሴቶችን ማጉላት ማሳየት እና ማድነቅ ነው። በዚህ ዙሪያ የጥበባት ሚና ላቅ ያለ በመሆኑ ተማሪዎች በሚሰማሩባቸው ስራዎች የራሳቸውን ግንዛቤ ከማሳደግ አልፈው ለሌላው የህብረተሰብ ክፍል ማሳየት እና እውቅናን መስጠት ይችሉበታል።

በመጨረሻው ክፍል ምዕራፍ አምስት የሥነ-ጥበባት መስተጋብር ዝምድና እና ትግበራ ላይ የሚያተኩር ነው። በዚህ ክፍል የእይታ እና የትውና ጥበባት እርስ በእርስ እና ከሌሎች ሙያዎች ጋር ያላቸውን መስተጋብር ዝምድና እና ጠቀሜታ

የሚታይበት ነው፡፡ በዚህም ክፍል የጥበባት ሚና በሁሉም ዘርፍ ጠቃሚ መሆኑ የሚፈተሽበት ነው፡፡

የ6ኛ ክፍል የትውን እና የእይታ ጥበባት ትምህርታቸውን ከጨረሱ በኃላ ተማሪዎች የሚከተሉትን ማድረግ ይችላሉ ፦

ተማሪዎች የ6ኛ ክፍል የትወና እና የእይታ ጥበባት ትምህርታቸውን ሲጨረሱ የሚከተሉትን ማድረግ ይችላሉ፦

- የእይታ ጥበባት አላባዊያንን (መስመር ፣ ዝርግ ቅርፅ ፣ ቅርጽ ፣ ቀለም ፣ ጥቁረት እና ንጣት ፣ ሸካራነት/ለስላሳነት ፣ መጠን ፣ ድግግሞሽ) ፣ ትያትር ፣ ተንቀሳቃሽ ምስል ቀረፃ ቴክኒኮች፣ የሙዚቃ አላባዊያንን (ምት ፣ የድምጽ ከፍታና ዝቅታ ፣ ጊዜያዊ የድምጽ ፍጥነት እና እርጋታ ፣ የድምጽ መወፈር እና መቅጠን ...) ፣ ውዝዋዜ እና የተንቀሳቃሽ ምስል ቀረፃ ቴክኒኮችን ይረዳሉ
- ቀላል የሙዚቃ ኖታዎችን (በG ቁልፍ እና በ F ቁልፍ) ላይ የተፃፉትን ያነባሉ፡፡
- ከሰሙት ድምጽ ከተመለከቱት የተንቀሳቃሽ ምስል እና ካዩት ምስል የታዩ መልዕክቶችን ፣ ምስሎችን እና ድርጊቶችን ይገልጻሉ፡፡
- በሜጀር እና ማይነር ቁልፎች ፣ በድምጽ ከፍታና ዝቅታ እና የቅኝት ቁልፍ (key signature) መካከል ያለውን ተመሳሳይነት እና ልዩነት ይገልጻሉ፡፡
- በትያትር ጥበባት (ትወና ፣ ማዘጋጀት ፣ የተውኔት ጽሑፍ) እና በፊልም ጥበባት መካከል ያለውን ተመሳሳይነት እና ልዩነት ይግልጻሉ፡፡
- ለስዕል እና ለሌሎች ተዛማጅ እይታዎች ኪነ-ንድፍ ሰርተው ያሳያሉ፡፡
- ቀላል ዜማዊ እና ስልተምታዊ መዝሙሮችን ከሙዚቃ መጻፊያ ሰሌዳ (ቀጭን/ወፈራም ድምጾች G እና F ቁልፎች) ላይ በመስራት ያሳያሉ፡፡
- ወፍራም እና ቀጭን ድምጾችን ይለያሉ፡፡
- ድምጽ አልባ ትወናን ከቁስ ጋር ፣ ሞንታጅ እና ያልተጻፈ ትወናን እንዲሁም ንድፍን ፣ ስዕልን እና የህትመት ጥበብ ክህሎቶችን ሰርተው ያሳያሉ፡፡
- በሙዚቃ ፣ በትያትር ፣ በተንቀሳቃሽ ምስል እና በፎቶግራፍ አማካኝነት ሁነቶችን ፣ ስሜቶችን ፣ ጭብጦችን ፣ ሀሳቦችን ይግልጻሉ፡፡

# ምዕራፍ አንድ

## 1. የስነጥበብ መሰረቶች

### መግቢያ

በዚህ ክፍል የትውን እና የእይታ ጥበባት ትምህርታችሁ ከዚህ በፊት ማለትም ከ6ኛ ክፍል በፊት የተማራችሁትን የትውንና የእይታ ጥበባት አላባዊያን ሰፋ ባለ መልኩ በመጠቀም ወደ ተግባር ሊለወጥ የሚችል ግንዛቤ እንዲኖራችሁ ተብሎ የተዘጋጀ ነው፡፡

የትውን እና የእይታ ጥበባትን መማር ያለው ጠቀሜታ እጅግ በጣም ሰፊ ነው፡፡ የትውን እና የእይታ ጥበባት መማር የሚያስፈልገው የጥበብ ባለሙያ ለመሆን ብቻ ሳይሆን በሌሎች ሙያዎች በሚኖረን የስራ ሂደት ዉስጥ ስራችንን በተሳካ እና ማራኪ በሆነ መልኩ እንድንሰራ ነው፡፡ ይህም ማለት የጥበባት ግንዛቤ ያለው ሰው በሁሉም የሥራ ዘርፎች ስኬታማ እንዲሆን የሚረዳውን ክህሎት ከጥበባት ያገኛል ማለት ነው፡፡ እነዚህ በሁሉም ሙያዎች ስኬታማ እንድንሆን የሚረዱን ክህሎቶች የ21ኛው ክፍለ ዘመን ክህሎቶች ይባላሉ፡፡ እነሱም የፈጠራ ችሎታ ፣ ችግር ፈችነት ፣ በጋራ የመስራት ችሎታ ፣ መቻቻል ውሳኔ ሰጭነት እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

የትውን እና የእይታ ጥበባት በውስጡ ብዙ ነገሮችን ያካተተ ነው፡፡ ጠቅለል ያለ ትርጉም ለመስጠት ያክል ሥነ-ጥበብ የሰው ልጆች ያለገደብ ሊግባቡ የሚችሉበት ቋንቋ ነው፡፡ ሀሳብን አስተሳሰብን ስሜትን የተለያዩ መረጃዎችን የምንለዋወጥበት ቋንቋ ነው፡፡ ተማሪዎች ከዚህ በፊት የተማራችሁትን እንደምታስታውሱት ሥነ-ጥበብን ለመስራት የምንጠቀምባቸው ግብዓቶች የሥነ-ጥበብ አላባዊያን ይባላሉ፡፡ የሥነ-ጥበብ አላባዊያን ጥበብን ለመስራት የምንጠቀምባቸው ዋና ዋና ነገሮች ናቸው፡፡ የትወና እና የእይታ ጥበባትን ለመስራት በውስጡ ብዙ የጥበብ ዓይነቶችን የያዘ ሲሆን በዋናነት የእይታ

ጥበባት፣ ኪነ-ንድፍ፣ ኪነ-ቅብ፣ ኪነ-ህትመት፣ ቅርጻቅርጽ፣ ሙዚቃ፣ የትያትር ጥበባት፣ ማለትም ትወና ማዘገጀት፣ ተውኔት መጽሐፍ እና የፊልም ጥበባት ይገኙበታል፡፡ በዚህ ምዕራፍ የተዘረዘሩትን የትወና እና የእይታ ጥበባት በመረዳት ተግባራዊ እውቀት እንዲኖረን እናደርጋለን፡፡

## አጥጋቢ የችሎታ ደረጃ

- የትወና እና የእይታ ጥበባት መግለጽ ይችላሉ።
- ኪነ-ንድፍ ለኪነ-ቅብ እና ለሌሎች የእይታ ጥበባት መሰረት መሆኑን ይገነዘባሉ።
- ሜጀር እና ማይነር ቁልፎችን እና የድምፅ መወፈር መካከለኛ እና መቅጠን እንዲሁም ኪ ሲግንቸር መግለጽ ይችላሉ።
- የትያትር ጥበባትን ትወና ማዘገጀት ተውኔት መጻፍ እና የፊልም ጥበባትን ምንነት መግለጽ ይችላሉ።

## 1.1. ኪነ-ንድፍ

### መግቢያ

ኪነ-ንድፍ በተመለከተ ቀደም ባሉት ክፍል መሠረታዊ ነገሮችን የተማሩ ሲሆን በዚህ ክፍለ ትምህርት ተጨማሪ ኪነ-ንድፍ በከፍተኛ ደረጃዎቹን የበለጠ ተግባራዊ ሥራ ላይ በማተኮር ልምምድ የምታደርጉበት ይሆናል። ንድፍ ለእይታ ጥበባት መሠረታዊ የሥነ ጥበብ አይነት መገለጫ በመሆኑ መታወቅ ያለበት ነገር ነው። ይህን በማሰብ በተለያዩ ርዕስ ተማሪዎች በአከባቢያቸው የሚገኙትን በመስራት ስለ ኪነ ንድፍ መሠረታዊ እውቀትና ግንዛቤ እንደሚያገኙ ይጠበቃል።

## አጥጋቢ የችሎታ ደረጃ

- የእይታ ጥበባትን ምንነት ይገልጻሉ።
- ኪነ-ንድፍ ለእይታ ጥበባት መሰረት መሆኑን ይገልጻሉ!

### ማነቃቅያ ተግባር-1


ኪነ-ንድፍ ማለት ምን ማለት ነው?

የእይታ ጥበባት የምንላቸው የጥበብ ባለሙያዎች ሃሳባቸውን ስሜታቸውን ወይም የተለያዩ መረጃዎችን ለሌሎች ሰዎች በማየት እንዲረዱት ተደርገው የሚሰሩ የጥበብ አይነቶችን ነው። እነዚህ የእይታ ጥበብ ዓይነቶች በዋናነት በአራት ይከፈላሉ።

እነዚህም:-

1. ኪነ ንድፍ (ድሮዊንግ)
2. ኪነ ቅብ (ፔንቲንግ)
3. የህትመት ጥበብ (ፕሪንትሜኪንግ) እና
4. ኪነ ቅርጽ(እስክላፕቸር) ናቸው።

ኪነ-ንድፍ ለሁሉም የእይታ ጥበባት መሠረት ነው። ይህም ማለት ኪነ ቅብን እና ሌሎች የእይታ ጥበባትን ለመስራት በምንጀምርበት ጊዜ በቅድሚያ ንድፋቸውን የምናጠናበት ሂደት ኪነ ንድፍ ስለሆነ ነው፡



ምስል 1. በእርሳስ የተሰራ የኪነ ንድፍ ስራ

ኪነ-ንድፍ ከእይታ ጥበባት መካከል ዋና መሠረት ሲሆን የጥበብ ባለሙያዎች የተለያዩ ደረቅ ማቅለም የሚችሉ መሳሪያዎችን እርሳስ ፣ እስክሪቢቶ ፣ ባለቀለም እርሳሶች ፣ ክራዮኖች ፣ ከሰል ፣ ጠመኔ ፣ ባለቀለም ጠመኔዎች ፣ ፓስቴል ፣ ላጲስ የመሳሰሉትን በመጠቀም ወረቀት ላይ ወይም ዝርግ ሰሌዳ ላይ የሚሰራ የጥበብ ዓይነት ነው ።

የተግባር ሥራ-1

1. ተማሪዎች የቤት ውስጥ ቁሳቁስ በንድፍ በመስራት ተለማመዱ?

ኪነ-ንድፍ ማለት በአከባቢያችን በአይን ያየናቸውን ነገሮች ቅርፃቸውን በአግባቡ እርሳስን፣ ከሰል እና እስክሪቢቶ የመሳሰሉትን ቁሳቁሶች በመጠቀም በወረቀት፣ በግድግዳ ላይ ለእይታ የምናቀርብበት ዘዴ ነው፡፡ በአካባቢያችን የሚታየው ቁሳዊ እሴቶችን ቅርጻቸውን እና መጠናቸውን ለማሳየትም ይረዳናል፡፡



ምስል 2. በንድፍ የተሰራ ዝሆን ምስል

ኪነ-ንድፍ የአካባቢያችንን የተለያዩ ቅርጽና ቀለማት ያላቸውን ቁሳቁሶች ቤቶችን እና የአካባቢያቸውን ያለውን ውበት እንዳለ አድርገን ለማሳየት የሚጠቅም ዘዴ ነው ፡፡



ምስል 3. የጋሞ ባህላዊ የቤት አሰራር (ኬታ)

ከጥንት ጀምሮ ይሠራ የነበረ የጥበብ ዓይነት ሲሆን በዘመናት ውስጥ የተፈጠሩ የንድፍ መስሪያ መሳሪያዎች እንደ ዘመኑ ስልጣኔ አይነታቸውና መጠናቸው እየተሻሻለ እና እየበዛ ባለንበት ዘመን መድረስ ችሏል፡፡

አሁን ባለንበት ዘመን ኪነ ንድፍ በኮምፒውተር የሚሰራ ሲሆን በኮምፒውተር የሚሰራ ንድፍ ዲጂታል ንድፍ (ዲጂታል ድሮዊንግ) ይባላል፡፡


**የተግባር ሥራ-2**

1. ተማሪዎች ለንድፍ ለመስራት የሚጠቅሙ የመስመር አይነቶች ተለማመዱ?

## ዲጂታል ንድፍ



ምስል 4. በዲጂታል ንድፍ እንቁራሪት እና ልጁ



ምስል 5. የዲጂታል ንድፍ

ንድፍ የምንሰራባቸው መሣሪያዎች በመስሪያ ስሌዳዎች ላይ የተወሰነ የሚታይ መስመር ይሰራሉ፡፡ በብዛት የምንጠቀምባቸው የንድፍ ስሌዳዎች ወረቀቶች ነው፤ በርግጥ ሌሎች እንደ ካርድቦርድ፣ጣውላ፣ የፕላስቲክ እንዲሁም የቆዳ ስሌዳዎችን ላይ ንድፍ ይሰራል ፡፡

ለትንሽ ጊዜ ቆይታ ብቻ የሚሆኑ ንድፎች በጥቁር ሰሌዳ ላይ ይሰራሉ፤ ኪነ-ንድፍ በዘመናት ውስጥ በብዛት የሚሰራ የእይታ ጥበብ ነው፤ ይህም የሆነው መሰረታዊ እና ውጤታማ ሀሳብን የመግለጽ አቅም ስላለው ነው፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የኪነ-ንድፍ መስሪያ መሣሪያዎች በቀላሉ የሚገኙ መሆናቸው በብዛት ለመስራት ዕድልን የሚሰጥ የእይታ ጥበብ እንዲሆን አድርጎታል፡፡ ንድፍን መስራት የፈጠራ ችሎታችንን እንድናዳብር ይረዳናል ፤በዚህ ምክንያት ብዙ ታዋቂ የሆኑ የእይታ ጥበባት ባለሙያዎች ከሁሉም ስራዎቻቸው በላይ የንድፍ

ስራዎቻቸው መጠን እጅግ ብዙ ነው፡፡

## 1.2. የመሠረታዊ እና ኢ-መሠረታዊ ቅኝት ፣ የድምጽ መወፈር መቅጠን እና በድንገት የሚፈጠር ድምጽ

### መግቢያ

ተማሪዎች ከዚህ በፊት ባሉት ክፍል የሙዚቃ ትምህርት በተለያዩ ምዕራፍ ተከፋፈለው ተምራችዋል፡፡ በዚህ ምዕራፍ ውስጡ ሙዚቃ ብዙ ነገር የያዘ የሥነ-ጥበብ አካል አንዱ እንደሆነ በሚገባ እንድትረዱ ያስፈልጋል፡፡

ሥነ-ጥበብ ሁሌም አዲስ ሲለሆነ በአግባቡ መማር ይጠበቅባችኋል፡፡ የመሠረታዊ እና ኢ-መሠረታዊ ድምጽ መውፈርንና መቅጠንን እና በድንገት የሚፈጠር ድምጽ በአገባቡ መማር አለባችሁ፡፡

### አጥጋቢ የችሎታ ደረጃ

- ▶ የቅኝትን ምንነት ይገልጻሉ፡፡
- ▶ መሠረታዊ እና ኢ-መሠረታዊ ቅኝት ለይተው ይገልጻሉ፡፡
- ▶ የድምፅ መወፈር መካከለኛ እና መቅጠን ለይተው ይገልጻሉ፡፡
- ▶ በድንገት የሚፈጠር ድምጽ ምንነትን ይገልጻሉ፡፡

ተማሪዎች በ5ኛ ክፍል ትምህርታችሁ ላይ መሰረታዊ የሙዚቃ አላባዊያንን እንደተማራችሁ ይታወቃል፡፡ እነዚህም ድምጽን አጉልቶ ወይም አቅጥኖ መጫወት፣ የጊዜ ቆይታ፣ ድምፅ እና ውዝዋዜ ናቸው፡፡ በዚህ የትምህርት ክፍል ላይ የሚከተሉትን ትማራላችሁ፡፡

**ሀ- መሠረታዊ ቅኝት (Major scale)፡-** መሠረታዊ ቅኝት ማለት በሙዚቃ ውስጥ መሰረታዊ የሙዚቃ ቁልፍ ነው፡፡ በሙዚቃ ውስጥ ሰባት መሰረታዊ ቁልፎች ያሉ ሲሆን ፤ የድምፅ ርቀታቸውም አምስት ሙሉ እና ሁለት ግማሽ የድምጽ ርቀት አለው፡፡ ይህ ርቀታቸውም በ3ኛ እና በ4ኛ እንዲሁም በ7ኛ ና በ8ኛ ድምፅ መካከል ያለው የግማሽ ድምፅ ርቀት ሲሆን ሌሎች አምስቱ ቀሪ ድምጾች ሙሉ ድምፅ አላቸው፡፡ እነዚህ ድምጾች ከዚህ በታች ተዘርዝረዋል፡፡ ከዚህ በታች የቀረበው ምሳሌ C ቅኝትን መሰረት በማድረግ ነው፡፡ C ቅኝት ማለት ነጬን ቁልፍ ብቻ በመጠቀም C ቁልፍ ላይ ጀምሮ C ቁልፍ ላይ የሚጨርስ ቅኝት ነው፡፡

DO RE MI FA SOL LA SI DO

C- D- E- F- G- A- B- C

ከላይ በፊደል የተጻፉት ድምጾች በ 1 እና ½ኛ እንደተዘረዘሩ ይታያል፡፡ ይህም አንድ ማለት ሙሉ ድምፅ ያላቸው ሲሆን ½ኛ ማለት ግማሽ ድምፅ ያላቸው መሆኑን ይገልጻል፡፡ C-D-E-G-A-B ሙሉ ድምፅ ያላቸው ናቸው፡፡ ከ E-F እና ከ B-C ግማሽ የድምፅ ርቀት አላቸው፡፡

**ለ - ኢ-መሰረታዊ ቅኝት (minor scale) ፡-** ኢመሰረታዊ ቅኝት እንደ መሰረታዊ ቅኝት ሰባት የተለያዩ ቁልፎች ያሉት ሲሆን አምስት ሙሉ እና ሁለት ግማሽ የድምፅ እርቀት አላቸው፡፡ ኢመሰረታዊ ቅኝት ከመሰረታዊ ቅኝት የወጣ የቅኝት ክፍል ነው፡፡ ልዩነታቸውም በመሰረታዊ ቅኝት ጊዜ በ3ኛ እና በ4ኛ መካከል እንዲሁም በ7ኛ እና በ8ኛ መካከል ግማሽ የድምፅ ርቀት ሲኖር ኢመሰረታዊ ቅኝት ጊዜ በ2ኛ እና በ3ኛ መካከል እንዲሁም በ5ኛ እና በ6ኛ መካከል ግማሽ የድምፅ ርቀት አላቸው፡፡

ኢመሰረታዊ ቅኝት ለማገኘት የተኛውንም መሰረታዊ ቅኝት መነሻ አድርገን ስድስት ወደ ፊት ወይም ሶስት ወደ ኃላ ቆጥረን የሚናገኘው ቅኝት ነው፡፡ ከዚህ በታች የቀረበው ምሳሌ A ቅኝትን መሰረት በማድረግ ነው፡፡ A ቅኝት ማለት ነጩን ቁልፍ ብቻ በመጠቀም A ቁልፍ ላይ ጀምሮ A ቁልፍ ላይ የሚጨርስ ቅኝት ነው፡፡

LA SI DO RE- MI- FA SOL LA-

LA SI DO RE- MI- FA SOL LA-

A- B- C- D- E- F- G- A G- A

1ሙሉ ግማሽ 1ሙሉ 1ሙሉ ግማሽ 1ሙሉ 1ሙሉ ሙሉ 1ሙሉ

ከላይ እንደተገለፀው ሙሉ ድምፅ ያላቸው ከ A-B ፣ ከ C-D ፣ ከ D-E ፣ ከ F-G እና ከ G-A ሙሉ ድምፅ ያላቸው ሲሆን ከ B-C እና ከ E-F የግማሽ ድምፅ ርቀት አላቸው፡፡

## ማነቃቅያ ጥያቄ -2

ድምፅ ማለት ምን ማለት ነው?

## ድምጽ

ድምጽ ማለት የመስማት ስሜትን የሚያነቃቃ አካላዊ ክስተት ሲሆን በህብረትም ይሁን በግል የሙዚቃ መሳሪያ ሲጫወትም ይሁን ሲዘምር እንዲሁም የሆነ ነገር ሲያወራ በጆሮ የሚሰማ ከሆነ ድምጽ ይባላል፡፡ ሙዚቃዊ ድምጽ ለሰው ልጅ እና ለሙዚቃ ለመሳሪያ በመባል ለሁለት ከፍለን እናየዋለን፡፡

- **የሰው ልጅ ድምጾች፡-** ለእያንዳንዱ ሰው የራሱን የሆነ ድምጽ አለው፡፡ እነሱም ከዚህ በታች በሚገኘው ሰንጠረዥ ውስጥ ተዘርዝረዋል፡፡

| የወንድ ድምጾች | የሴት ድምጾች |
|---|---|
| ቀጭን (tenor) | ቀጭን (soprano) |
| መካከለኛ (bartone) | መካከለኛ (mezzo soprano) |
| ወፍራም(bass) | ወፍራም (alto) |

ሰንጠረዥ 1 የሰው ልጅ ድምፅ

- **የሙዚቃ መሳሪያ ድምጽ፡-** ይህ ድምጽ ደግሞ ቀጭን እና ወፍራም ድምጽ በመባል በሁለት ይከፈላሉ፡፡

| የመሳሪያ አይነት | የመሳሪያ ስም | ድምጽ |
|---|---|---|
| የምት | ከበሮ | ድምጻቸው እንደየአሰራራቸው ይለያያል |
| የትንፋሽ | ዋሽንት ፣ ዛዬ ፣ማይራ ወዘተ… | ዋሽንት መካከለኛ፣ ዛዬ ወፍራም እና ማይራ ቀጭን |
| የክር | ዲታ ፣ በገና እና ማሲንቆ | ዲታ እና ማሲንቆ መውፈርም መቅጠንም የሚችል ነው፡፡ በገና ወፍራም ድምጽ ይሰጠናል፡፡ |
| እርስ በርስ በመጋጨት ድምጽ የሚሰጡ | ጽናጽል ፣ ቃጭል | አንድ ድምጽ የሚሰጥ መሳሪያ ነው፡፡ |

ሰንጠረዥ 2 የሙዚቃ መሳሪያ ድምጽ

**1.ቀጭን ድምጽ፡-** በሙዚቃ መሳሪያ ተጨዋችም ይሁን በመዝሙር ዘማሪ ቀጥኖ

ወይም ወጥቶ ለጆሮአችን የሚሰማ ከሆነ ቀጭን ድምጽ እንለዋለን፡፡

**ለምሳሌ፡-** ከአገራችን የሙዚቃ መሳሪያዎች መካከል ዋሽንት ፣ ፊላ እና ጥሩምባ ቀጭን ድምጽ ያላቸው የሙዚቃ መሳሪያዎች ናቸው፡፡

**የመወያያ ጥያቄ -1**

1. በአካባቢያችሁ የሚገኙ ቀጭን ድምጽ ያላቸውን የሙዚቃ መሳሪያዎች አብራሩ?

**2. ወፍራም ድምጽ፡-** ይህ ድምጽ ደግሞ የቀጭን ተቃራኒ ሲሆን ዘማሪ ወይም የሙዚቃ መሳሪያ ተጫዋች አውርዶ ወይም አወፍሮ ሲጫወት ወይም ሲዘምር ለጆሮአችን ወፍሮ ይሰማል ፤ ይህም በሙዚቃ አነጋገር ወፍራም ድምጽ ይባላል፡፡

**ለምሳሌ፡-** ድንኬ፣ በገና እና ዛዬ

ድንገት የሚፈጠሩ የሙዚቃ ድምጽ ምልክቶች (Accidental)

ድንገት የሚፈጠሩ የሙዚቃ ድምጽ ምልክት ማለት የሙዚቃ መጻፊያ ሰሌዳ ላይ የቁልፍ ምልክት ከተቀመጠ በኋላ ከቁልፉ በቀኝ በኩል ወይም ከኖታው በግራ በኩል የሚቀመጥ ምልክት ሲሆን አንድ ሙዚቃ በምን መሰረታዊ ወይም በምን ኢመሰረታዊ እንደተጻፈ ለማወቅ የሚጠቅም ምልክት ነው፡፡

ድንገት የሚመጣ የሙዚቃ ድምጽ ምልክቶች በዓይነት ሦስት ናቸው፡፡

እነሱም፡-

- ግማሽ ድምጽ ወደ ቀኝ (sharp)
- ግማሽ ድምጽ ወደ ግራ (flat)
- ወደ ቀድሞ ድምጽ መመለስ (natural)

ግማሽ ድምጽ ወደ ቀኝ (sharp) #

ግማሽ ድምጽ ወደ ቀኝ (ሻርፐ) ማለት አንድ ቅኝትም ይሁን አንድ ኖታ በግማሽ ድምጽ መጨመር ማለት ነው፡፡

**ለምሳሌ** G A B C D E F# G

ከላይ የሚታየው “G” መሰረታዊ ቅኝት ሲሆን በዚህ ቅኝት ውስጥም አንድ ግማሽ ድምጽ ወደ ቀኝ እናገኛለን፡፡ ይህ ወደ ቀኝ የተጨመረ ቁልፍም “F” ሲሆን “F” ን በግማሽ ድምጽ መጨመር ማለት ነው፡፡ ይህ ማለት ከG-E ድረስ በነጭ ቁልፍ ብቻ ተጫውተን F ስንደርስ በነጩ ፈንታ F ፊት ለፊት ያለውን ጥቁር ቁልፍ መጫወት ነው፡፡

## የማወያያ ጥያቄ-2

1. ከላይ በሚታየው ቅኝት ውስጥ ስንት ግማሽ ድምጽ ወደ ቀኝ እንዳለ አብራሩ?
2. በአካባቢያችሁ የሚገኙ ቀጭን ድምጽ ያላቸውን የሙዚቃ መሳሪያዎች አብራሩ?

ግማሽ ድምጽ ወደ ግራ (ፍላት) ♭

ግማሽ ድምጽ ወደ ግራ (ፍላት) ማለት ስኬል ውስጥም ይሁን በኖታ የተጻፈው በግማሽ ድምጽ መቀነስ ማለት ነው፡፡

ለምሳሌ፡- F G A B♭ C D E F

ከላይ የሚታየው ስኬል “F” ሜጀር ስኬል ሲሆን በዚህ ስኬል ውስጥም አንድ ግማሽ ድምጽ ወደ ግራ አለው፡፡ ይህም “B” በግማሽ ድምጽ ወደ ግራ መቀነስ ማለት ነው፡፡ ይህ ማለት ከF-A ድረስ በነጭ ቁልፍ ብቻ ተጫውተን B ስንደርስ በነጩ ፈንታ ከB ወደ ኋላ ያለውን ጥቁር ቁልፍ መጫወት ነው፡፡

ወደ ቀድሞ ድምጽ መመለስ (ናቹራል) ♮

ግማሽ ድምጽ ወደ ቀኝ ወይም ግማሽ ድምጽ ወደ ግራ ከነበረ በት ግማሽ ድምጽ ጨምረን ወይም ቀንሰን ወደ ቀድሞ ድምጽ መመለስ (ናቹራል) እንቀይረዋለን፡፡

ለምሳሌ G A B C D E F♮ G

በምሳሌ አንድ ላይ “F” ን ወደ ቀኝ በግማሽ ድምጽ ሲጨምር ነው ያየነው ፤ እዚህ ላይ “F” ወደ ነበረበት ይመለሳል፡፡

F G A B♮ C D E F

በምሳሌ “B” በግማሽ ድምጽ ሲቀንስ አይተናል እዚህ ላይ “B” ወደ ነበረበት ይመለሳል፡፡

## 1.3. የትያትር ጥበባት፤ ትወና፣ ማዘጋጀት፣ የተውኔት ፅሁፍ እና የፊልም ጥበባት

### መግቢያ

ተማሪዎች ከዚህ ባሉ ምዕራፎች የትያትር ጥበብን ተምረዋል፡፡ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የትያትር ጥበባት ትወና ፣ ማዘጋጀት ፣ የተውኔት ፅሁፍ እና የፊልም ጥበባትን በሙዚቃ እና በውዝዋዜ እንዴት መስራት እዳለባቸው ይማራሉ፡ ፡ ትያትር ጥበባት ለሰው ልጅ ከእለታዊ እንቅስቃሴ ጋር የተያዘ በመሆኑ ድርሰት እንዴት መጻፍ እንዳለበት እና ማዘጋጀት እንዳለባቸው ይማራሉ፡፡

ተውኔት ከትውን ጥበባት ዘርፎች ማለትም ከሥነ-ጽሁፍ፣ ከሥነ-ስዕል፣ ከሙዚቃ ፣ ከውዝዋዜ ፣ ከሰርከስ ትርኢት፣ ከአስማት፣ ከኦፔራ፣ ከፊልም ጥበቦች ወዘተ ውስጥ የሚካተት ነው፡፡ ተውኔት የሰው ልጆችን የእለት ከእለት ገጠመኝ አስመስሎ እየቀዳ በጊዜና በቦታ ተወስኖ የሚከወን ታሪክ ነው፡፡ የተውኔት ድርሰት የተደረገ ታሪክ ወይም ምናባዊ ታሪክን ቃላትን እንደ አገባብ ሥርዓታቸው አስማምቶ በመደርደር የሚከወን የጥበብ አይነት ነው፡፡

### አጥጋቢ የችሎታ ደረጃ

- ▶ የትወና ጥበብን ይገልጻሉ፡፡
- ▶ የትያትር ጥበባትን ማለትም ትወና ፤ ማዘገጀት ፤ ተውኔት መጻፍ እና የፊልም ጥበባትን ምንነት ይገልጻሉ፡፡
- ▶ ተማሪዎች የተውኔት ዘውጎችን ይረዳሉ፡፡
- ▶ ተማሪዎች የተውኔት ድርሰት አላባውያንን ይረዳሉ፡፡

### ማነቃቂያ ጥያቄ -3

1. ቴአትር ምንድን ነው?

2. ትወና ምንድን ነው?

## 3.3. የቴአትር ጥበባት

ቴአትር የሰው ልጆችን የእለት ተእለት ተግባራት ለመድረክ በሚመጥን መልኩ

በማዝጋጀት ለማስተማር ለማዝናናት እና የተለያዩ ሃሳቦችን ለመግለፅ የምንጠቀምበት የጥበብ ዓይነት ነው፡፡ ቴአትር የሰው ልጆች ከሚከውኑት ኃይማኖታዊ ክንዋኔዎች ማለትም ለፈጣሪ ምስጋና ከማቅረብ የተወሰደ ጥበብ ነው፡፡ ቴአትር በውስጡ ድርሰት መፃፍ፣ ማዘገጀት፣ ተዋንያን ፣ ተመልካች፣ የድምፅ ግብዓት ፣ እና የመድረክ ዝግጅትን የያዘ ነው፡፡

ቴአትር በአንድ በተወሰነ ቦታ ላይ በቀጥታ መድረክ ፣ በተመልካቾች ፊት የዕውነተኛ ወይም ምናባዊ ታሪኮችን በምልክት ፣ በንግግር ፣ በሙዚቃ እና በዳንስ ጥምረት ለተመልካቾች ተዋንያን የሚተገብሩት የጥበብ ዓይነት ነው፡፡

## የቴአትር ዓይነቶች

በዋናነት የቴአትር ዓይነቶች ሁለት ናቸው፡፡ እነሱም አሳዛኝ/ትራጅዲ እና አስቂኝ/ ኮሜዲ ናቸው፡፡

**ሀ- አስቂኝ/ኮሜዲ ቴአትር** በባህሪው ተመልካቾችን እያዝናና የተለያዩ ቁም ነገሮችን ማስተላለፍ ወይም ማስተማር የሚቻልበት የቴአትር ዓይነት ነው፡፡ አላማው ሰዎችን በአጋጣሚ ፣ በተለያዩ ገጠመኞች የሰሩትን ስህተቶች በመድገም ፈገግታን በመፍጠር ቁም ነገሮችን ማስጨበጥ ነው፡፡

### የተግባር ሥራ-3

1. ተማሪዎች በአካባቢያዊ ባህል ሊገለፅ የሚችል አጭር አዝናኝ ቴአትር ሰርተው እንዲያሳዩ ያድርጉ?

**ለ- አሳዛኝ/መራር/ ትራጀዲ ቴአትር፡-** በዚህ ዓይነቱ ዘውግ የተፈጠሩ ወይም ምናባዊ ታሪኮችን በመጠቀም ተመልካቾችን የሚያሳዝን የትያትር ዘውግ ነው፡ ፡በመሪ (ዋና ገፀ-ባህሪያት) በሚደርስ አሳዛኝ ክስተቶች ተመልካቾች የራሳቸውን ታሪክ እስኪመስላቸው ለማሳዘን የሚሰራ የቴአትር ዘውግ ነው፡፡

## ድንገቴ ፈጠራ/ኢምፕሮቫይዜሽን

ድንገቴ ፈጠራ ያልተፃፈ በሃሳብ ብቻ የምናውቃቸውን እና ገፀ-ባህሪያትን በመከፋፈል ከርዕስ ጉዳዩ ሳይወጡ ሃሳቦችን እየፈጠሩ መተወን ነው፡፡ ህፃናት የቤተሰብ ሚናን በመውሰድ የእናት፣የአባት፣የልጅ ሚናን በመውሰድ የሚጫወቱበት(የሚተውኑበት) ምንም ዓይነት የተፃፈ ድርሰት ሳያነቡ የሚተዉኑበት የተውኔት ዓይነት ነው፡፡

## ቴአትር የሚይዛቸው ነጥቦች

ቴአትር የትወና የጥበብ ዓይነት ሲሆን በተመልካቾች ፊት በቀጥታ እየከወንን የምናቀርበው የጥበብ ዓይነት ነው። ቴአትር ለመስራት ድርሰት፣ አዘጋጅ፣ ተዋንያን፣ የመድረክ ባለሙያዎች ፣ የመድረክ ዲዛይን ባለሙያ፣ አልባሰት ፣ የአልባሳት ዲዛይነር፣ የገፅ ቅብ ባለሙያ እና አስፈላጊ ቁሳቁሶች ያስፈልጋሉ።

## 1.3.1. ትወና

ትወና:- የሰው ልጆች ከተፈጠሩበት ጊዜ አንስቶ ሰዎች የእለት ከእለት ኑሯቸውን ለማስቀጠል ሲሉ እየከወኑ እንደመጡ እና ትወና ከሰዉ ልጆች አመጣጥ ጀምሮ እንደመጣ በርካታ የዘርፉ ምሁራን ያስቀምጣሉ። ቢሆንም በትወና ሙያ ቴስፒስ የአለማችን የመጀመሪያው ተዋናይ እንደሆነም በርካቶች ይስማማሉ። ትወና አካላትን ፣ የፊት ገጽታን ፣ ድምጽን፣ እንቅስቃሴን በመጠቀም ታሪክን የሚያስተላልፍ የሙያ ዓይነት ነው።

ትወና ማደግ እና ማዳበር አለበት ተዋናይ ለታዳሚው አስፈላጊ የሆነውን የባህሪ እና የፕሮጀክት ምንነት ማወቅ አለበት። ተዋናይ በመድረክ ላይ ሊያየው የሚችለውን ሁሉ እውነት እና እምነት በጥሩ ሁኔታ የተከናወነ የአካል ብቃት እንቅስቃሴ በተለይ በአሳዛኝ ጊዜያት በጨዋታ ውስጥ ለአንድ ተዋናይ አስፈላጊ ነው።

ከትወናው ከተሰጡት ሁኔታዎች አንፃር ማመቻቸቶች አመክንዮአዊ መሆን አለባቸው። ቴምፖ-ሪትም ፣ ቴምፖ-ትርጉም ፍጥነት እና የሪትም-ትርጉም የተለያየ የልምድ ጥንካሬዎች ሊኖሩት ይገባል። ትወናው እውነተኛ ለመምሰል ተዋናይ ሰው ሰራሽ መሆን አለበት። ትወና በአካል እና በድምፅ አማካይነት ስሜቶችን ወደ ተከታታይ ቋሚ አቀማመጥ እና አመለካከቶች የሚቀይር የመግለፅ ሥርዓት ነው።

**ተዋናይ በ3 መሠረታዊ ነገሮች ኀበዝ ይሆናል።**

1. ተወላጅ ችሎታ (ተሰጥኦ)።
2. ሥልጠና (አጠቃላይ ትምህርትን ጨምሮ)።
3. ልምምድ ሥልጠና እና ትርጓሜዎች;- መዝናናት ፣ ማተኮር ምናብ እና ምልከታ።

**ሀ) ድምጽ እና አካል ለተመልካቾች ለመግለጽ የቁጥጥር ድምጽን እና አካልን መማር አለበት።**

1. መረዳት

2. ልምምድ

3. ተግሣጽ

አንድን ትወና ከመተወናችን በፊት የምንተውነውን ገፀ-ባህሪ መረዳት ማወቅ አስፈላጊ ነገር ነው። በመቀጠል የተረዳነውን ገፀ-ባህሪ መለማመድ ተከታዩ ተግባር ነው በመቀጠልም አዘጋጅ ሌሎችንም ጨምሮ የሚሰጡትን ተግሳጽ ወይም አስተያየት በመቀበል መተወን የኀበዝ ተዋንያን ተግባር ነው፡

## ለ) ምናባዊ እና ምልከታ

የተሰጣችሁን ገፀ-ባህሪ በቀላሉ ለመረዳት እና ለመተወን በተመሳሳይ ድርግያዎች በተለያዩ ግንኙነቶች ውስጥ ያሉ ሰዎችን ይመልከቱ እና ያስቡ። “ተፅዕኖ ያለው ማህደረ ትውስታ” የሚለው ብዙውን ጊዜ ተዋናዩ የማስታወስ አጠቃቀም በሕይወቱ ውስጥ የሚመሳሰሉ ወይም ሊያስነሱ የሚችሉ ፣ በመድረክ ላይ ባለው ገጸ-ባህሪ የሚፈለጉትን ስሜቶች ለማግኘት የሚያገለግል ነው።

ይህ የስሜታዊ ትውስታን (ያለፈውን ስሜት ማስታወስ) ፣ የስሜት ህዋሳት (ስሜቶችን በማስታወስ) ፣ እና መተካት በትወና ውስጥ ያለውን ገጸ -ባህሪ ሰው በአእምሮ መተካት በእውነተኛ ህይወት ውስጥ የሆነ ሰው ማስታወስ በቀላሉ እንድንገሪዳ እንድንተውን ያደርጋል።

## ሐ) ቁጥጥር እና ተግሣጽ

ተዋናዮች የትኩረት ሀይሎቻቸውን እንዴት ማጎልበት እንዳለባቸው መማር አለባቸው። አሁን ባለው ሁኔታ (በመድረክ ላይ ተዋናይ መሆን ፣ ተመልካች ፊት ለፊት) እና የጨዋታው አውድ ላይ ገጸ-ባህርን በመወከል መከወን እንዳለበት/ባት ማወቅ አለበት/ባት። ምን እያደረግኩ ነው ፣ እኔ እንዴት ነኝ ብሎ በመለየት ማወቅ ይኖርበታል/ባታል።

## 1. ሚናውን ይተንትኑ

ገፀ-ባህሪው ምን እንደሚፈልግ ፣ አስተሳሰቡ ፣ ባህሪው ፣ እምነቱ ወዘተ ከድርሰቱ ደጋግመው በማንበብ ለማወቅ ይጣሩ የሌሎችንም ጠይቀዉ ይረዱ።

## 2. ዓላማዎችን ይወቁ

በዋናነት የገጸ-ባህርው/ሪዋ መገኘት አላማው ምን ልያሳካ/ልታሳካ እንደተገኘ/ች ለይተው ይወቁ ወይ ይለዩ።

## 3. የባህሪ ግንኙነቶች

ገጸ-ባህሪችሁ ከሌሎች ገጸ-ባህሪዎች ጋር ያለውን ግንኙነት ለይቶ ማወቅ ወሳኝ ነው፡፡

### 4. በሚንተውንበት ጊዜ ማሟላት ያለባቸው ተግባራት

ተዋናዮች ገፀ-ባህሪያቸው ከጭብጡ እና ከጨዋታው ድርጊት ጋር እንዴት እንደሚዛመዱ መረዳት አለባቸው፡፡

1. በገፀ-ባህርው ውስጥ ይሁኑ እርስዎ የሚሉትን ሳይሆን እንዴት እንደሚሉት በገጸ-ባህሪው አዕምሮ ውስጥ የሚሄዱ ድርጊቶች እና ያልተነገሩ ሀሳቦች- በመስመሮቹ መካከል ለድርጊቶች መሠረታዊ ፣ ሥነ ልቦናዊ ፣ ስሜታዊ ፣ ተነሳሽነት ለይተው ይወቁ፡፡
2. በአጠቃላይ ወደ ልምምድ ይግቡ

ድምጸትን እንቅስቃሴን በዋናነት ስሜትን በመጠቀም ወደ ልምምድ ይግቡ የስሜት መለዋወጦችን ለይቶ ማወቅ የግድ ይላል፡፡

### የድምፅ ባህሪዎች

ተዋናዮች የድምፅን ጥራት (ትንበያ የመስማት ችሎታ ፣ የድምፅ ፣ የመለዋወጥ ፣ የመለኪያ ፣ ደረጃ) እና የንግግር ችሎታቸውን (ቃላትን በግልፅ እና በትክክል በመጥራት) ለማሻሻል የተለያዩ መልመጃዎችን ማወቅ አስፈላጊ ነው፡፡

ጎበዝ ተዋንያን የተለያየ ገጸ-ባህርያትን ይለማመዳል ይተውናል፡፡ ጎበዝ ተዋናያን ለመሆን ልምምድ እና መማር አስፈላጊና አስፈላጊ ነው፡፡ ቴአትር የትውን ጥበባት ውህደት ነው፡፡ የትውን ጥበባት የምንላቸው የጥበብ ዓይነቶች የጥበብ ባለሙያው የራሱን ሰውነት ፣ ድምፅ እና እንቅስቃሴዎች በመጠቀም የሚከውናቸውን የጥበብ ዓይነቶች ናቸው፡፡ እነዚህም ቴአትር ፣ ሙዚቃ ፣ ውዝዋዜ እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

## 1.3.2. የተውኔት ጽሁፍ ዘውጎች

የተውኔት ዘውግ የተውኔት ድርሰት ጸሀፊው አንድን ርእሰ-ጉዳይ መሰረት አድርጎ ጽፎ የሚያቀርብበት የተውኔት ዝርያ ነው፡፡ ዘውጎች በርካታ ቢሆኑም በዋናነት በሁለት ዝርያ እንከፍላቸዋለን፡፡ እነርሱም፡-

- አስደሳች (አስቂኝ ወይም ኮሜዲ)
- አሳዛኝ (ትራጄዲ) ናቸው ፡፡

በዋናነት ከነዚህ በተጨማር ሶስት አይነት በጭብጥ፤ በቅርጽ እና በቴክኒክ የምመደቡ ዘውጎች አሉ፡፡ እነሱም፡-ጭብጣዊ ዘውግ ፤ቅርጻዊ ዘውግ ቴክኒካዊ ዘውግ ወዘተ ናቸው፡፡

አንድ የተውኔት ድርሰት ጸሐፊ ለመጻፍ ሲነሳ ከላይ ከጠቀስናቸው ሁለት አይነት ዝርያዎች በመነሳት መጻፍ የሚፈልገውን አስደሳች ወይም አሳዛኝ የተውኔት አይነት ይመርጥና ከሶስቱ ዘውጎች አንዱን መርጦ ይጽፋሉ፡፡

## የተውኔት ድርሰት አላባዊያን

የተውኔት ድርሰት አላባዊያን የተውኔት ድርሰት የአካል ክፍሎች ናቸው ማለት ይቻላል፡፡ ቤት ስሰራ (በሲሚንቶ ፣ በአሸዋ ፣ በድንጋይ) ወዘተ እንደሚሰራ ሁሉ የተውኔት ድርሰትም የሚጻፈው በተውኔት ድርሰት አላባዊያን ነው፡ የተውኔት ድርሰት አላባዊያን የምንላቸው የሚከተሉት ናቸው፡-

1. መቼት
2. ገጸ-ባህሪ
3. ቃለ-ተውኔት
4. ጭብጥ
5. ሴራ

### 1. መቼት

መቼት የሚባለው የተውኔቱ ጊዜና ቦታ ነው

### 2. ገፀ-ባህሪ

በፈጠራ ታሪክ ውስጥ ያሉ የምናብ አለም ሰዎች ናቸው፡፡

### 3. ቃለ-ተውኔት

በታሪክ ውስጥ የሚገኝ የገጸ-ባሪያት ምልልስ ወይም ንግግር ነው፡፡

### 4. ጭብጥ

ተውኔቱ ሊያስተላልፍ የፈለገው ዋና ማዕከላዊ ሃሳብ ወይም አስተምሮት ነው፡፡

### 5. ሴራ

ሴራ ታሪክ ሲደመር ግጭት ሲሆን ምክንያትና ውጤትን መሰረት አድርጎ በታሪክ ውስጥ የሚጻፍ የግጭት አይነት ነው፡፡ ታሪክ የምንለው መነሻ ሃሳብ ፣ መካከለኛ

ሃሳብ እና ማጠቃለያ ሃሳብ ያለው ሲሆን ታሪክ ከጊዜ አኳያ ደርጊቶች በቅደም ተከተል ተተንትነው የሚቀመጡበት ክፍል ነው።

ግጭት በታሪክ ውስጥ የሚፈጠሩ አለመግባባቶች ናቸው። የተለያዩ አይነት ግጭቶች አሉ። እነርሱም፡-

- ሰው ከ ፍጡራን ጋር
- ሰው ከ ተፈጥሮ ጋር
- ሰው ከ ፈጣሪ ጋር
- ሰው ከ እራሱ ጋር የምያደር

## አዘጋጅ

ዝግጅት የምንለው የአንድን ስራ ቅንብር የምንለው ነው። ስራ ተጀምረው እስኪያልቅ ድረስ ያለው ስነ-ጥበባዊ ወይም አርቲስትክ እና ድራማውን ውበቱን የሚጠብቅ የሚቆጣጠር የስራ ክፍል ነው። አዘጋጅ የአንድ ስራ ጀርባ አጥንት ነው። አንድ ሰው ጀርባ አጥንት ከሌለ ቆሞ መራመድ እና መንቀሳቀስ አይችልም የጀርባ አጥንት ለሁሉም ነገር አስፈላጊ ነው። ለአንድ ትያትር ክፍል ለሬድዮ እና ለቴሌቪዥን ድራማን ዝግጅት አዘጋጅ ወሳኝ የጀርባ አጥንት ነው። አዘጋጅ ተዋንያዎችን በትያትር ውስጥ የሚገኙ ባለሙያዎችን የሚመራ ነው። የቴክንክ ባለሙያዎችን ተዋንያን በማዘዝ በመቆጣጠር የማዘዝ መብት እና ሀላፍነት ያለው ነው። በዋናነት ፕሮድውሰሩ ደራሲው እና ገንዘብ ያዥ የበላይ ጠባቅዎች ናቸው። ፕሮድውሰሩ የፊልሙን ፣ የትያትሩን ሙሉ ወጭ የሚያወጣ ባለቤት ነው።

አዘጋጅ በውስጡ ተዋንያንን ፣ ፕሮዳክሽን ማናጀር የቴክኒክ ባለሙያ የምንላቸው መድረክ አስተባባርና የመብራት ዲዛይነር እና ባለሙያዎች የድ ምፅ ዲዝይነር እና ባለሙያዎች ፣ የአልባሳት ድዛይነር እና ባለሙያ ፣ ቃልጠቋም ፣ የገጽ ቅብ ባለሙያ ፣ የቁሳቁስ ባለሙያ እነዚህን ሁሉ በመቆጣጠር የማዘዝ ሀላፍነት ያለው ነው።

## የመድረክ ክፍሎች

| | | |
|---|---|---|
| የኋላ ግራ | የኋላ መሀል | የኋላ ቀኝ |
| የግራ መሀል | መሀል | የቀኝ መሀል |
| የፊት ግራ | የፊት መሀል | የፊት ቀኝ |

ከላይ የተዘረዘሩ የመድረክ ክፍሎች ገፀ ባህሪያት ከተሸከሙት ሀሳብ ክብደቶች በየመድረክ ክፍሎች በመንቀሳቀስ ሀሳባቸውን ያስተለልፋሉ። ተውኔት ዋና ቁም ነገር የያዘ ገፀ ባህሪ መሀሉን ክፍል በመጠቀም ሀሳቡን ያስተላልፋል። በመቀጠል ብዙ ሀሳብ የሌላቸው ገባር

ታርኮችን የያዙ ገፀ ባህርዎች እንዲሁም በትዕይንቱ ከባድ ያልሆነ ሀሳብ የያዘ የኃላ መድረክ ክፍሎች በመጠቀም ያስተላልፋሉ፡፡ ጠንከር ያለ ሀሳብ ጉዳየች ስገጥሙ የፊተኞች የመድረክ ክፍል በመጠቀም ይገልጣሉ፡፡ የኃላ የመድረክ ክፍል ተለቅ ያለ መካከለኛና ከዛ በላይ ሀሳቦችን ስያዝ የመሀለኛውን ክፍል በመጠቀም ሀሳቦችን ያስተላልፋሉ፡፡ ተውኔቱ ትልቅ እና ዋና የሚባሉ ወደ ጡዘት የሚያደርሱ ሀሳቦችን ከፊት የመድረክ ክፍል በመጠቀም ነው፡፡

## 1. ቅድመ ዝግጅት ተግባር

ቅድመ ዝግጅት ተግባር፡- በዚህ ተግባር አዘጋጅ ከደራሲ ጋር በመሆን የሚተገብር ተግባራት ናቸው፡፡ ስለአጠቃላይ ገፀባህሪያት አሳሳል ስለግጭት የተውኔት መዋቅሮች ፣ የቃል ተዉኔት ደረጃ ፣ የትነት ስልትና በግጭት ዘር የሚነሱ ሀሳቦች ከደራሲው ጋር በመሆን ያጣራሉ፡፡ የድርሰት ፅሁፍ ይተነትናል ፡፡ ተዋንያን ለገፀ-ባህሪያት ይመረጣል በምን ያህል ጊዜና ወጪ እንደምያልቅ ያቅዳል ፣ የቴክኒክ ባለሙያዉ ይመርጣል ፣ ተግባራትን ይሰጣል፡፡

## 2. የዝግጅት (የልምምድ) ወቅት ተግባር

የዝግጅት (የልምምድ) ወቅት ተግባር፡ - ይህ ተግባር ብዙ ጊዜና ጉልበትን የሚፈጅ ነው፡፡ የሚያጋጥሙ ልምምዶችና ውይይቶችን ያበዙበታል አዘጋጁ ለተዋናያንና ለቴክኒክ ባለሙያወች ተግባራትን ፣ ገፀ-ባህሪያትን ከሰጠ በኃላ ጥያቄ የፈጠረባቸውን በጋራ በመፍታት ወደ ልምምድ እንዲገቡ ድዛይነሮች እና የዲዛይን ስራ እንዲሰሩ እና ጀምሮ የሚያደርግበት የዝግጅቱ ከባድ ክፍል ነው፡፡

## 3. የትውን ወቅት ተግባራት

የትውን ወቅት ተግባራት፡- አዘጋጅ ደራሲውን ካገኘ ከጅምሩ እስከ መጨረሻ የማማከር የመጠየቅ ስራ እየስራ ውሳኔዎችን ያስተላልፋሉ፡፡ ከተዋንያንና ከባለሙያዎች ጋር ይወያያል፡፡ ከደራስ ጋር በመወያየት መቀየር መቀነስ ያለባቸው ነገሮችን በመለየት በውይይት በመተማመን ድራማዊ ዉበትን በማጉላት ከተዋንያንና ከባለሙያዎች ጋር በመወያየት ስነ-ጥበባዊ ውበቶችን የምናሳድግበት ለመድረክ የምናበቃበት የመጨረሻ የተግባር ክፍል ነው፡፡

## 1.4. የውዝዋዜ ጥለቶች እና በውዝዋዜ ታሪኮችን መፍጠር

ውዝዋዜ በቀጥታ ወይም በካሜራ ፍት የሚንከናወነው የትወና ጥበብ ነው፡ ፡ ጥለቶችን ለመፍጠር የውዝዋዜ መሰረቶችን ወይም አለባዊያን ለይቶ ማወቅ

ያስፈልጋል፡፡ በዋናነት ውዝዋዜ በሁለት ይከፈላል፡-

1. ባህላዊ ውዝዋዜ
2. ዘመናዊ ውዝዋዜ

1. ባህላዊ ውዝዋዜ ማለት የአንድ አከባቢን አኗኗር ዘዴ ባህል ወግ የሚያሳይ ነው፡፡
2. ዘመናዊ ውዝዋዜ ማለት በፈለግነው ልክ የሚንጨምረውና የሚንቀንሰው በራስ ፈጠራ የሚሰራ ነው፡፡

እነዚህ መሰረቶች ከወቅን የራሳችን ጥለቶችን ለመፍጠር አንድ ደራስ ድርሰቱን ከመጣፉ በፍት በምናቡ የሚጽፋን ይፈጥራል፡፡ እንደዛው የራሳቸውን ውዝዋዜ ጥለቶችን ለመፍጠር በአዕምሯችን የሚንፈልገውን ታርኮችን መፍጠር ከዛ ጠለቶችን በአዕምሯችን ፈጥረን መጨመር ⁞ መቀነስ ⁞ ማፋጠን ⁞ በማዘገየት ከለሎች ጠለቶች ጋር ማቆራኘት ይኖርብናል ከዛም አቋቋም መለየት እና መፍጠር ያስፈልጋል፡፡ የሚፈጠረው አቋቋም ወይም ኬሮግራፍ W M n U L 7 O V I I እነዚህና ለሎችን አቋቋም አይነቶችን ይጠቀማሉ፡፡

## የተግባር ሥራ-5

1. በአራት ቡድን ተከፋፍላችሁ ቀላል እና አጭር የተውኔት ጽሁፍ በማዘጋጀት እና በቂ ልምምድ በማድረግ በክፍል ውስጥ አቅርቡ?
2. በቡድን በቡድን ተከፋፍላችሁ ባህላዊ ውዝዋዜ እና ዘመናዊ ውዝዋዜ በማዘጋጀት እና በቂ ልምምድ በማድረግ ለክፍል ተማሪዎች አቅርቡ?
3. ባቀረባችሁት ስራ ላይ ውይይትና ሃሳብ ተለዋወጡ?

## ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ የትውን እና የእይታ ጥበባት ምንነት ተምራችኃል፡፡ የትውን እና የእይታ ጥበባት የሰው ልጆች ያለ ገደብ መግባባት የሚችሉበት ቋንቋ ነው ፡፡ ልክ እንደ ሌሎች ቋንቋዎች የትውን እና የእይታ ጥበባት የራሳቸው የሆነ መዝገበ ቃላት እና የቋንቋ ሥርዓት አላቸው፡፡ የትውን እና የእይታ ጥበባትን መዝገበ ቃላት የሥነ-ጥበብ አላባዊያን እንላቸዋለን የቋንቋ ሥርዓታቸውንም የሥነ-ጥበብ መርሆዎች እንላቸዋለን፡፡ እነዚህ አላባዊያን እና መርሆዎች በተለያዩ፡፡ የትውንና የእይታ ጥበባት ውስጥ የተለያየ ስያሜ ቢሰጣቸውም አገልግሎታቸው ግን ተመሳሳይ ነው፡፡

# የክለሳ ጥያቄዎች

## ሀ) የሚከተሉትን ጥያቄዎችን እዉነት ወይም ሀሰት በሉ።

1. ተማሪዎች የእይታና የትውን ጥበባትን ከተማሩ በኃላ መግለጥ ይችላሉ።
2. የህትመት ጥበብ ከእይታ ጥበባት አንዱ ነው።
3. ግጭት ማለት በታሪክ ውስጥ የሚፈጠር አለመግባባት ነው።
4. ኪነ ንድፍ በትውን ጥበባት መካከል ይመደባል።
5. ቃለ-ተውኔት በታሪክ ውስጥ የሚገኝ የገጸ-ባሪያት ምልልስ ነው።

## ለ) የሚከተሉትን ጥያቄዎችን ትክክለኛውን መልስ ምረጡ

1. ለኪነንድፍ ስራ የማያገለግለው ቁስ የቱነው ?
   - ሀ) እርሳስ
   - ሐ) ቀለም
   - ለ) ከሰል
   - መ) ማርከር
2. ለመሰረታዊ ቅኝት ስንት የሙዚቃ ቁልፎች አሉ?
   - ሀ) ስድስት
   - ሐ) አምስት
   - ለ) አራት
   - መ) ሰባት
3. ____________ጊዜንና ቦታን ይገልጣል?
   - ሀ) ሴራ
   - ሐ) መቼት
   - ለ) ጭብጥ
   - መ) ቃለ ተውነት
4. ከሚከተሉት ውስጥ የእይታ ጥበብ አይነት ያልሆነው የቱ ነው ?
   - ሀ) ኪነ ንድፍ
   - ሐ) ኪነ ህንፃ
   - ለ) ትወና
   - መ) የህትመት ጥበብ

## ሐ) አዛምዱ

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ግማሽ ድምጽ ወደ ግራ | ሀ. # |
| 2. ግማሽ ድምጽ ወደ ቀኝ | ለ. ♭ |
| 3. ወደ ቀድሞ ድምጽ መመለስ | ሐ. ♮ |

## መ) የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ

1. የእይታ ጥበብ ዓይነቶችን ጻፉ?
2. የትያትር ዓይነቶች ስንት እንደሆኑ ዘርዝሩ?
3. የድምጽ ዓይነቶችን ግለጡ?
4. አዘጋጅ የሚባለው ማነው? ተግባሩስ?

# ምዕራፍ ሁለት

## 2. የስነጥበብ መሰረቶች

### መግቢያ

በፈጠራዊ አገላለጽን ሁሉም ሰው እንደ የአከባቢያቸው ከተለያየ ነገር በማወቅ ፣ በመረዳት ፣ በመገንዘብ እና እንድሁም ለተለያየ አገልግሎቶች እንደሚውል ያውቁና በተግባርም በደረጃቸው ተገልግሎባቸው እንዳለፉ ይታመናል፡፡ በመሆኑም በዚህ ርዕስ ላይ ስለፈጠራ የበለጠ እውቀትና ግንዛቤ እንድያገኙ ማድረግ የዚህ ምዕራፍ ትኩረት አቅጣጫ ነው፡፡ በዚህም መሠረት ተማሪዎች ከላይ የተዘረዘሩት መሰረታዊ ነገሮች በስልተምታዊ መዝሙር ፣ ሙዚቃ መጻፊያ ሰሌዳን ፣ ወፍራምና ቀጭን ድምፅን ፣ በሙዚቃ መጻፊያ ሰሌዳ ላይ ማስቀመጥን ፣ በወፍራምና በቀጭን ድምፅ በመካከል ያለው ልዩነት ማወቅ በራሳቸው ተሳትፎ በተማሪ ተኮር የማስተማር ዘዴዎች በመታገዝ ትምህርቱን እንዲማሩ ይጠበቃል፡፡

መስመር የንድፍ ብቻ ሳይሆን በትዕይንታዊ ጥበባት ሁሉ የጀርባ አጥንትና ዋና የባሕርያት ጉልበት ያለው መገለጫ ነው፡፡ ልምምዶች በጥረትና በትጋት እንዲሁም በጥሞና ክትትል ከተደረገበት የመስመር ባሕርይ ጥናት ተጨማሪ የሥነ-ልቦናዊ ዕውቀት ትርፍ እንዳለው ይታመናል፡፡

### አጥጋቢ የችሎታ ደረጃ

- ፈጠራዊ አገላለጽ ይገልፃሉ
- ፈጠራዊ አገላለጽ ይዘረዝራሉ
- ትውንና የእዕታ ጥበብን በመጠቀም ፈጠራዊ አገላለጽ ያስረዳሉ

## 2.1. ስልተ ምታዊ መዝሙሮች ከሙዚቃ መጻፊያ ሰሌዳ (ወፍራም እና ቀጭን ቁልፍ) ሰሌዳ መስራት እና መዘመር

### 2.1.1. የሙዚቃ መጻፍያ ሰሌዳ (ስታፍ)


**አጥጋቢ የችሎታ ደረጃ**

- የሙዚቃ መጻፊያ ሰሌዳ መስመሮችን ይዘረዝራሉ፡፡
- የሙዚቃ መጻፊ ሰሌዳ ሰርተው ያሳያሉ፡፡
- ቀላል ኖታዎችን ያነባሉ፡፡

**ማነቃቅያ ተግባር-1**

1. የሙዚቃ መጻፊያ ሰሌዳ ማለት ምን ማለት እንደሆነ በቡድን ተወያዩ?

የሙዚቃ መጻፊያ ሰሌዳ፡- ማለት አምስት እኩል ወደ ጎን ወይም አግድም የተሰመሩ መስመሮች ሲሆኑ እና በውስጡም የሚገኙ አራት ባዶ ቦታዎች አጠቃልሎ የያዘ የሙዚቃ መጻፊያ ሰሌዳ ይባላል፡፡ የተለያየ የሙዚቃ ምልክት (የጊዜ ምልክት ፣ ወደታች የሚሰመር መስመር ፣ የኖታዎች እና የዕረፍት ምልክቶ ፣ የቁልፍ ምልክቶች ፣ በድንገት የሚፈጠሩ ድምጾችን ያካተተ ነው፡፡ሁሉም በሙዚቃ መጻፊያ ሰሌዳ ላይ የሚጻፉ ምልክቶች ከግራ ወደ ቀኝ ይነበባሉ፡፡




ምስል 6. የሙዚቃ መጻፊያ ሰሌዳ

**የተግባር ሥራ-1**

1. ተማሪዎች አምስት እኩል መስመሮች ወደ አግድም አስምሩ?

**የኖታና የዕረፍት ምልክት**

የኖታ ምልክት፡- ማለት ድምፅ አሰምቶም ሆነ ሳያሰሙ ሙዚቃን መጫወት ነው


፡፡ የዕረፍት ምልክት ማለት ዝም ማለት ወይም ማረፍ ማለት ነው፡፡

## ድምጽ




ሙሉ 4 ምት   ግማሽ 2 ምት   ሩብ 1 ምት   1/8ኛ ½ ምት   1/16ኛ ¼ ምት

## እረፍት




ሙሉ 4 ምት   ግማሽ 2 ምት   ሩብ 1 ምት   1/8ኛ ½ ምት   1/16ኛ ¼ ምት

ከላይ በኖታውና የዕረፍት ምልክት ሥር የሚታየው ቁጥር የሚመለክተው 1 ሙሉ ኖታ ወይም ሙሉ ዕረፍት መሆኑን 1/2 ግማሽ ኖታ ወይም ግማሽ ዕረፍት 1/4 ዕሩብ ኖታ ወይም ዕሩብ ዕረፍት 1/8 የዕሩብ ኖታውን ወይም ዕረፍት በሁለት ቦታ ማካፈል 1/16 ዕሩብ ኖታን ወይም ዕረፍትን በአራት ቦታ ማካፈል ማለትን ይገልፃል፡፡

ኖታ ዜማ አሰምተው መጨዋት እና ዕረፍት ማረፍ እንደሆነ በለፈው ትምህርት ላይ ያየን ቢሆንም አንድ ሙሉ እና አንድ ሙሉ ዕረፍት እኩል የጊዜ ቆይታ መኖሩን መዘንጋት የለብንም፡፡

| የኖታ ስም | የኖታ ምልክት | የጊዜ ቆይታ | የዕረፍት ስም | የእረፍት ምልክት |
|---|---|---|---|---|
| ሙሉ ኖታ | 𝅝 | አራት ምት የጊዜ ቆይታ አለው | ሙሉ ዕረፍት | 𝄻 |
| ግማሽ ኖታ | 𝅗𝅥 | ሁለት ምት የጊዜ ቆይታ አለው | ግማሽ ዕረፍት | 𝄼 |
| ሩብ ኖታ | ♩ | አንድ ምት የጊዜ ቆይታ አለው | ሩብ ዕረፍት | 𝄽 |
| 1/8ኛ ኖታ | ♪ | ግማሽ ምት አለው | 1/8ኛ ዕረፍት | 𝄾 |
| 1/16ኛ ኖታ | 𝅘𝅥𝅯 | አንድ ምት ለአራት ይከፈላል | 1/16ኛዕረፍት | 𝄿 |


ሰንጠረዥ 1. ኖታ እና ዕረፍት ምልክት

ከላይ እንደተገለፀው የሙዚቃ የልብ ትርታ ምት ነው፡፡ እነዚህ በትክክል በመረዳት ማጥናት አስፈላጊ ነው፡፡ ከዚህ በታች የአነባበብ ዘዴዎችን እንመልከት አንድ ምት ማለት በእግራችን ወይም በእጃችን በማጨብጨብ እናጥናቸው፡፡

♩ (ሩብ)ኖታ፡- ይህ ምልክት አንድ ምት አለው፡፡ በእግራችን ተረከዝ መሬት በመረገጥ ከፊት ያሉትን የእግር ጣቶች ወደ ላይ በማንሳት አንድ ምት በመምታት ወደ ታች መሬት በመምታትና በማንሳት አንድ ምት እናገኛለን፡፡


መሬት እግር እንደገና ቦታው ሲመለስ ያለው ድምፅ በእኩል ወደታችም ወደ ላይም ድምፁን ሳይቀይር የተነሳበት ቦታ ሲመለስ የአንድ ምት ዋጋ እናገኛለን፡

**ለምሳሌ፡-** ከዚህ በታች ያለውን ‹‹ታ›› በማለት እናንብብ፡፡





የእዚህን የሩብ ኖታ ዋጋ በትክክል ከተረዳን ክፍልፋዮቻቸውን በዚህ መሰረት በመመነዛዘርና እኩል ዋጋ እየሰጠናቸው እናነባቸዋለን፡፡

ልክ እንደዚህ አራት ምት ያለውም ድምፁን ሳያቋርጥ አራት ጊዜ በመርገጥና በማንሳት እኩል ዋጋ በመስጠት መጫወት ነው፡፡





## የተግባር ሥራ-2

1. ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ኖታዎችን እጅ እያወጣችሁ ተራ በተራ አንብቡ?




በዚህ መሰረት ሁለት ምት ያለው ከላይ አንድ ምት የነበረውን ድምፅን ሳያቋርጥ ሁለት ጊዜ መርገጥና ማንሳት ማለት ነው፡፡






### የተግባር ሥራ-3


1. ተገቢውን የጊዜ ቆይታ በመስጠት ከዚህ በታች የተቀመጡትን ሩብ ዕረፍት ምልክቶችን በመቁጠር በራሳችሁ ተለማመዱ?




1/8ኛ በአንድ ምት ውስጥ ሁለት እኩል ቦታ ከፍለን እግራችን ወደ ታች ሲመታ አንድ ድምጽ ወደ ላይ ሲነሳ አንድ ድምጽ መስጠት መቻል ነው፡፡

### የተግባር ሥራ-4

1. ከዚህ በታች ለተዘረዘሩት ሩብ ለእያንዳንዱ አንድ ምት እየሰጣችሁ ተለማመዱ?




1/8ኛ በአንድ ምት ውስጥ ሁለት እኩል ቦታ ከፍለን እግራችን ወደ ታች ሲመታ አንድ ድምጽ ወደ ላይ ሲነሳ አንድ ድምጽ መስጠት መቻል ነው።





## የተግባር ሥራ-5

1. ተገቢውን የጊዜ ቆይታ በመስጠት ከዚህ በታች የተቀመጡትን 1/8ኛ ኖታ ምልክቶችን በመቁጠር በራሳችሁ ተለማመዱ?



1/16ኛ አንድ የሩብ ኖታ ዋጋን አራት እኩል ቦታ ከፍለን እግራችን ወደ ታች ሲመታ ሁለት ድምጽ ወደ ላይ ሲነሳ ሁለት ድምጽ መስጠት መቻል ነው።





## የተግባር ሥራ-6

1. ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ኖታዎችን ተለማመዳችሁ እጅ እያወጣችሁ ተረ በተራ አንብቡት?



በታች ያለውን የዕረፍት ምልክቶችን ድምጽ ሳናሰማ የጊዜ ቆይታ ብቻ በአግባቡ ጠብቀን መቁጠር አለብን። ሙሉ ዕረፍት አራት ምት የጊዜ ቆይታ አለው።




## የተግባር ሥራ-7

1. ተገቢውን የጊዜ ቆይታ በመስጠት ከዚህ በታች የተቀመጡትን ሙሉ ዕረፍት ምልክቶችን እግራችሁን መሬት በመምታት እና በማንሳት አንብቡ?



ግማሽ ዕረፍት ሁለት ምት የጊዜ ቆይታ አለው፡፡

የድ.መነሻ ነጥብ የድ.መድረሻ ነጥብ





## የተግባር ሥራ-8

1. ተገቢውን የጊዜ ቆይታ በመስጠት ከዚህ በታች የተቀመጡትን ባለ ግማሽ ዕረፍት ምልክቶችን ተለማመዱ?




ዕሩብ ዕረፍት አንድ ምት የጊዜ ቆይታ አለው፡፡





## የተግባር ሥራ-9

1. ተገቢውን የጊዜ ቆይታ በመስጠት ከዚህ በታች የተቀመጡትን ሩብ ዕረፍት ምልክቶችን በመቁጠር በራሳችሁ ተለማመዱ?




ድምጽ ሳይወጣ እግር ወደ ታች ስንመታ አንድ 1/8ኛ እና እግር ወደ ላይ ሲነሳ አንድ 1/8ኛ ዋጋ መስጠት ነው፡፡








## የተግባር ሥራ-10

1. ተገቢውን የጊዜ ቆይታ በመስጠት ከዚህ በታች የተቀመጡትን 1/8ኛ ዕረፍት ምልክቶችን በመቁጠር በራሳችሁ ተለማመዱ?




ድምጽ ሳይወጣ እግር ወደ ታች ሲመታ ሁለት 1/16ኛ እና እግር ወደ ላይ ሲነሳ ሁለት 1/16ኛ ዋጋ መስጠት ነው፡፡







## የተግባር ሥራ-11

1. ተገቢውን የጊዜ ቆይታ በመስጠት ከዚህ በታች የተቀመጡትን 1/16ኛ ዕረፍት ምልክቶችን በመቁጠር በየቡድኑ ተለማመዱ፡፡




## የተግባር ሥራ-12


1. ከዚህ በታች የተጻፉትን ኖታ እና የረፍት ምልክቶችን አንብቡ?




የኖታ ክፍልፋይ



የዕረፍት ክፍልፋይ






ኖታው ከሙሉ ኖታ ሲያንስ ከግንዱ ጋር ይጻፋል፡፡

ኖታው ከሩብ ኖታ ሲያንስ የባንዲራ ምልክት ይኖራል ወይም በድልድይ ይያያዛል፡፡

## 2.1.2. ቁልፍ (ክሌፍ)

የሙዚቃ ቁልፍ: - ማለት በሙዚቃ መፃፊያ ሰሌዳ ላይ ከኖታም ይሁን ከሌላ ከጊዜ ምልክት ወይም የቅኝት ቁልፍ ቀድሞ የሚጻፍ ቁልፍ ሲሆን ይህም ቁልፍ በሙዚቃ መጻፍያ ሰሌዳ ላይ በባዶ ቦታም ይሁን በመስመር ላይ የሚጻፈውን የኖታ አይነቶቸን ለመለየት ይጠቅማል፡፡

ከየተኛውም የሙዚቃ ምልክቶች ቀድሞ በሙዚቃ መጻፊያ ሰሌዳ ላይ የሚቀመጥ ቁልፍ ነው፡፡ በዚህ ክፍል ላይ ቁልፎችን በሁለት ከፍለን እናያቸዋለን ፡፡ እነሱም ቀጭንና ወፍራም ናቸው፡፡


### 1. ቀጭን ቁልፍ (G ቁልፍ)

ቀጭን ቁልፍ (G ቁልፍ) በሙዚቃ መጻፊያ ሰሌዳ ላይ አምስት ወደ አግድም የተሰመረ መስመር ላይ ይቀመጣል፡፡ ይህ ቁልፍ በሙዚቃ መጻፊያ ሰሌዳ ላይ ሁለተኛ መስመር ጠምዛዛ ምልክት ይቀመጣል፡፡ ጠምዛዛ ምልክት G የሚል ስም ይሰጠዋል፡፡

ቀጭን ቁልፍ የተባለበት ምክንያትም ቀጭን ድምፅ ያለው የሙዚቃ መሳሪያና ቀጭን ድምፅ ያለው መዝሙር በዚህ ቁልፍ ላይ ስለሚጻፍ ቀጭን ቁልፍ ይባላል፡ ፡ በዚህ ቁልፍ ላይ የሚጻፈው የሙዚቃ መሳሪያም መካከለኛ እና ቀጭን ድምፅ ያለው ነው፡፡ መካከለኛ የሚባለው በፒያኖ ስምንት 'C" ዎች መካከል አራተኛ ላይ ያለው 'C" ነው ፡፡



ምስል 7. ቀጭን ቁልፍ



ምስል 8. ቀጭን ቁልፍ በሙዚቃ መጻፊያ ሰሌዳ ላይ ሲቀመጥ

በሙዚቃ መጻፊያ ሰሌዳ ላይ የቁልፍ ምልክት ከተቀመጠ እኚህ ፊደላት በኖታ መልክም ይሁን በፊደል ከተቀመጠ ስማቸው እንደነበረ ይጠራል።


እነሱም:-

- አንደኛ መስመር E
- ሁለተኛ መስመር G
- ሦሥተኛ መስመር B
- አራተኛ መስመር D

አምስተኛ መስመር F ብለን እንጠራለን ይህ ስማቸው በቀጭን ቁልፍ ከተጻፈ ቦታቸውንም ይሁን ስማቸው ሊቀየር አይችልም።

- በአንደኛ ባዶ ቦታ ላይ F
- በሁለተኛ ባዶ ቦታ ላይ A
- በሦስተኛ ባዶ ቦታ ላይ C እና

በአራተኛ ባዶ ቦታ ላይ E እኚህ ፊደላት በባዶ ቦታ ላይ የሚጻፉ ናቸው ።ይህን G መነሻ አድርገን ለሌሎች ፊደላትም ስማቸውን እንሰጣለን ስም ስንሰጥም የፊደል ተራቸውን ተጠብቆ (alphabetical order) ነው።




ምስል 9. ቀጭን ቁልፍ

## መዝሙር ለመዘመር የምንጠቀምበት ዘዴ

በዚህ ክፍል ደረጃ ላይ መዝሙርን ለመዘመር የምንጠቀምንበት ዘዴ አጠቃላይ የአዘማመር ዘዴ ነው፡፡ የአንድን መዝሙር የአዘማመር ዘዴ የምንጠቀመው ግጥማቸውና ዜማቸው በጣም ቀላል እና እኛ የምናውቀውን መዝሙር ከመረጥን በኋላ ካልሆነ መምህሩ ወይም መምህሯ በራሱ/ሷ መዝሙር የሚመርጥ ከሆነ ስንኝ በስንኝ በመክፈል ስለሚዘምሩ ተማሪዎች ትኩረት ሰጥታችሁ ተከታተሉ፡፡የአዘማመር ዘዴዎች በዋናነት በሁለት ክፍለን እናያቸዋለን፡፡ እነሱም አጠቃላይ አዘማመር እና በስንኝ ከፋፍሎ የመዘመር ዘዴ ናቸው፡፡

**በስንኝ ክፍለን የመዘመር ዘዴ፡-** ማለት አንድን መዝሙር በየስንኙ እያከፋፈለን እየተረዳን የምንዘምርንበት ሂደት ነው፡፡ ይህ ዘዴ ለአጠቃላይ አዘማመር የሚንዘጋጅበት የአጠናን ዘዴ ነው፡፡

**አጠቃላይ አዘማመር፡-** ማለት አንድን መዝሙር ግጥሙን ፣ ዜማውን በሚገባ ተረድተን ሳናቋርጥ በስልተ ምት ውስጥ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ መዘመር ነው፡፡

የአዘማመር ቅድመ ተከተል

- የመዝሙሩን ግጥም በደብተራችዉ ላይ ፃፉ
- መዝሙሩን ተማሪዎች ከመዘመራችው በፊት መምህራችዉ ሲዘመሩ በደንብ መስማት አለባችሁ
- ከዛ በኋላ ተማሪዎች በጋራ ዘምሩ
- ተማሪዎችን በቡድን እየተከፋፈላችው ዘምሩ
- እጅ በማውጣት ተማሪዎች በመምርጥ ፊት ወጥተው ዘምሩ

ከታች በሙዚቃ መጻፊያ ሰሌዳ ላይ የተጻፈውን እንመለከት ከታች በሙዚቃ መጻፊያ ሰሌዳ ላይ የተጻፈው መዝሙር አራት ስንኝ ያለው መዝሙር ነው፡፡ እሱንም በስንኝ ክፍለን እናየዋለን፡፡

ወንድሜ ያዕቆብ ወንድሜ ያዕቆብ__________________ስንኝ አንድ

ተኛህ ወይ ተኛህ ወይ_______________________ስንኝ ሁለት

ደወል ተደወለ_____________________________-ስንኝ ሦስት

ተነሳ ተነሳ_________________________________ስንኝ አራት

ተማሪዎች እስኪረዱ ድረስ የመጀመሪያውን ስንኝ ደጋግመን መዘመር ይጠበቅብናል ፤ የቀረውን ስንኝም ልክ እንደዛው ስንኝ በስንኝ እየከፋፈለን መዘመር መቻል አለብን፡፡

በመቀጠልም ሁሉን ስንኝ አንድ ላይ አያይዘን በስልተ ምት ውስጥ ሆነን መዘመር አለብን፡፡ ከዛም በኋላ እጃችሁን እያጨበጨባችሁ መዘመር መቻል አለባችሁ፡፡

ለምሳሌ፡- በሙዚቃ መጻፊያ ሰሌዳ ላይ ቀጭን ቁልፍ አስቀምጠን በዛ ላይ ሙዚቃ እንፅፋለን እንማራለን፡፡

## ወንድሜ ያዕቆብ







### የተግባር ሥራ-13

ከላይ የተቀመጠውን መዝሙር ደጋግማችሁ ዘምሩ?

2. በሙዚቃ መጻፊያ ሰሌዳ ላይ በባዶ ቦታዎች የሚቀመጡትን ፊደላትን ዘርዝሩ?

የተግባር ሥራ -13

## 2. ወፍራም ቁልፍ (F ቁልፍ/ በዝ ክለፍ)

ወፍራም ቁልፍ በሙዚቃ መጻፊያ ሰሌዳ ላይ እንደ ቀጭን ቁልፍ ከሁሉም ሙዚቃዊ ምልክቶች (ከጊዜ ምልክት እና የቅኝት ቁልፎች) ቀድሞ የሚቀመጥ ምልክት ሲሆን


በቀጭን ቁልፍ ላይ የማይፃፍ የሙዚቃ መሳሪያ ወይም መዝሙር በዚህ ቁልፍ ውስጥ ይጻፋል፡፡ በቀጭን ቁልፍ የማይጻፍ ሲባል ወፍራም ድምጽ ያለው የሙዚቃ መሳሪያና ወፍራም ድምጽ ያለው ዘማሪ በወፍራም ቁልፍ ስለሚፃፍ ወፍራም ቁልፍ ይባላል፡፡

ከዚህ ከአምስቱ መስመሮች ውስጥ አራተኛውን መስመር “F” የሚል ስም ስለሚሰጥና በአራተኛ መስመር ላይ ጠማማ ምልክት ተቀምጦ ከአራተኛ መሰመር ከታች በኩል አንድ ነጥብ እና ከአራተኛ መስመር ከላይ በኩል አንድ ነጥብ ባጠቃላይ በሁለት ነጥብ ታጅቦ ይቀመጣል፡፡

በቀጭን ቁልፍ እንዳየነው የሙዚቃ መፃፊያ ሰሌዳ ከታች ወደ ላይ እንደሚቆጠር መዘንጋት የለብንም፡፡



ምስል 10. የወፍራም ቁልፍ ምልክት




ምስል 11.

ምስል 12. የወፍራም ቁልፍ ምልክት ሙዚቃ መፃፊያ ሰሌዳ ላይ ሲቀመጥ

ከላይ በወፍራም ቁልፍ በሙዚቃ መፃፍያ ሰሌዳ ላይ በመስመሩ ላይ የተጻፉት

1. አንደኛ መስመር ላይ G
2. ሁለተኛ መስመር ላይ B
3. ሶሥተኛ መስመር ላይ D
4. አራተኛ መስመር ላይ F እና

5. አምስተኛ መስመር A


በሙዚቃ መጻፊያ ሴለዳ ላይ በባዶ ቦታ የሚጻፉ ፊደላት ከዚህ በታች ይገኛሉ፡፡

1. አንደኛ ባዶ ቦታ ላይ A
2. ሁለተኛ ባዶ ቦታ ላይ C
3. ሶሥተኛ ባዶ ቦታ ላይ E እና አራተኛ ባዶ ቦታ ላይ G

እነዚህ ከላይ ያየናቸው በመስመርም ይሁን በባዶ ቦታ የተጻፉት ስማቸውም ሆነ ቦታቸው ሊቀያየር አይችልም፡፡

ወፍራም ቁልፍ ላይ መሳሪያም ይሁን መዝሙር ከመካከለኛው "C" ወይም (ሚድል) "C" ወደ ታች ያለው ነው፡፡

በታች በስዕሉ ላይ የሚታየው መሳሪያ በአብዛኛው ጊዜ ለመዝሙር የምንጠቀመው የሙዚቃ መሳሪያ ሲሆን ወፍራሙንም ቀጭኑንም አንድ ላይ የያዘ የሙዚቃ መሳርያ ነው፡፡ በአጠቃላይ ቁልፎችን የያዘ ነው፡፡ እነዚህ ቁልፎች ሁለት አይነት መልክ አላቸው ፤ እነሱም 36 ጥቁርና እና 52 ነጭ ቁልፎች ናቸው፡፡




ምስል 6. የፒያኖ ምስል


**የማነቃቂያ ጥያቄ -2**

1. ወፍራም ቁልፍ ማለት ምን ማለት እንደሆነ አብራሩ?
2. ድምጽ ማለት ምን ማለት እንደሆነ ለመምህራችው አብራሩ?

## ድምፅ

ድምፅ ምን እንደሆነ ምዕራፍ አንድ ላይ አይተነዋል በዚህ ምዕራፍ ላይ ድምፅን ለሶስት ከፍለን እናየዋለን፡፡ እነሱም፡- ወፍራም ድምፅ ፣ መካከለኛ እና ቀጭን ድምጽ ናቸው፡፡

**ወፍራም ድምፅ** ፡-ማለት በሙዚቃ መሳሪያ ተጫዋችም ይሁን በዘማሪ አውርዶ ወይም አውፍሮ ስጨዋት ወይም ሲዘምር ለጆሯችን ወፍሮ ይሰማል ማለት ሲሆን ይህም በሙዚቃ ወፍራም ድምጽ ይባላል፡፡



ምስል 7. ዲንኬ

1. **መካከለኛ ድምጽ፡-** ድምጽ ማለት ከወፍራም ድምጽ ቀጠን ወይም ከቀጭን ወጣ የሚል የድምጽ ክፍል ነው፡፡

**ለምሳሌ፡-** ዋሽንት

2. **ቀጭን ድምጽ፡-** ይህ ድምፅ የወፍራም ተቃራኒ ሆኖ ሲገኝ በሙዚቃ መሣርያ ተጫዋችም ይሁን በዘማሪ ቀጥኖ ወይም ወጥተው ለጆሮአችን የሚሰማ ከሆነ ቀጭን ድምፅ እንለዋለን፡፡

**ለምሳሌ፡-** ጡሩምባ እና ፊላ

## የተግባር ሥራ-14

ሀ. የወፍራም እና የቀጭን ድምጽ ልዩነት ግለጹ?

ለ. ከቡድናችሁ መሀል ቀጭን ድምጽ ያለው ተማሪ ለዩ?

## 2.2. ኪነ-ንድፍ ለኪነ-ቅብ እና ለህትመት

### መግቢያ

ተማሪዎች የእይታ ጥበብን ስራን ለመስራት ከሁሉ አስቀድሞ ኪነ-ንድፍን በሚገባ መረዳት፣ ማወቅ እና መገንዘብ ይጠበቅባችዋል፡፡ ያለ ኪነ-ንድፍ የተኛውም ዓይነት ለህትመት እና ቀለምቅብ ስራ መስራት ስለማይቻል ተማሪዎች ኪነ ንድፍን በሚገባ መወቅ አለባቸሁ፡፡

### አጥጋቢ የችሎታ ደረጃ

- ኪነ-ንድፍ አይነቶችን እና ሥነ-ዘዴዎችን ይገልፃሉ፡፡
- ኪነ-ንድፍ አይነቶችን እና ሥነ-ዘዴዎችን በመስራት ያሳያሉ፡፡
- ኪነ-ንድፍን ለኪነቅብ እና ለሌሎች የእይታ ጥበባት በመሰረት ያዘጋጃሉ፡፡

### የማነቃቂያ ጥያቄ -3

1. የኪነ-ንድፍ አሰራር ዘዴዎች ምን ምን እንደሆኑ በቡድን ተወያዩ?
2. የኪነ-ንድፍ ዓይነቶች ዘርዝሩ?


ኪነ-ንድፍ፡ - ለንድፍ ሥራ ብቻ ሳይሆን ለሌሎች ዕይታዊ ጥበባት ሁሉ የጀርባ አጥንትና ዋና የባሕርያት ጉልበት ያለው መገለጫ ነው። ልምምዶች በጥረትና በትጋት እንዲሁም በጥሞና ክትትል ከተደረገበት የመስመር ባሕርይ ጥናት ተጨማሪ የሥነ-ልቦናዊ ዕውቀት ትርፍ እንዳለው ይታመናል።

### 2.2.1. የንድፍ ምንነትና መሠረታዊ ባህሪያት

ንድፍ፡- ማለት መስመሮችን በዋነኛነት በመጠቀም የሚሠራ የፈጠራ ውጤት ወይም ምስል ነው፡፡ የንድፍ ጥበብ ከሌሎቹ የሥነ-ጥበብ ዘርፎች የበለጠ አንድን ሃሳብ፣ ስሜት ወይም ቁስ በፍጥነት የምናስቀምጥበት ወይም የምናንፀባርቅበት የፈጠራ ሂደት ውጤት ነው፡፡

የንድፍ ክህሎት ለሁሉም የሥነ-ጥበብ የፈጠራ ሥራዎች መሠረታዊ ነው፡፡ አንድ ሰው የንድፍ ጥበብ ክህሎቱ እየጨመረ በሄደ ቁጥር አካባቢውን በበለጠ የፈጠራና የግንዛቤ ብቃት መመልከትና መረዳት እንዲችል ያደርገዋል፡፡ የሰው ልጅ በሙሉ በተፈጥሮ ከሚያገኛቸው ክህሎቶች አንዱ ንድፍ የመንደፍ ዝንባሌና ፍላጎት ነው፡፡

ሰው ሁሉ ስለንድፍ ምንነት ከማወቁ በፊት አንድን ነገር ተጠቅሞ የመጫር፣ የማስመርና የመንደፍ እንቅስቃሴዎችን ያደርጋል:: በመሆኑም የንድፍ ፅንሠ ሃሳብና እንቅስቃሴ የጀመረው የሰው ልጅ በምድር ላይ መኖር ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ ነው ማለት ይቻላል:: በታሪክ ከቀደሙና ለዘመናት ከኖሩ የሰው ልጅ የንድፍ ውጤቶች ውስጥ የሰው ልጅ በዋሻ ግድግዳዎች ላይ የሰሯቸው የንድፍ ውጤቶች ናቸው:: የንድፍ ዝንባሌና ፍላጎት ምንም እንኳን ለሁሉም ሰው ከተፈጥሮ የተቸረ ቢሆንም ማንኛውም ሰው የንድፍ ክህሎቱን በትምህርት በማዳበር የበለጠ ገላጭ የሆነ የንድፍ ጥበብ መስራት ይችላል:: የንድፍ ጥበብ ችሎታ ነገሮችን በጥልቀት ማየትን የሚጠይቅ ከመሆኑም በላይ በብዛትና በተከታታይ የሚደረጉ ተግባራዊ እንስቃሴዎችን ይጠይቃል::



ምስል 8. የሰው ፊት


## 2.2.2. . የኪነ-ንድፍ አሰራር ዘዴዎች


ኪነ-ንድፍ ማንኛውም ነገር ለመስራት ፣ የመጀመሪያው እርምጃ ቅርጻችውን በማስተዋል ማየት ነው:: በመቀጠል ከቅርጻቸው በመመልከት መዋቅራዊ መስመሮች በማስቀመጥ በጣም አስፈላጊ ዝርዝሮች ተጨምረው ይስተካከላሉ ፣ በመጨረሻም ጥቃቅን ዝርዝሮች እስከ መጨረሻው ይሰራሉ:: እነዚህን የተለያዩ የንድፍ ደረጃዎች በሚፈጽሙበት ጊዜ የመስመሮች በትክክለኛ ቦታዎች መቀመጥ ከተረጋገጠ በኃላ ማጉላት አስፈላጊ ነው::

ጥሩ የኪነ ንድፍ ስራ በራሱ ሊታይ ወይም ለታላቅ የኪነቅብ ስራ መሠረት ሊሆን ይችላል፡፡ በዋናነት ብዙ ዓይነት የእርሳስ አቀባብ ዘዴዎች አሉ ፤ ከነዚህ መካከል

በዚህ የትምህርት ክፍል የምናጠናው አራት ዓይነት ዘዴዎችን ነው፡፡


1. ቅርጽን የተከተለ የመስመር አቀባብ ዘዴ
2. የተጠላለፈ መስመር አቀባብ ዘዴ
3. በነጥብ አቀባብ ዘዴ
4. በማሸት ዘዴ





ምስል 9. የኪነ-ንድፍ አሰራር ዘዴዎች

ቅርጽን የተከተለ የመስመር አቀባብ ዘዴ





ምስል 10. የኪነንድፍ አሰራር ዘዴዎች በንጣት እና በጥቁረት

## 1.ቅርጽን የተከተለ የመስመር አቀባብ ዘዴ

ይህ ዘዴ በአግድም ፣ በቁም ወይም በሰያፍ እርስ በእርስ ቅርብ የሆኑ የመስመሮች አቀማመጥ ነው።



ምስል 11. ምስል 15 ቅርጽን የተከተለ የመስመር አቀባብ ዘዴ




ምስል 12. ቅርጽን የተከተለ የመስመር አቀባብ ዘዴ

የተግባር ሥራ-15


1. ማሪዎች በቤታቸው የሚገኙ ቁሳቁሶችን ቅርጽን የተከተለ የመስመር አቀባብ ዘዴ በመጠቀም ሰርታችሁ አሳዩ?

## 2. የተጠላለፈ መስመር አቀባብ ዘዴ

ይህ ዘዴ መስመሮችን በማጠላለፍ በመደራረብ የንድፍ ስራን የመስራት ሂደት ነው፡፡



ምስል 13. በተጠላለፈ መስመር አቀባብ ዘዴ የተሰራ የቁሳቁስ ንድፍ



ምስል 14. በተጠላለፈ መስመር አቀባብ ዘዴ የመልካዓምድር ንድፍ

የተግባር ሥራ-16

ተማሪዎች ባከባቢያቸው የሚገኙ መልከዓምድርን የተጠላለፈ መስመር አቀባብ ዘዴ በመጠቀም ሰርታችሁ አሳዩ?

## 2. በነጥብ አቀባብ ዘዴ

ይህ ዘዴ ነጥቦችን በመጠቀም ነጥቦችን በማቀራረብ እና በማራራቅ ጥቁረትና ንጣት በመፍጠር የሚሰራ ሥነ-ዘዴ ነው።



ምስል 15. በነጥብ አቀባብ ዘዴ የድመት ምስል ንድፍ



ምስል 16. በነጥብ አቀባብ ዘዴ የቁሳቁስ ንድፍ

### የተግባር ሥራ-17

1. ተማሪዎች ባከባቢያቸው የሚገኙ የቤት እንስሳትን በነጥብ አቀባብ ዘዴ በመጠቀም ሰርታችሁ አሳዩ?

## 3. የማሸት ዘዴ

ይህ ዘዴ የንድፍ መሳሪያዎችንን የምንስለውን ስዕል ካቀለምን በኋላ በማሸት እና በማዋሀድ የሚሰራ ሥነ-ዘዴ ነው።



ምስል 17. በማሸት ዘዴ የተሰራ የፊት ንድፍ

## የተግባር ሥራ-18

1. ማሪዎች በክፍላችሁ ውስጥ የሚገኙ ጓደኞችሁን በማሸት ዘዴ በመጠቀም ሰርታችሁ አሳዩ?

## የኪነንድፍ አይነቶች

### 1. የቁሳቁስ ንድፍ

የቁሳቁስ ንድፍ (ስቲሊፍ ድሮዊንግ) የምንለው የማይነቃነቅ ሕይወት አልባ አብዛኛውን ጊዜ ግዑዝ የሆኑ ቁሳቁሶችን ስንሰራ፣ ለምሳሌ ተፈጥሯዊ (ምግብ ፣ አበባ ፣ የሞቱ እንስሳት ፣ ዕፅዋት ፣ አለቶች ወይም ዛጎሎች) ወይም ሰው ሰራሽ (የቤት ውስጥ ቁሳቁሶች፣ መጻሕፍት ፣ የአበባ ማስቀመጫዎች ፣ ጌጣጌጦች ፣ ሳንቲሞች ፣ ቧንቧዎች እና የመሳሰሉት) ፡፡



ምስል 18. የፍራፍሬዎች የሚያሳይ የቁሳቁሶችን ንድፍ



ምስል 19. ቁሳቁስን በንድፍ

የተግባር ሥራ-19

1. ተማሪዎች በአካባቢያቸው የሚገኙ ቁሳቁሶችን ፣ አበባ ወይም ዕፅዋት በጥሩ ሁኔታ የተደረደሩትን በመረጣችሁት የንድፍ ስነዘዴ በመጠቀም ሰርታችሁ አሳዩ?

2. የሰው ገፅ ምስል ንድፍ

የሰው ፊቱ ምስል ንድፍ የአንድ ሰው ሥዕል ፣ ፎቶግራፍ ፣ ሐውልት ወይም ሌላ

ጥበባዊ ውክልና ሲሆን በዋነኝነት ፊቱ እና ትከሻው የሚገለጡበት ነው። ዓላማው የሰውን አምሳያ ፣ ስብዕና እና ስሜቱን ማሳየት ነው።



ምስል 20. የሰው ፊት ምስል ንድፍ



ምስል 21. የሰው ፊት ምስል ንድፍ

## የሰው ፊት ገፅ ላይ የሚገኙ አካላትን በተናጠል ማጥናት

ተማሪዎች ቀደም ብለው በነበሩት ክፍለ ጊዜያት የተማሯቸውን መሠረታዊ የንድፍ አሠራር ግብዓቶች በተግባር የሚሞክሩበትና በተለይም በሰው የፊት ገፅታ ላይ የሚገኙ


የሰውነት አካላትን በተናጠል የሚያጠኑበት ይሆናል፡፡

በመሆኑም በዚህኛው ክፍለ ጊዜያት ዓይን፤ አፍንጫ፣ከንፈርና ጆሮ ከተለያዩ አቅጣጫዎች ሲታዩ ምን እንደሚመስሉና እንዴት በንድፍ ማስቀመጥ እንዳለባቸው እንዲለማመዱ መምህሩ ለምሳሌነት የሚሆኑ የዓይን ንድፎችን

በጥቁር ሰሌዳ ላይ በማስፈር ተማሪዎቹ እያዩ እንዲሰሩ ማበረታታት ይኖርባቸዋል፡፡

## ዓይን፡


የዓይንን አቀማመጥ የሚያሳይ የንድፍ አሰራር



ምስል 26 የዓይንን አቀማመጥ የሚያሳይ የንድፍ አሰራር

## አፍንጫ፡


የአፍንጫን አቀማመጥ የሚያሳይ የንድፍ አሰራር



ምስል 22. የአፍንጫን አቀማመጥ የሚያሳይ የንድፍ አሰራር

## ከንፈር፡


የከንፈርን አቀማመጥ የሚያሳይ የንድፍ አሰራር



ምስል 23. የከንፈርን አቀማመጥ የሚያሳይ የንድፍ አሰራር

## ጆሮ፡


የጆሮን አቀማመጥ የሚያሳይ የንድፍ አሰራር




ምስል 24. የጆሮን አቀማመጥ የሚያሳይ የንድፍ አሰራር

## የፊት ምስል


ሙሉ የፊት ገፅታ አቀማመጥና ልኬት




ምስል 25. የፊት ገፅታ አነዳደፍ ሂደት



ምስል 26.  የፊት ገፅታ አነዳደፍ ሂደት



ምስል 27. የተለያየ እይታ ያላቸው የፊት ገፅታ አነዳደፍ




ምስል 28. የተለያየ እይታ ያላቸው የፊት ገፅታ አነዳደፍ

## የተግባር ሥራ-20

1. ተማሪዎች ዓይን፤ አፍንጫ፣ከንፈርና ጆሮ ከተለያዩ አቅጣጫዎች በንድፍ ሰርታችሁ አሳዩ?
2. ተማሪዎች በአካባቢያቸው የሚገኙ ተጽዕኖ ፈጣሪ ወይም ታዋቂ ግለሰቦችን በመረጣችሁት የንድፍ ሥነ-ዘዴ በመጠቀም ሰርታችሁ አሳዩ?
3. ተማሪዎች የሰው ፊት ምስል በመረጣችሁት የንድፍ ሥነ-ዘዴ በመጠቀም ሰርታችሁ አሳዩ?

## 1. የሙሉ ምስል ንድፍ


የሰው ምስል ንድፍ (ፍገር ድሮዊንግ) በማንኛውም የእይታ ጥበባት ውስጥ ዋናው የጥበብ ሥራ አለባበስም ሆነ እርቃን ቢሆን የሰው ምስል ነው:: የሰው ምስል ንድፍ የአንድ ግለሰብ ወይም ቡድን ተግባር ላይ ያተኮረ የእይታ ጥበባት ነው:: የሰው ምስል ንድፍ ብዙውን ጊዜ ሊኖራቸው የሚችል ታሪካዊ ፣ አፈ ታሪክ ፣ ምሳሌያዊ ወይም ምናባዊ ሥዕሎች ናቸው::



ምስል 29. ሙሉ የሰው ምስል ንድፍ

## 2. የሙሉ የሰው ምስል ንድፍ አሰራር


የተመጣጠነ ሙሉ የሰው ምስል ንድፍን ለመስራት ፊቱን እንደ መለኪያ እየተጠቀምን ሌላውን የሰውነቱን ክፍሎች በታዎች ማግኘት እንችላለን፡፡ ይህ ልኬት እንደየ እድሜው ይለያያል፡፡




ምስል 30. ሙሉ የሰው ምስል ንድፍ ምጣኔ አሰራር

## ሙሉ የሰው ምስል በመስመር ንድፍ

የሙሉ የሰው ምስል በመስመር ንድፍ የሚሰራው መስመሮችን በመጠቀም የሰውን እንቅስቃሴ በቀላሉ ለመግለፅ የሚያስችል ነው፡፡



ምስል 31. ሙሉ የሰው ምስል በመስመር ንድፍ





ምስል 32. ሙሉ የሰው ምስል በመስመር ንድፍ

### የተግባር ሥራ-21

1. ተማሪዎች ከቤተሰብ አባላት መካከል የሙሉ ምስል በመረጣችሁት የንድፍ ሥነ-ዘዴ በመጠቀም ሰርታችሁ አሳዩ?
2. ተማሪዎች በመስመር ንድፍ በመጠቀም የምትወዱት ጨዋታ ስትጫወቱ የሚያሳይ ስዕል ሰርታችሁ አሳዩ?

## የሙሉ እንስሳት ምስል ንድፍ



ምስል 33. የእንስሳት ንድፍ

**የተግባር ሥራ-22**


1. የሙሉ እንስሳት ምስል ንድፍ ሰርተው በማሳየት ተማሪዎች በመረጡት የንድፍ ሥነ-ዘዴ በመጠቀም ስሩ?

## 3. የመልክዓ ምድር ንድፍ

የመልክዓ ምድር ንድፍ ፣ ተፈጥሯዊ መልክዓ ምድሮች እንደ ተራሮች ፣ ሸለቆዎች ፣ ዛፎች ፣ ወንዞች እና ደኖች ፣ በተለይም ዋናው ርዕሰ -ጉዳይ ሰፊ እይታ ባለበት መልክዓ ምድር ነገሮች በተዋሃደ መልኩ የሚሰራ የንድፍ ስራ ነው::



ምስል 34. የመልካምድር ንድፍ



ምስል 35. የዛፍ ንድፍ

## የተግባር ሥራ-23

1. ተማሪዎችን ከላይ የተቀመጡትን እና ባአከባቢያቸው የሚገኙ የዛፍ አይነቶችን በንድፍ ተለማመዱ?
2. ተማሪዎች ባአከባቢያችሁ ከሚገኙ ተፈጥሯዊ መልክዓ ምድሮች እንደ ተራሮች ፣ ወንዞች ፣ ዛፎች በቡድን በቡድን በመሆን ተለቅ ባለ ወረቀት ላይ በንድፍ ሰርታችሁ አሳዩ?

## 2.2.3. ንድፍ ለኪነ ቅብ እና ህትመት ስራ

### 1. ንድፍ ለኪነ ቅብ

ንድፍን በመጀመሪያ በእርሳስም ሆነ በከሰል ከነደፍን በኋላ የተለያዩ ቀለማትን በመቀባት በቀለም ቅብ የውበት የጥልቀት ባህሪን በቀለማት ንብረት የምናፀባርቅበት ቀለም ቅብ ይባላል፡፡










ምስል 36. የወፍን ንድፍን ቀለም ቅብ






ምስል 37. መልከዓ ምድር

የተግባር ሥራ-24

1. ተማሪዎች ባከባቢያችሁ ከሚገኙ እጸዋፋትን ቅድመ-ንድፍን ለቀለም ቅብ በማዘጋጀት ሰርታችሁ አሳዩ?
2. ተማሪዎች የሰራችሁትን ቅድመ-ንድፍ በቀለም ቅብ ሰርታችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ?

## 2. ንድፍን ህትመት ስራ

ንድፍን በመጀመሪያ በእርሳስም ወረቀት ፣ በድንች ወይም በእንጨት ላይ በመንደፍ ቀለም በመጠቀም በተለያዩ ነገሮች ላይ በማተም የሚሰራ የእይታ ጥበብ ነው፡፡




ምስል 38. ንድፍን ለህትመት ስራ

የተግባር ሥራ-25

1. ተማሪዎች ባአከባቢያችሁ ከሚገኙ የእርሻ መሳሪያዎችን በቅድመ-ንድፍን ለህትመት በማዘጋጀት ሰርታችሁ አሳዩ?
2. ተማሪዎች የሰራችሁትን የእርሻ መሳሪያዎችን ቅድመ-ንድፍ በህትመት ሰርታችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ?

## 2.3. በትያትር ፣ በፎቶ እና በተንቀሳቃሽ ምስል ሃሳብን መግለጽ

### መግቢያ

ትያትርን ፣ በተንቀሳቃሽ ምስል እና በፎቶ በቡዙ ነገር መግለጽ ስለምችሉ ተማሪዎች በዚህ ትምህርት ክፍል ላይ ሀሳባቸውን እንዴት መግለጽ እዳለባቸው በተገቡው መማር ይጠበቅባቸዋል፡፡ በትያትር ሊገለፅ የማይቻል ሀሳብ ቀለም ማለት እንችላለን፡፡ የማህበረሰብን እና የግለሰቢን ሀዘን ፣ ደስታ ፣ ችግር ውጣውረድ እና የተለያዩ ነገርን በተንቀስቃሽ ምስልና በፎቶ ሀሳብን መግለጽ እንደሚቻል በቂ ግንዛቤ እና እውቀት መኖር ያስፈልጋል፡፡

### አጥጋብ የችሎታ ደረጃ

- ትያትርን በተንቀሳቃሽ ምስል ይገልፃሉ
- በፎቶ ምስል ፈጠራዊ ሃሳብን ይዘረዝራሉ
- ትውንና በፎቶ ምስል በመጠቀም ፈጠራዊ አገላለጽ ያስረዳሉ

### የማነቃቂያ ጥያቄ -3

1. የፎቶ ግራፍን ጥቅም አብራሩ?

## ቴአትር

ቴአትር የሰው ልጆችን የእለት ተእለት ተግባራት ለመድረክ በተንቀስቃሽ ምስል እና በፎቶ መጠን መልኩ በማዘጋጀት ለማስተማር ለማዝናናት እና የተለያዩ ሃሳቦችን ለመግለፅ የምንጠቀምበት የጥበብ ዓይነት ነው፡፡



ምስል 39. ታሪካዊ ሀሳብን የሚያሳይ ትያትር

## ፎቶግራፍ

ፎቶግራፍ ማለት ሰዎች ለዕይታ በምያምር ስፍራ ለመዝነኛና ለማስታስታዎሻ ለማስቀመጥ የምነሱበት ፎቶግራፍ እና በተጨማሪ ባህልን አለባበስን ፣ ውዝዋዜን ፣ ብርቅዬ እንስሳትንና የተለያዩ የማስታዎሻ ጌጣጌጦችን በፎቶ መልክ ስያስቀምጥ ፎቶግራፍ እንላለን።

ለምሳሌ፡- የሜዳ አህያ ፣ የቤተሰብ ፎቶ፣የሰርግ ፎቶ ፣ የሀዘንና የመሳሰሉትን ያካትታል።



ምስል 40. የሀገራችንን መልካምድርን እና የእህል አጨዳ ሃሳብን የሚያሳይ ፎቶ

## ፊልም

ፊልም ወይም ተንቀሳቃሽ ምስል ተብሎ የሚጠራው፣ በፊልም ላይ ያሉ ተከታታይ ፎቶግራፎች በስክሪኑ ላይ በፍጥነት በተከታታይ ብርሃንን ተጠቅመዋል::

ፊልም ድራማን ለማስተላለፍ እና በተለይም ስሜትን ለማነሳሳት በሚያስደንቅ ሁኔታ ውጤታማ ሚዲያ ነው:: የተንቀሳቃሽ ምስሎች ጥበብ እጅግ ውስብስብ ነው፣ ከሞላ ጎደል ከሌሎች ጥበቦች እና ስፍር ቁጥር የሌላቸው ቴክኒካል ችሎታዎች (ለምሳሌ በድምጽ ቀረጻ፣ ፎቶግራፍ እና ኦፕቲክስ) አስተዋጽዖን ይፈልጋል:: በ 19 ኛው ክፍለ ዘመን መገባደጃ ላይ ብቅ ማለት ይህ አዲስ የጥበብ ቅርጽ በ 20 ኛው ክፍለ ዘመን እና ከዚያም በኋላ ከነበሩት በጣም ታዋቂ እና ተደማጭነት ሚዲያዎች አንዱ ሆነ::

## የፊልም ዓይነቶች

ዘጋቢ ፊልሞች፣ የሙከራዊ ፊልሞች፣ አኒሜሽን ፊልሞ፣ የጣርነት ፊልሞች እና አዝናኛ፣ አሰቃቂ እና ሙዚቃዊ እና ሌሎችም የመሳሰሉ ልብ ወለድ ዘውጎች ሊመደቡ ይችላሉ::



ምስል 41. የእርቅ ሥነ-ሥራትን ለተንቀሳቃሽ ምስል ሲቀረፅ የሚያሣይ

### የተግባር ሥራ -26

1. በአከባቢያችሁ ከሚታዩት በርካታ እንቅፅስቃሴዎች እና ሀሳቦች መከከል አንዱን መርጣችሁ በሚያስተምር እና በሚያዝናና መልኩ በአጭር ትያትር በቡድን በቡድን ሆናችሁ አዘጋጅታችሁ አቅርቡ?

## 2.4. የውዝዋዜ አላባውያን

ውዝዋዜ ከትውን ጥበባት አንዱ። ውዝዋዜ ፣ ትወና ፣ ሙዚቃ የማይለያዩ ተመጋጋቢ የጥበብ ዘርፎች ናቸው። ውዝዋዜ የስሜት ፣ ግፊት እና ክህሎት ነው። ውዝዋዜ ሀሳቦቻችንን፣ ስሜቶቻችንን እና ልማዶቻችንን ለማስተላለፍ እንቅስቃሴን የሚጠቀም የጥበብ አይነት ነው።

የውዝዋዜ አላባውያን የምንላቸው ማንኛውንም ነገር ለመስራት የሚያስፈልጉ ግብአቶች እንዳሉት ሁሉ የውዝዋዜ ጥበብ የሚያስብለው አላባውያን አሉት። ዳንስ በሚከተሉት አምስት ክፍሎች ሊከፈል ይችላል።

1. አካል
2. ድርጊት
3. ቦታ
4. ጊዜ
5. ጉልበት

### 1. አካል፡ ማነው የሚወዛወዘው? ተወዛዋዥ!

የሰው አካል በውዝዋዜ ሲመለከቱ ሌሎች የሚያዩት ነው። አንድ ተወዛዋዥ በሚንቀሳቀስበት ጊዜ መላውን ሰውነት ሊጠቀም ወይም የነጠላ የአካል ክፍሎችን ማጉላት ይችላል።

### 1. ድርጊት፡ ተወዛዋዥ ምን ያደርጋል? ይንቀሳቀሳል!

ድርጊት በውዝዋዜ ድርጊት ውስጥ የሚሳተፍ ማንኛውም የሰው እንቅስቃሴ ነው። ተወዛዋዥ ምን ያደርጋሉ? እነሱ ይንቀሳቀሳሉ - ይህ የሚያከናውኑት ተግባር ነው። እርምጃ እንደ የፊት መግለጫዎች ወይም የእጅ ምልክቶች ያሉ ትናንሽ እንቅስቃሴዎችን እንዲሁም እንደ ማንሳት፣ መሽከም ወይም ከባልደረባ ጋር ወይም በቡድን የተደረጉ ትላልቅ እንቅስቃሴዎችን ያጠቃልላል። “እርምጃ” በእንቅስቃሴዎች መካከል እንደ ቆመ ወይም ጸጥታ እንደ ተከናወነ እንቅስቃሴ ይቆጠራል።

### 1. ቦታ፡ ተወዛዋዥ የት ይንቀሳቀሳል? ቦታ ላይ!

ቦታ የውዝዋዜ ድርጊት የት እንደሚካሄድ ነው. ዳንስ ማለቂያ በሌለው በተለያዩ መንገዶች በማንኛው ቦታ ላይ ውስጥ ይንቀሳቀሳል።

## 1. ጊዜ፡- ሰውነት ከጊዜ ጋር በተያያዘ እንዴት ይንቀሳቀሳል?

ባለሙያዎች በጊዜ ሂደት ላይ ውሳኔ ማድረግ አለባቸው. እንቅስቃሴያቸው ፈጣን ነው ወይስ እረጋያለ? በስራው ወቅት የተወሰኑ እርምጃዎች በተለያየ ፍጥነት ይደጋገማሉ? ከሆነ ለምን? ጊዜን በሚከተሉት መንገዶች ማሰብ እንችላለን:: የእጆች እና በእግሮች ላይ የመርገጥ ተግባር ተመልካቾች የሚሰሙትን ውስብስብ ሪትም ይፈጥራል:: ውዝዋዜ በጊዜ የተገደፈ ነው:: ጊዜ የውዝዋዜ ጥለቶችን ስናገጣትማቸው ስንት ጊዜ እንደምያደጋግም ፈጥነቱንና ዝግታውን መለየትና ማወቅ ያስፈልጋል::

## 1. ጉልበት፡ እንዴት? ተወዛዋዥ በቦታ እና በጊዜ በኃይል ይንቀሳቀሳል!

ስለዚህ አሁን በቦታ እና በጊዜ ውስጥ የሚንቀሳቀሱ አካላት አሉን:: በቂ አይደለም? በትክክል አይደለም:: አምስተኛው እና የመጨረሻው የውዝዋዜ አካል - ጉልበት ያስፈልገናል.

ጉልበት ተወዛዋዥች እንዴት እንደሚንቀሳቀሱ ለመለየት ይረዳናል. ምን ዓይነት ጥረት ይጠቀማሉ? ምናልባትም እንቅስቃሴዎቻቸው ትክክል እና ጠንካራ ናቸው, ወይም ምናልባት ቀላል እና ነጻ ሊሆኑ ይችላሉ. ጉልበት የእንቅስቃሴውን ጥራት ይወክላል-ኃይሉን እና ውበቱን:: ጉልበት የውዝዋዜን ውበት የሚያመጣ ወሳኝ የጥበብ ኪንውን ነው:: የፈጠርናቸው ጥለቶችን ስናገጣጥም ጊዜን መሰረት አድረገን ጉልበትን በመጨመር ይራሰል::

**የተግባር ሥራ-27**

1. አከባበቢያቸው ላይ ከሚገኙ ባህላዊ ውዝዋዜ መርጣችው በቡድን በመሆን የውዝዋዜ አላባዊያን መሰረት አድርጋችሁ ተለማመዱ?

**ማጠቃለያ**

ስልተምት ማለት የጊዜ ቆይታ ሲሆን በአንድ በተወሰነ የጊዜ ቆይታ መካከል የሚከናወን የድምፅ መርዘምና ማጠር እንዲሁም ዝምታ የጊዜ ርዝማኔ ሆኖ በጣም አጭር ፣ መካከለኛ ፣ በጣም ፈጣንና የተለያዩ መረጃዎችን (የዝላይ፣የፈረስ ግልብያና የተለያዩ ምቶችን) በሙዚቃ ምልክቶች በመተካት የሚያገለግሉ ሲሆን ወፍራም እና ቀጭን ቁልፍ ተማሪዎች የሙዚቃ መሳውያ አገልግሎትን እንዲረዱ እና በሰው ድምፅ ሆነ በሙዚቃ መሣሪያ ላይ ወፍራምና ቀጭን ድምፅን ለይቶ በመረዳት እውቀታቸውን እንዲያዳብሩ ማስተማር ያስፈልጋል።

ህትመት ማለት በምስል ፣ በቅርጻቅርጽ ወይም በቀጥታ ቀለም የማተም ዘዴ ነው። በሌላ በኩል በቀለም ነክሮ ወይም ቀብቶ በተለያዩ ድዛይኖች ፈጥሮ መስራት ሲሆን በድንች ፣ በጎማ ፣ በእንጨትና በወረቀት ላይ ድዛይን ነድፎ በመቅረፅና ቀለም በመጠቀም በተለያዩ ነገሮች ላይ ማተምን ያጠቃልላል።

## የክለሳ ጥያቄዎች

### ሀ) የሚከተሉትን ጥያቄዎችን እዉነት ወይም ሐሰት ብላችው መልሱ?

1. በሙዚቃ መፃፊያ ሰሌዳ ለይ አራት ወደ ጎን የተሰመሩ መስመሮችና አምስት ባዶ ቦታዎች አሉ።
2. ሙዚቃና የኪነ ጥበብ የአንድን አከባቢ ባህል ልገልጹ ይችላሉ።
3. ህትመት ማለት በምስል እና በቅርፅ ቀጥታ ቀለም ማተም ነው።
4. ወፍራም ድምፅ ያለው የሙዚቃ መሳሪያና ቀጭን ድምፅ ያለው መዝሙር በቀጭን ቁልፍ ላይ ይፃፋል።
5. በትያትር የማይገለጹ የተወሳሰቡ ሀሳቦች አሉ።

### ለ) አዛምዱ

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. የቁሳቁስ ንድፍ | ሀ. ፍትና ትክሻ የሚሳልበት |
| 2. የመልካዓ ምድር ንድፍ | ለ. የሞቱ እንስሳት የሚሳሉበት |
| 3. የሰው ገጽ | ሐ. ሰውን ከነ-ሙሉ አካል |
| 4. የሙሉ ምስል ንድፍ | መ. ወንዞችና ደኖች |

## ሐ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።

1. በሙዚቃ መሳሪያ ላይ ወፍራምና ቀጭን ቁልፍ ልዩነታቸውን ፃፍ?
2. ህትመት ማለት ምን ማለት ነው?
3. በአከባቢያችሁ ከሚገኙ ባህላዊ ቅርስ መካከል ሁለቱን በስዕል አሳዩ?
4. ተማሪዎች በአከባቢያችው ከሚገኙ ቀጭን ድምፅ ያላቸው የሙዚቃ መሳሪያ አብራሩ?
5. ታርካዊ እና ባህላዊ ትያትሮችን በምን ይገለጣሉ?

# ምዕራፍ ሦስት

## 3. የእይታና የትወና ጥበብ ታሪካዊና ባህላዊ አውድ

### መግቢያ

ተማሪዎች በቀድሞ የትምህርት ምዕራፍ ውስጥ ፈጠራዊ አገላለፅ ተምራችዋል፡፡ በዚህ ምዕራፍ የሥነ-ጥበባትን ታሪካዊ እና ባህላዊ አውድ የሚመለከት ነው፡፡ በዚህ ክፍል በምዕራፍ አንድ እና ሁለት ያገኙትን ሃሳባዊ እና ተግባራዊ እውቀት ከታሪክ እና ባህል አውድ አንጻር በማየት የአካባቢያቸውን እና የሃገራቸውን ባህል እና ታሪክ የሚገልጹበት ነው፡፡

በሀገራችን ሆነ በክልላችን ውስጥ የሚገኙ የትወናን እና የእይታ ጥበብ አገለግሎታቸውን የምንማርበትና የምንለይበት ነው፡፡ በአከባብያችን ያለው ባህልንና ቅርስን በትውን እና በእይታ ጥበብ የተለያዩ አከባቢያችን በሚገኙ ነገሮች እንዴት መግለጥ እንዳለብን የምንረዳበትና ግንዛቤን የምናዳብርበት ሆኖ ቀርቧል፡፡

የትውንና የእይታ ጥበብ የአከባብያችን ባህልና ታሪክን የሚያንፀባርቅ ሲሆን የትውንና የእይታ ጥበባት አገለግሎታቸውም በሚገባ ተረድተን የምንጠቀምበት ዘዴዎች በያንዳዱ ምሳሌዎች የተካተቱ ሲሆኑ እንደየ አከባብያችን ሁኔታ ልንጠቀም እንችላለን ፡፡

ታሪክ ፣ ባህል እና ቅርስ የአንድ ህዝብ ወይም ማህበረሰብ የዕድገት ፣ የስልጣኔ ፣ የአኗኗር ዘይቤ ደረጃ የሚያሳይ እና መገለጫዎች ናቸው ፡፡ ይህም የአንድ ሀገር ህዝብ ወይም ማህበረሰብ የአኗኗር ፣ አለባበስ ፣ አመጋገብ ፣ የደስታ የሐዘን መገለጫ ባህላዊ እሴቶች ናቸው፡፡

በመሆኑም የህብረተሰቡን ታሪክ፣ ባህል እና ቅርስ መንከባከብ እና መጠበቅ ያስፈልጋል፡፡

በመዝሙሮች፣ በእይታ ጥበባት በትያትር ጥበባት፣በተንቀሳቃሽ ምስል እና በፎቶ አማካኝነት የአከባቢን የኪነ -ጥበብ ታሪኮችን ይገልፃሉ፡፡

አጥጋቢ የችሎታ ደረጃ

- በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉ ምስላዎችን እና ምልክቶችን ይዘረዝራሉ፡፡
- ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያወችን መጫወት እና አካባቢያዊ ውዝዋዜዎች መወዛወዝ ሰርተው ያሳያሉ፡፡

## 3.1. የትውን እና የእይታ ጥበባትን በመጠቀም ታሪክን መንገር እና ማሳየት

### መግቢያ

ተማሪዎች በዚህ ክፍለ ትምህርት ላይ ታሪክ ፣ ባህል እና ቅርስ በሚገባ ተረድተውና ተገቢውን ዕውቀት በማግኘት በትወና እና በእይታ ጥበብ አስመስለው መስራት ይማሩበታል፡፡

የትውን እና የእይታ ጥበባትን ከፍተኛ በሆነ መንገድ ታሪክ እና ባህልን የመንገር ፣ የማሳየት እና በጥበባዊ መንገድ የማስተላለፍ አቅም አላቸው፡፡ በትወና እና በእይታ ጥበባትን የሚሰሩ ባህላዊ እና ታሪካዊ ክንውኖች በቀላሉ ከትውልድ ትውልድ ይተላለፋሉ፡፡

የእይታ ጥበባትን በመጠቀም ታሪክን እና ባህልን የሚነገሩ እና የሚያሳዩ በርካታ ሰዐሊያን ፣ ደራሲያን ፣ ገጣሚያን ፣ የሙዚቃ ባለሙያዎች አሉ፡፡ ስራዎቻቸውም ታሪክን እና ባህልን በማስተለለፍ ህያው ሆነው ይኖራሉ፡፡

አጥጋቢ የችሎታ ደረጃ

- በእይታ ጥበባት ፣ በትያትር ጥበባት ፣ በተንቀሳቃሽ ምስል እና በፎቶ አማካኝነት የአከባቢን የኪነ-ጥበብ ታሪኮችን ይገልፃሉ፡፡
- በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉ ምስላዎችን እና ምልክቶችን ይዘረዝራሉ፡፡
- ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎችን ተጫወተው እና አካባቢያዊ ውዝዋዜዎች ሰርተው ያሳያሉ፡፡

የማነቃቂያ ጥያቄ -1

1. አከባቢያቹ የሚገኙ ታሪካዊ እና ባህላዊ የእይታ ጥበብ እና ቅርሳችን እንዴት እንደምሰሩ ተወያዩ?

## 3.1.1. የእይታ ጥበባትን በመጠቀም ታሪክን መንገር እና ማሳየት

የእይታ ጥበባት ከሰው ልጅ የአስተሳሰብ ዕድገት ጋር ተያይዞ የመጣና በየጊዜው ከነበረው የሥልጣኔ ደረጃ ጋር እያደገ የመጣ ፈጠራዊ የሙያ ዘርፍ ነው። የእይታ ጥበባት ከጥንት ጀምሮ በየደረጃው የሰው ልጆች ማህበራዊ ፣ ኢኮኖሚያዊ ፣ ፖለተካዊ ፣ ባህላዊ ፣ ኃይማኖታዊ ፣ ታሪካዊ ፣ ተፈጥሮአዊ ፣ ምናባዊና ግላዊ የሆኑ ጉዳዮቻቸውን ይገልፁበትና የዕለት ተዕለት የኑሮ ደረጃዎቻቸውን የሚያንፀባርቁበት የጥበብ ዘርፍ ሆኖ ቆይቷል። በተጨማሪም በየዘመኑ የኖሩ የጥበቡ ባለሞያዎች የውስጥ ስሜቶቻቸውን ማለትም ደስታቸውን ፣ ብሶታቸውን ፣ አካባቢአቸውን ፣ ወዘተ የሚገልፁበት ዓለም አቀፋዊ ቋንቋ ነው።

ሥነ-ጥበብ በሁኔታዎች ላይ ያለንን ግንዛቤ ከፍ በማድረግ ነገሮችን በበለጠና በተሻለ መልኩ እንድንረዳ ያደርገናል።

ተማሪዎች የእይታ ጥበባትን በሚኖሩበት ማህበረሰብ ውስጥ ያላቸውን ልምድ የሚያንፀባርቁበት፣ ከአካባቢያቸው ጋር ያላቸውን መልካም ግንኙነት የሚገነቡበትና የተለያዩ ልምዶቻቸውን የሚያካትቱበት መንገድ ነው።

የሰው ልጅ መኖር ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ ሥነ-ጥበብ ነበር። ሁል ጊዜም ቢሆን የሰው ልጅ የመፍጠር ፍላጎትና ተፈጥሮ ሥነ-ጥበብን ለመሥራት ወሳኝ ምክንያት ሆኖ ቆይቷል። ሥነ-ጥበብ የሰው ልጅ ታሪኩን በፅሁፍ ማስፈር ከመጀመሩ በፊት ነበር።

በዚህ ክፍል ጊዜ የሥነ-ጥበብን አመጣጥና ቀደምት ታሪክ አጠር ባለመልኩ እንማራለን። በአውሮፓ የተገኙ የዋሻ ውስጥ ስዕሎች ከ40 ሺህ አመታት በፊት አካባቢ የተሰሩ መሆናቸው ይገመታል፡፡ በጥንት ጊዜ በዋሻ ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች የተለያዩ አራዊቶችን ምስል በዋሻ ግድግዳዎች ላይ ያሰንደ ዘመኑ እርዝማኔና ልዩ ባሕሪ አንፃር ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶት በስፋትና በጥልቀት ያልተጠና በመሆኑ ለወደፊት የምርምር አዋቂዎች ሰፊና ድንግል የጥናት መስክ መሆኑ ይታመናል።


እስካሁን ከፅሁፍ ማስረጃና አፈ-ታሪክ ገለፃ መሠረት ኢትዮጵያ የሦስት ሺ ዘመን የሥልጣኔ ባለቤትናት የሚለውን በመቀበል ታሪካችንን የምንገልፅ ቢሆንም እውነቱ ግን በአርኪዮሎጂ ማስረጃዎች በተለይም በቅድመ ታሪክ ጥናት ዘገባ የእንስሳትና የሰው ልጅ ቅሪተ-አካሎችንና የጥንት ሰው የሥራ ማከናወኛ መሣሪያዎችን በመመርመርና ዘመናቱን በመለካት ይረጋገጣል።

እንዲሁም የጥንት ሰውም የዕለት እንቅስቃሴውን፣ ተግባሩንና ስሜቱን የሚገልጽባቸው የዋሻ ሥዕሎችና ፍልፍል ሥራዎች በሐረር፣ በሰሜንና ደቡብ ኢትዮጵያ በተለያዩ የታሪክ ሥፍራዎች በብዛት መገኘታቸው የሀገራችን ታሪክ ከተጠቀሰው ሦስት ሺህ ዘመን በላይ መሆኑን ያስረዳል፡፡

## ታሪካዊ እና ባህላዊ እሴቶችን የሚያሳይ የገበያ ስዕል

ገበያ ስናስብ ብዙ ነገር ሊታሰብ ይችላል፡፡ ገበያ ሀብታም፣ ድሃ ፣ የሌለው ያለው ሁሉ በአንድ ላይ የሚጠቀምበት የስራ ቦታ ነው፡፡ ገበያ ብዙ ነገሮች ከተለያዩ አከባቢዎች የሚመጡበትና የሚጠጣና የሚበላ ሁሉ የሚቀርብበት የንግድ ቦታ ነው፡፡


**ለምሳሌ፡-** ሮ ተራ ፣ በግ ተራ ፣ እህል ተራ ፣ የልብስ ተራ ፣ ቅቤ ተራ ወዘተ በማለት ስያሜ ተሰተው የሚሰራበት ቦታ ነው፡፡



ምስል 53. ታሪካዊ እና ባህላዊ እሴቶችን የሚያሳይ የገበያ ስዕል

### የተግባር ሥራ-1

1. ተማሪዎች ከላይ የተመለከታችሁትን የገብያ ስዕል በቡድን በመሆን በደንብ ተመልክታችሁ ታሪካዊ እና ባህላዊ እሴቶችን እንዴት እንደያዘና እንደተሰሩ ተወያዩ ለሌሎች ቡድን ጓደኞቻችሁ እንዲነግሩ ማድረግ?2.
2. ተማሪዎች አካባቢያቹ ላይ ያለውን ገበያ በደንብ በመመለከት ከላይ በተመለከታችሁትን የገበያ ስዕል መሰረት ባህላዊ እሴቶችን በያዘ መልኩ በራሳችሁ አገላለፅ በንድፍ ስዕል ሰርታችሁ አሳዩ?



ምስል 54. ወደ ገበያ ሲሄዱ




ምስል 55. የአፄ ቴድሮስ በመቅደላ ከእንግሊዞች ጋር ያደረጉትን ጦርነት ታሪክ የሚያሳይ ስዕል፡፡

### የተግባር ሥራ-2

1. ተማሪዎች ከላይ የተመለከታችሁትን የአፄ ቴድሮስ በመቅደላ ከእንግሊዞች ጋር ያደረጉትን ጦርነት ታሪክ ስዕል በቡድን በመሆን በደንብ ተመልክታችሁ ታሪካዊ እና ባህላዊ እሴቶችን እንዴት እንደያዘና እንደተሰሩ ተወያዩ እና ሌሎች ቡድን ጓደኞቻችሁ እንዲነግሩ ማድረግ?

2. ተማሪዎች አከባቢያችሁ ያሉ ታሪክ አዋቂ ሰዎችን በደንብ በመጠየቅ ከላይ በተመለከታችሁት ስዕል አሳሳል መሰረት ታሪካዊ እና ባህላዊ እሴቶችን በራሳችሁ አገላለፅ በንድፍ ሰርታችሁ አሳዩ?
3. ተማሪዎች አባቶችን በአደዋ ጦርነት ጣልያንን ያሸፍንበት ታሪክ አከባቢያችሁ ያሉ ታሪክ አዋቂዎችን ሰዎችን በደንብ በመጠየቅ ከላይ በተመለከታችሁትን ስዕል መሰረት ታሪካዊ እና ባህላዊ እሴቶችን በያዘ መልኩ በራሳችሁ አገላለፅ በትወና ጥበብ ሰርታችሁ አሳዩ?



ምስል 56. ወራቶችን እና በየወራቶቹ የሚከናወኑ ሥራዎችን የሚያሳይ ተከታታይ ስዕል

## 3.2. ባህላዊ የሙዚቃ መሣሪያዎችና አካባቢያዊ ውዝዋዜዎች

### መግቢያ

ተማሪዎች በዚህ ምዕራፍ ትምህርት ላይ ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪዎችንና የአካባቢያዊ ውዚዋዜዎችን በተገቢው መማሪ አለባቸው፡፡ በሁሉም አከባቢ እንደየ አከባቢያቸው ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪዎችንና የአካባቢያዊ ውዚዋዜዎችን ያለ ሲሆን ተማሪዎች ይህን በተገቢው መንገድ ተምረው በማወቅ ፤ በመረዳት እና በመገናዘብ ክህሎታቸውን ፤ እውቀታቸው እና ጥበባቸውን ማዳበር ይጠብቅባቸዋል፡፡

### አጥጋቢ የችሎታ ደረጃ

- የባህላዊ ሙዚቃ መሳሪያ ምንነት ይገልፃሉ፡፡
- ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያ አይነቶችን ይዘረዝራሉ፡፡
- ከአከባቢያቸው ከሚገኙ ቁሳቁስ ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያ ሰርተው ያሳያሉ፡፡

**የማነቃቂያ ጥያቄ -2**

1. በአከባቢችሁን የሚገኙ ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎችን ተወያይታችው ዘርዝሩ?

### 3.2.2. -ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች

ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያ ማለት ሰዎች በአከባቢያቸው በተለምዶ ወይም የራሳቸውን እውቀት መሰረት አድርገው ወይም ሌሎች የሚሰሩትን በማየትና በማገናዘብ የተለያዩ የተፈጥሮ ወይም አንዳንድ ሰው ሰራሽ ቁሳቁሶችን በመጠቀም የሚሰሩት የሙዚቃ መሳሪያ ነው፡፡

የሀገራችን ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያ በአብዛኛው እንደ ሌላው ዓለም የሙዚቃ መሣሪያ በፋብሪካ የሚመረት አይደለም፡፡

ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያ በሀገራችን ከጥንት እየተወራረሰ የመጣውን እውቀት ሰዎች ተጠቅመው የራሳቸውን ባህል እና ወግ የሚገልጹበት ዘዴ ነው፡፡ በየአከባብያቸው የተለያየ የሙዚቃ መሳሪያዎች ፤ ዜማዎችን ፤ ውዝዋዜን በማሰማት የአንድን አከባቢ ባህል ሊገልጹ ይችላሉ፡፡ ባህል ማለት አንድ ሰው የራሱን ወግና ታሪክን አውቆ የሌላውንም የሚረዳበት መንገድ ሲሆን ይህ መንገድም በአልባሳት ፤

በአመጋገብ ፣ በሰርግ እና በመሳሰሉ ነገሮች ሰዎች የራሳቸውን ባህል የሚገልጹበት መንገድ ነው።

ከነኝህ መገለጫዎች ሙዚቃ እና የሙዚቃ መሳሪያዎችን ከፍተኛ ቦታ የሚይዝ ነው። ሙዚቃ በምድር ላይ ያሉ ሁሉ የሰው ልጆች የሚጠቀሙት የጥበብ ሥራ ነው። ለሰው ልጆች በተለየ ሁኔታ የአዕምሮ ማነቃቅያና መዝናኛ ሆኖ ያገለግላል። ሀገራችን ብዙ ብሔር ብሔረሰቦች እና ህዝቦች ያሉባት በመሆኑ በየአከባብያቸው የተለያዩ የሙዚቃ መሳሪዎች በዜማ በመደገፍ ባህላቸውን ይገልፃሉ።

ባህላዊ የሙዚቃ መሣሪያ የተባለበት ምክንያት ሰዎች የራሳቸውን ባህል ለመግለጽ በራሳቸው እውቀት ስለሚሰሩና የራሳቸውን ማንነት ይገልጻሉ ብለው ስለሚያስቡ ያወጡት ስያሜ ነው።

## ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያ አይነቶች

በሀገራችን የተለያዩ ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያ አይነቶች አሉ። ከእነሱ መካከልም ጥቂቶቹን እንመለከታለን። ይህ ያሀገራችን የሙዚቃ መሳሪያ በአራት ጎራ ይከፈላል። እነሱም የምት ፣ የክር ፣ የትንፋሽ እና እርስ በርስ በመጋጨት ድምጽ የሚፈጥሩ ናቸው።

**የማነቃቂያ ጥያቄ -3**

1. የምት ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች ከምን እንደሚሰሩ አብራሩ?

## ሀ. የምት የሙዚቃ መሳሪያዎች


የተለያዩ የምት የሙዚቃ መሳሪያዎች በየአከባቢያችን ሲኖሩ ከእነሱ መካከል ጥቂቶቹን እንመለከታለን።

ከበሮ፡- ከበሮ የምት የሙዚቃ መሳሪያ ሲሆን የመንፍሳዊ አገለልሎትም ይሁን ለሰርግ ፣ ለለቅሶ እና የተለያዩ በዓላት ጊዜ የሚያገለል የምት ሙዚቃ መሳሪያ ነው። ከበሮ ሲመታ ሽብሸባ ወይም ውዝዋዜ እንዲኖር ስለሚያደርግ ለመዝሙሩ ድምቀት ይሆናል ።


ይህ ሙዚቃ መሳሪያ አንድን መዝሙር ከስልተ ምቱ እንዳይወጣ አድርጎ የሚመራ መሳሪያ ነው። ይህ መሳሪያ የሚሰራውም ከጨርቅ ፣ ከእንጨት እና ከከብት ቆዳ ነው።

የከበሮ አይነቶች የተለያዩ ሲሆኑ ፤ ለመንፈሳዊ አገልግሎት የሚሆነው በአሰራሩ ሁለት በኩል መምቻ ያለው ሲሆን በግራ እጅ የሚመታበት ጠባብ ሲሆን በቀኝ እጅ የሚመታበት ሰፊ ነው።

ይህም በአብዛኛው በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስትያን ላይ መዝሙርን ለማጀብ ዋነኛ ድርሻ አለው።




ምስል 57. ከበሮ



ምስል 58. ለጋብቻ እና ለበዓላት የሚያገለግል ከበሮ (ካራቤ)

ይህ በምስሉ ላይ የሚታየው የሙዚቃ መሳሪያ ከሸክላ እና ከተለያዩ የእንስሳት ቆዳዎች የሚሰራ የሙዚቃ መሳሪያ ሲሆን ለሰርግ እና ለአንዳንድ አስደሳች ነገሮች እንጠቀመዋለን።



ምስል 59. ሁለቱም እኩል በእኩል የሆነ ከበሮ

ይህ በምስሉ ላይ የሚታየው ከበሮ ሁለቱም እኩል በእኩል የሆነ የምት የሙዚቃ መሳሪያ ነው። ይህ ከበሮ የሚሰራውም ከተለያዩ የእንስሳት ቆዳና ከእንጨት ነው። አብዛኛውን ጊዜ የምንጠቀመውም ለመንፈሳዊ አገለግሎት እና ለተለያዩ ክብረ በዓላት ነው።

1. በአከባቢያችሁ የሚገኙ የምት የሙዚቃ መሳሪዎችን በጹሁፍ ግለፁ፡፡

## ለ. የትንፋሽ የሙዚቃ መሳሪያዎች

የትንፋሽ የሙዚቃ መሳያሪዎች ብዙ አይነቶች ናቸው፡፡ ከእነሱ መካከል ጥቂቶችን እናያለን፡፡

### ዋሽንት(ሱሱሌ)


ይህ የሙዚቃ መሳሪያ በሀገራችን በኢትዮጵያ ይሁን በክልላችን በተለያዩ ቦታዎች የሚጠቀሙበት የሙዚቃ መሳሪያ ሲሆን ውስጡም ከላይ እስከ ታች ክፍት ይሆናል፡፡ የሚሰራውም ከቀረከሀ ፣ ከሸምበቆ ፣ ከቱቦ ወይም ውስጡ ክፍት ከሆነ ከማነኛውም ቀጭን ብረት ይሰራል፡፡

የዋሽንቱ እርዝማኔው ከ35-40 ሴንቲ ሜትር ርዝመት ሊኖረው ይችላል፡፡ ለዋሽንት አራት እና ከዛ በላይ ቀዳዳዎች ሲኖሩ የሚሰሩት እኩል ርቀት ላይ ነው፡፡ ይህን የሙዚቃ መሳሪያ ሲጫዎቱት በጣም የሚያምርና የሚያሳዝን ድምፅ ያለው ሲሆን በአለማዊ ሙዚቃም ሆነ በመንፈሳዊ መዝሙር የምንጠቀመው የሙዚቃ መሳሪያ ነው፡፡




ምስል 60. ዋሽንት ሲጫወት

ማይራ፡- ይህ የትንፋሽ የሙዚቃ መሳሪያ ሲሆን ከቀጫጭን ቀርከሀ ወይም ከሸምበቆ የሚሰራ የሙዚቃ መሳሪያ ነው፡፡ ስድስት የተለያዩ ቁመት ያላቸው ሲሆኑ አሰራራቸውም እንደየ ቁመታቸው የተለያዩ ናቸው፡፡ ስድስቱም በዛው ልክ የሚያወጣውም ድምፅ የተለያየ ነው፡፡



ምስል 61. ማይራ

**ካሳ** - ይህ ካሳ የሚባለው የትንፋሽ የሙዚቃ መሳሪያ አሰራሩ ቀንድ በመጥረብ ወይም በማሾል ነው። የሚያገለግለውም በተለያዩ አከባቢዎች ለለቅሶ ፣ ለስብሰባ ፣ የዕድር ውይይት ሲኖር እንደ ጠሩምባ መጥሪያ አድርገው ይጠቀሙታል። ይህ የሙዚቃ መሳሪያ አንድ ድምፅ ብቻ ያለውና ድምፁም ከሩቅ የሚሰማ ነው።




ምስል 62. ካሳ

**ሎላታ፡-** ይህ የሙዚቃ መሳሪያ በክልላችን ውስጥ በደራሼ አከባቢ የሚገኝ የሙዚቃ መሳሪያ ሲሆን በአከባቢያቸውም ታዋቂ የሆነ የሙዚቃ መሳሪያ ነው። የሚሰራውም ከተለያዩ ከእንስሳት ቀንድና ከጠንካራ እንጨት የሚዘጋጅ የትንፋሽ የሙዚቃ መሳሪያ ነው። ከላይ እስከ ታች ውስጡ በሙሉ ክፍት የሆነና በአፉ በኩል ጠበብ ያለ እና በታች በኩል ሰፋ ብሎ የሚሰራ ነው።

የላይኛው ስፋቱ 7 ሴንቲ ሜትር የታቸኛው ስፋት 5 ሴንቲ ሜትር እና ቁመቱ 40 ሴንቲ ሜትር ርዝመት አለው። ይህንን መሳሪያ በመጠቀም የአከባቢዊ ነዋሪዎች በበዓላት ጊዜ ባህላዊ ጨዋታቸውን ያደምቁበታል።

**ዛዬ፡-** ይህ የሙዚቃ መሳሪያ በክልላችን በተለያዩ አከባቢዎች ሲጠቀሙበት የቆዩ የትንፋሽ የሙዚቃ መሳሪያ ነው፡፡ የሚሰራውም ከቀርከሀ ፣ ከእንጨት ፣ ከከብት ቀንድና ከቆዳ የሚዘጋጅ ሲሆን ድምፁም እንደ ጡሩመባ ከፍና ዝቅ ያለ ሲሆን አጨዋዎቱም የሀዘንና የደስታ ጊዜ የተለያየ ነው፡፡ በደስታ ጊዜ ሲሆን በውዝዋዜና በሰዎች ድምፅ ይታጀባል ፡፡



ምስል 63. ዛዬ

**ዲንኬ፡-** የሚባል የሙዚቃ መሳሪያ በዳውሮ አከባቢ በከፍተኛ ሁኔታ የሚጠቀሙበትና ከብዙ አመታት ጀምሮ የአካባቢውን ባህል ሲያስተዋውቅ የቆየ የትንፋሽ የሙዚቃ መሳሪያ ነው፡፡ ዲንኬ የሙዚቃ መሳሪያ በአለማችን ረጅሙ የሙዚቃ መሳሪያ ነው፡፡ በሀገራችን ውስጥ በብዙ አከባቢ ለለቅሶ ለበዓላት የአካባቢያቸውን ጨዋታ ሲጫወቱበት እና ሲገለግሉበት ቆይተዋል፡፡ ይህ መሳሪያ የሚሰራው ከቀርካሀ ፣ ከገመድ ፣ ከቀንድ እና ከቆዳ ዙርያውን አጊጦ የተሰራ የሙዚቃ መሳሪያ ነው፡፡ በዲንኬ የሚታጀቡ ሰባት የአጨዋዎትና የውዝዋዜ አይነቶች አሉ፡፡ እነሱም ታታ ፣ ኮናሽያ ፣ ካርጭያ ፣ የዳ ፣ ጋድልያ ፣ ኤቃና ሎማቶ በመባል ይታወቃሉ፡፡



ምስል 64. ዲንኬ


65. ���� -2

የሚከተሉትን ጥያቄዎችን መልሱ?

1. የትንፋሽ የሙዚቃ መሳሪያዎችን አይነቶችን ዘርዝሩ?
2. በአከባቢያችው የሚገኝ የትንፋሽ የሙዚቃ መሳሪያዎችን ጥቅማቸውን በጹሁፍ አብራሩ?


## ሐ. የክር የሙዚቃ መሳሪያዎች

ክራር፡- ይህ የሙዚቃ መሳሪያ ከክር የሚሰራ የሙዚቃ መሳሪያ ሲሆን የሚሰራውም ከእንጨት ፣ ከክር ፣ ከቆዳ የሚዘጋጅ የሙዚቃ መሳሪያ ነው። በዚህ የሙዚቃ መሳሪያ ላይም አምስት ወይም ስድስት ክሮች ይኖራሉ። አጠቃቀሙም መዝሙርንም ይሁን ባህላዊ ጨዋታ ያጅባል። በውስጡም አምስት የተለያዩ ድምፆች ይኖራሉ። የክራር አጨዋወት አምስት ጣቶችን በአምስት በክሩ ላይ በማስቀመጥ ተራ በተራ በአንድ አንድ ጣት እንጫወታለን።



ምስል 66. ክራር


በገና፡- ወፍራም ድምጽ እና አስር ጅማት ያለው የክር የሙዚቃ መሳሪያ ነው። በገና በአገራችን በብዛት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስትያን ለመንፈሳዊ አገልግሎት የሚውል የሙዚቃ መሳሪያ ነው። በገና የሚሰራው ከእንጨት ፣ ከጅማት/ከከብት ጅማት እና ከቆዳ ነው።



ምስል 67. በገና

ማስንቆ፡- ባለ አንድ ክር የሙዚቃ መሳሪያ ነው፡፡ ማሲንቆ ወፍሮም ይሁን ቀጥኖ ተቃኝቶ የፈለገነውን ድምጽ መስጠት የሚችል የሙዚቃ መሳሪያ ነው፡፡

ማሲንቆ ለአለማዊም ይሁን ለመንፈሳዊም አገልግሎት የሚሆን የክር የሙዚቃ መሳሪያ ነው፡፡ የማሲንቆ አጨዋወት የማሲንቆ መምቻ በቀኝ እጅ በመያዝ በማሲንቆ ላይ የተወጠረውን ክር በግራ ጣት በማስቀመጥ እና በማንሳት እንጫዋታለን፡፡




ምስል 68. መስንቆ

## መ. እርስ በርስ በመጋጨት ድምፅ የሚፈጥሩ የሙዚቃ መሳሪያዎች

ጽናጽል፡-ይህ የሙዚቃ መሳሪያ በሀገራችን በተለይ በሀይማኖት ተቋማት የሚጠቀሙበት የሙዚቃ መሳሪያ ነው፡፡ በተለይ በኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስትያን መዝሙር ሲዘምሩ ከሌሎች ሙዚቃ መሳሪዎች ጋር በመሆኑ ለመዝሙሩና ለውዝዋዜው ድምቀት እንዲኖር

የሚያደርግ የሙዚቃ መሳሪያ ነው፡፡ ጽናጽል አጨዋወት እጅን በማወዛወዝ እርስ በርስ በማጋጨት ድምፅ እንዲሰጥ እንደርጋለን፡፡



ምስል 69. ጽናጽል

**ሉሌት፡-** የሙዚቃ መሳሪያ ብቻ ሳይሆን የሴቶች የእግር ማስጌጫ ነው፡፡ በደራሼ ባህል ሉሌት የሚባለው ከመዳብ የሚዘጋጁ ትናትሽ ቃጭሎች ናቸው፡፡ በከረሚያ እደ ጥበብ ባለሙያዎች ተሰርተው ለገበያ ይቀርባሉ፡፡ ቃጨሎቹ በቀጭንና ጠንካራ ክር ከታሰሩ በኃላ ሴቶቹ እንደ እግር አልቦ በቁርጭምጭሚታቸው ላይ ያደርጉታል፡፡ በተንቀሳቀሱ ቁጥር እያቃጨሉ ሙዚቃን ይፈጥራሉ፡፡ እያንዳንዷ ሴት ስትራመድ የሚያመነጨው ድምጽ የተለያየ ስለሆነ በልምድ መልኳን ሳያዩ ማንነቷን እስከመለየት ይደረሳል፡፡ በተጨማሪ በውዝዋዜ ወቅት ጨዋታን በማድመቅ ከፍተኛ ጠቀመታ አለው፡፡



ምስል 58 ሉሌት

## የሚከተለውን ጥያቄ መልሱ?

1. የጽናጽል ተግባራትን ምን እንደሆነ ተወያይታችው አብራሩ?

## 3.2.3. ባህላዊ ውዝዋዜ

በሰዎች እንቅስቃሴ እንዲታይ ወይም ለመደሰት የሚደረግ የኪነት ሥነ-ጥበብ ነው፡ ፡ ውዝዋዜ እንደየ ባህሉ የሚለያይ ሲሆን በአንድ ባህል ውስጥ በርካታ ልዩ ልዩ የውዝዋዜ አይነቶች ሊኖሩ ይችላሉ፡፡

ውዝዋዜ ሰዎች በተለያዩ አከባቢዎች ባህልን ለማስተዋወቅ በሰርግና በኃይማኖት በዓላት ሙዚቃ እና የሙዚቃ መሳሪያዎችን ተጠቅመው ስሜታቸውን የሚገልፁበት መንገድ ነው፡፡

**ለምሳሌ፡-** ከዚህ በታች ያለው ምስል ተመልከቱ፡፡



ምስል 70. የጋሞ ባህላዊ ውዝዋዜ



ምስል 71. የወላይታ ባህላዊ ውዝዋዜ



ምስል 72. የዳውሮ ባህላዊ ውዝዋዜ



ምስል 73. የደራሼ ባህላዊ ውዝዋዜ

## የተግባር ሥራ-4

1. ተማሪዎች በቡድን እየሆናችሁ የአከባቢያቸውን ውዝዋዜ አቅረቡ?

### ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ተማሪዎች ለእይታ ጥበብ የሚጠቀሙበት ፎቶግራፍ ፣ቅርፃቅርፅ ፣ እና የተለያዩ ሙያ በመጠቀም በአካባቢያችን የሚገኙ ባህልንና ቅርስን በስዕል መልክ ቀለምን ፣ እርሳስን ፣ ከሰልንና የመሳሰሉትን በመጠቀም ለዕይታ ማስቻል ሲሆን በአከባቢያችን የሚገኙ ቅርሶች ግንዛቤ እንዲኖር ተደርጓል፡፡ የሙዚቃ መሣሪያዎች ዓይነታቸውና አገልግሎታቸው በሰፊው በማወቅና በአከባቢያችን ያለውን ውዝዋዜን በመጠቀም ባህልን ለማሳደግ እና አመታዊ ክብረ በዓላትን ለማክበር ለተማሪዎች በሚስማማ መልክ በማዘጋጀት ትምህርቱን ተግባራዊ በማድረግ ለተማሪዎች ማስገንዘብ ተችሏል፡፡ በተጨማሪ ተማሪዎች ባህላዊ ጨዋታዎችን እና ውዝዋዜዎችን በሚገባ ተረድተዋል፡፡ በትምህርት ወቅት ያገኙትን እውቀት በመጠቀም ባህላቸውን እንዲጠብቁ በተንቀስቃሽ ምስል ፣ በፎቶ በመዝሙር እና የተለያዩ የትውን እና የእይታ ጥበብን በመጠቀም ማህበረሰቡን እንዲያገለግሉ ግንዛቤ ተሰቷቸዋል፡፡

# የክለሳ ጥያቄዎች

## ሀ. እውነት ወይም ሀሰት በሉ

1. የእይታ ጥበብ የአንድን አከባቢ ባህልንና ታሪክን ሊገልጽ ይችላል፡፡
2. በፎቶግራፍ አንድን ቅርስ ማቅረብ ቅርፃቅርፅ ተብሎ ይጠራል ፡፡
3. ክራር የትንፋሽ ሙዚቃ መሣሪያ በመባል ይታወቃል፡፡
4. ዋሽንትና ማይራ የምት ሙዚቃ መሳሪያዎች ናቸው፡፡
5. የምት ሙዚቃ መሣሪዎች ለመንፈሳዊ አገልግሎት ብቻ ያገለግላሉ፡፡

## ለ) ትክክል የሆነውን መልስ ምረጡ

1. ከሚከተሉት ውስጥ በደቡብ ኢትዮጵያ አከባቢ የምገኝ ቅርስ የቱነው?

   ሀ) አክሱም ሀውልት ሐ) ጀጎል ግምብ
   ለ) ኮንሶ ዋካ መ) ሁሉም

2. የትንፋሽ ሙዚቃ መሳሪያ ያልሆነው የቱ ነው?

   ሀ) ዋሽንት ለ) ማይራ ሐ) ከበሮ መ) ዲንኬ

3. ከሚከተሉት ውስጥ ልዩ የሆነው ምረጡ?

   ሀ) በገና ለ) ክራር
   ሐ) ማስንቆ መ) ሉሌት

## ለ. የሚከተሉትን ጥያቄዎችን መልሱ

1. በአከባቢያችው ከሚገኙ ከእደ-ጥበብ ሙያዎች ሁለቱን ፃፉ?
2. በክልላችን ውስጥ የሚገኙ ቅርሶችን በዝርዝር አብራሩ?
3. ከምት የሙዚቃ መሣሪያዎችን መካከል አንዱን በስዕል አሳዩ?

# ምዕራፍ አራት

## 4. የእይታ እና የትወና ጥበባትን በመጠቀም ሀገር በቀል እውቀቶችን ማድነቅና መግለጽ

### መግቢያ

ይህ ምዕራፍ የሚያተኩረው ሀገር በቀል እውቀቶች ላይ ሲሆን በዚህ ክፍል በአካባቢያችን የሚገኙ በማህበረሰቡ ትልቅ ቦታ ይዘው የሚገኙ እሴቶችን ማጉላት ማሳየት እና ማድነቅ ነው፡፡ በዚህ ዙሪያ የጥበባት ሚና ላቅ ያለ በመሆኑ ተማሪዎች በሚሰሯቸው ስራዎች የራሳቸውን ግንዛቤ ከማሳደግ አልፈው ለሌላው የህብረተሰብ ክፍል ማሳየት እና እውቅና መስጠት ይችሉበታል፡፡

ኢትዮጵያ ለሰው ልጅ መገኛ ብቻ ሳይሆን ለሙዚቃ ፣ ለትውን ፣ ለእይታ ጥበባትን ፣ ለባህል እና ለበርካታ አገር በቀል እውቀቶች ባለቤትነት፡፡

አገር በቀል እውቀቶችን የምንላቸው የአንድ አከባቢ ማህበረሰብ ከሌላ ማህበረሰብ በተለየ መንገድ ባህሉን የሚከውንበት መንገድ እና ለዛ ማህበረሰብ መለያ ሲሆኑ አገር በቀል እውቀቶች እንላቸዋለን፡፡ ለምሳሌ የእጅ ስራ አመራረት፣ የቤት አሰራር እና ቤት የማስዋብ ፣ የምግብ ስርዓቱ፣ በዓል አከባበሩ፣ ህክምና ፣ ግጫት አፈታት ፣ የደስታና የሀዘን ስርዓቶች ወ.ዘ.ተ.... ናቸው፡፡ በተጨማሪ በአከባቢያቸው የሚገኘውን ነገር ወይም ቁሳቁስ በመጠቀም ለበዓላት ወቅት ጅራፍ ፣ ገመድ፣ ገና ፣ ኳስ እና የተለየዩ ነገሮችን ተጠቅመው ባህላዊ ጨዋታዎችንና ውዝዋዜዎችን በመረዳት እንዲሁም የአከባብን ባህል የሚያንፀባርቁ ሃሳቦችን በስነ ውበት በመግለጥና በማስተዋወቅ መሆን ይጠበቅባቸዋል፡፡

### አጥጋቢ የችሎታ ደረጃ

- አካባቢያዊ የትወና እና የእይታ ጥበባትን በመዝሙር በትያትር ጥበባት፣በተንቀሳቃሽ ምስል እና በፎቶ አማካኝነት ሰርተው ያቀርባሉ፡፡
- ኪነንድፍ እና ባለቀለም የወረቀት ሞዛይክ በመጠቀም ባህላዊ እና ታሪካዊ ምስሎችን ሰርተው ያሳያሉ፡፡

- በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉ ምስላዎችን እና ምልክቶችን ሰርተው ያሳያሉ፡፡
- ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎችን መጫወት እና አካባቢያዊ ውዝዋዜዎች ያሳያሉ፡፡

## 4.1. የትውን እና የእይታ ጥበባትን በመጠቀም አገር በቀል እውቀቶችን ማድነቅ እና መግለጽ

### መግቢያ

ተማሪዎች በዚህ ክፍለ ትምህርት ላይ አገር በቀል እውቀቶችን በሚገባ ተረድተውና ተገቢውን ዕውቀት በማግኘት በትወና እና በእይታ ጥበብ ማድነቅ እና መግለጽ ይማሩበታል፡፡

አገር በቀል እውቀቶችን ማለት አንድ ሰዉ በአከባቢያቸው የምገኝ ባህልና ቅርስ በእደ ጥበብ ፣ በቅርፃቅርፅ ፣ ከሌላ ማህበረሰብ በተለየ መንገደ ሲተገበር እና መለያው ሲሆን አገር በቀል እውቀት እንለዋለን፡፡ ሀገር በቀል ስነ-ጥበባት ሲባል ጥበብ የራሱ የሆነ ቅርፅ ፣ እድገት ፣ ለውጥ እና መሻሻል ሲኖረው ቀደም ባለው ጊዜ ይሰሩ የነበሩ ስዕሎችን ቅርፃቅርፆችን ብንመለከት የማህበረሰቡን የተለያዩ ክንዋኔዎችን ለማሳየት ከሚጠቀሙባቸው ቦታዎች የሃይማኖት ስፍራዎች ትልቁን ድረሻ ይወስዳሉ፡፡ ምንም እንኳን መንፈሳዊ ይዘት ቢኖራቸውም ክብ ፊት ፣ ትላልቅ አይኖች ያለሏቸው እና ቀለም አጠቃቀማቸው ኢተዮጵያዊ መልክ መያዛቸው ሃገረሰባዊ የጥበብ አገላለፅ ዘይቤ ስላላቸው ከሌሎች የአሳሳል ዜቤይዎች የተለዩ ናቸው፡፡

### አጥጋቢ የችሎታ ደረጃ

- የትውንና የእይታ ጥባብን በመጠቀም አገር በቀል እውቀቶችን ይዘረዝራሉ፡፡
- የትውን እና የእይታ ጥባብን በመጠቀም በተንቀሳቃሽ ምስልና በፎቶ ያሳያሉ፡፡
- የትውን እና የእይታ ጥባብን በመጠቀም አገር በቀል እውቀቶችን ሰርተው ያሳያሉ፡፡
- በአከባቢያቸው የሚገኙ ባህላዊ የልጆች ጨዋታን ሙዚቃንና ምስልን ይገልጣሉ፡፡

### የማነቃቂያ ጥያቄ -1

1.አከባቢያቹ የሚገኙ ታሪካዊ እና ባህላዊ የእይታ ጥበብ እና ቅርሶችን እንዴት እንደተሰሩ ተወያዩ?

## 4.1.1. ሀገር በቀል የእደ ጥበብ ስራዎች

**እደ ጥበብ፡-** ሰዎች በተለያዩ ማህበረሰብ ዉስጥ የእጅ ሙያዉን ተጠቅሞ የቤት ቁሳቁሶችን፣ ጌጣጌጦችን ሰርቶ ካቀረቡ እደ ጥበብ እንላለን። ለምሳሌ ሻማ ስራ፣የሸክላ ስራ ፣ የእንጨት ስራ እና የመሳሰሉትን ይዛል። የዕደ -ጥበብ ባህሪላዊ መሳሪያዎችን እና ዘዴዎችን በመጠቀም በእጅ የሚሰራ የእቃ ዓይነት ናቸው።

እደ ጥበብ ባህላዊ እና ታሪካዊ መቼት ላይ በመመርኮዝ ከአካባቢ አከባቢ ሊለያይ ይችላል። እነዚህ የእጅ ሥራ ዕቃዎቹ ብዙውን ጊዜ በእጅ የተሠሩ እና የተሸመኑ እና ብዙውን ጊዜ እንደ አስፈላጊ የቤት ዕቃዎች ተደርገው ይታያሉ። በእጅ የተሰሩ የጥጥ ጨርቃ ጨርቆች እና አልባሳት የጥበብ ባሕላዊ የዕደ ጥበባት አንድ የተለመደ ምሳሌ ናቸው።

**ሽመና፡-** ኢትዮጵያ ከሚትታወቅባቸው በርካታ ባህላዊ አና ታሪካዊ እሴቶች መካከል የሕዝቦች ባህላዊ አለባበስ አንዱ ነው። ይህ ባህላዊ አለባበስ ደግሞ በአመዛኙ የሽመና ሥራ ውጤት ነው። የሽመና ሥራ በሀገራችን መቼና እንዴት እንደተጀመረ በትክክል የሚገልጽ የጽሑፍ መረጃ ባይኖርም ከሺ ዓመታት በላይ ዕድሜ እንዳለው አንዳንድ ጽሑፎች ይጠቁማሉ።

አሁን ባለንበት ዘመን በሀገራችን የሺ ዓመታት በላይ ዕድሜ ያስቆጠረው የሽመና ሥራ በስፋት የተዋወቀው ከጋሞ ተራራማ ቦታዎች የሚኖሩ ማሕበረሰብ አባላት አማካይነት ነው።

ከእነዚህ ውስጥ በጣም አስደናቂ ከሆኑት ሸማኔዎች መካከል በደቡብ ኢትዮጵያ ምዕራብ ደጋማ አካባቢዎች (በተለይም በዶርዜ) ውስጥ በሚገኘው የጋሞ ማኅበረሰብ ውስጥ ይገኛሉ። የእጅ ሥራ ምርት የአከባቢን ፣ ባህላዊ ወግ ፣ እና አገር በቀል ዕውቀትን የሚወክል መስህብ ነው። በእርግጥ ኢትዮጵያ እጅግ በጣም ብዙ የባህላዊ የእጅ ሥራዎችን በማምረት ረጅም ታሪክ አላት።



ምስል 74. የሽመና ሥራ



ምስል 75. ባህላዊ አልባስ

የተግባር ሥራ-1

1.ከላይ የተመለከታችሁት ባህላዊ ልብሳችን ሥነ-ውበታዊ ዕሴቱን አድንቁ?

2.ኪነንድፍ በመጠቀም ባህላዊ አልባሳትን ሥነ-ውበታዊ ዕሴት በጠበቀ መልኩ ሳሉ?

## ቅርጫት


ቅርጫት ስራ በተፈጥሮ ያደጉ ቁሳቁሶችን እንደ ቀርከሀ፣ ሸንበቆ እና ሌሎች

በጣም ጥቂት ቀላል መሳሪያዎችን የሚጠቀም ጥንታዊ የእጅ ሥራ ነው። ቀርከሀ ፣ ሸንበቆ በርካታ የቤት ቁሳቁሳች ለመስራት ያገለግላል እነደ ወንበር ፣ ጠረጴዛ ለቁሳቁስ መያዣ የሚያገለግሉ ቅርጫቶች ለማዘጋጀት ይውላሉ። የቅርጫት ስራ በሚሰሩና በሚጠቀሙበት ጊዜ ለቤትዎ ውበት ሊጨምር እና ለራስዎ የግል ትልቅ የትርፍ ጊዜ ማሳለፊያ ሊሆን የሚችል ነው።


ተማሪዎች የቀርከሀ ቅርጫት እና ሸመና አንፃር አካባቢያቸውን በዝርዝር እንዲለዩ እንዲያውቁና እንዲንከባከቡ እንዲሁም ውበቱን ፣ በንድፍና ቀለም ቅብ በቅርጻቅርፅ አማካኝነት እንዲገልፁ በማድረግ ላይ ያተኮረ ይሆናል።



ምስል 76. ቁሳቁስ ለመስራት የተዘጋጀ ቀርከሃ



ምስል 77. የቅርጫት ስራ



ምስል 78. ያለቀ ቅርጫት

## የተግባር ሥራ-3

1. ከላይ የተመለከታችሁት እና አከባቢያችሁ የሚገኙ የቅርጫት ሥራዎችን ሥነ-ውበታዊ ዕሴት አድንቁ?
2. የቅርጫት ሥራዎችን ሥነ-ውበታዊ ዕሴት በጠበቀ መልኩ አከባቢያችሁ በሚገኙ ቁሳቁሶችን በመጠቀም ሰርታችሁ አሳዩ?

**ሸክላ፡-** የአፈር ውጤት ነው:: የሸክላ ውጤቶች ፥ የቤት ቁሳቁሶችን እንደ ድስት ፣ ገንቦ ፣ ማሰሮ ፣ ሰሀን ፣ ኩባያ ወዘተ…እንዲሁም ለግንባታ ቤት ፣ ግቢ አጥር ፣ የመሬት ምንጣፍ ወለሎችን ወዘተ ፤ የተለያዩ ጌጣጌጦችን ቅርፃቅርፆችን ወዘተ… የሚሰራበትና የሰው ልጅ ሥልጣኔ ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ እስከአሁን ያልተለየው የዕደ ጥበብ መሠረት ነው:: ዋና ዋና የሸክላ ዕቃዎችን ዓይነቶች ፣ የድንጋይ ንጣፎችን እና ገንቦን ያካትታሉ:: የሸክላ አካል ከመቃጠሉ በፊት ወይም በኋላ ማስጌጥ ይችላል::

**ጀበና፡-** ኢትዮጵያ ውስጥ ለቡና ማፍያ የሚያገለግል ከሸክላ የሚሰራ አንገት ያለው ከስሩ ክብ የሆነ ፣ ከጎኑ ደግሞ ሹል የሆነ ማንቆርቆሪያ አፍ ያለው ፣ ባብዛኛው ጠቆር ያለ መልክ ያለው እቃ ነው::

ይህ የሚሰራውም በሸክላ ሰሪዎች ነው፤ በመጀመሪያ በጭቃ ተሰርቶ ይደርቃል፤ ከዚያ ይወለወላል፤ ከዚያ ይተኮሳል፤ ተተኩሶ ወይም በዕሳት ነዶ አፈር ይመስላል:: በሸክላ ሰሪዎች ለገበያ ይቀርባል:: ከዚያ ተጠቃሚዎች በእሳት ለብልበው ጥቁር ቀለም ይይዛል:: በመጨረሻ በስራ ላይ ይውላል::

**ለምሳሌ፡-** የጀበና አሰራር እንመልከት



ምስል 74 የሸክላ ሥራ

## ባህላዊ የልጆች ጨዋታ

በሀገራችን የተለያዩ ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያ አይነቶች እንዳሉ ባለፈው ምዕራፍ እንደተማሩ ይታወቃል፡፡ በዚህ ምዕራፍ ትምህርት ላይ ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎችን በመጫወት እና አከባቢያዊ ውዝዋዜዎች በመወዛወዝ ባህላችን ለሌሎች እንዲታወቅና እንድያድግ በመጫዎት እንገልጻለን፡፡ የጋሞ ባህላዊ የልጆች ጨዋታ በተለያዩ ማህበረሰብ ውስጥ እንደ አከባቢያቸውና የተለያዩ የልጆች ባህላዊ ጨዋታ ሲኖር በቴፕ ፣ በፊልም ፣ በቴሌቭዥንና በሚድያዎች እንደምትመለከቱት የልጆች ጨዋታ እንደየአከባቢው የተለያዩ በመሆኑ በባዓላት ሆነ በማነኛው ጊዜ ስሜታቸውን ለመግለጽ እና ለመዝናናት የባህላቸው ጨዋታ ከውዝዋዜ ጋር በማቀናጀት ያሳያሉ፡፡

**ለምሳሌ፡-** የመስቀል መቀበያ/ማስቃላ ጫቻ

## የመስቀል በዓል አከባበር በጋሞ አከባቢ እና ጨዋታ (ጋዜ ካሳ)

ከመስከረም መጀመሪያ ጀምሮ ፣ ከኢትዮጵያ አዲስ ዓመት በዓል ጋር የሚመሳሰል ፣ ዮ ማስቀላ አከባበር እስከ ወር መጨረሻ ድረስ በድምቀት ይከበራል፡፡

በዋናነት ፣ በዓመቱ ውስጥ ላበረከቷቸው እና ለወደፊቱ መልካም ነገሮች እንዲኖራቸው ለመጸለይ ለአከባቢው የእግዚአብሔር ስም የሆነውን ጦሳ ለማመስገን በማሰብ ይሰበሰባሉ፡፡

ዮ ማስቀላ በዓል ጋር በመንደሩ ውስጥ እንደ የሴቶች ቀን (ሶፌ ማስቃላ) እና የእርድ ቀን የመሳሰሉ የተለያዩ ባህላዊ ልምዶች ይከወናሉ፡፡

ሌላው የሚያስደስት ነገር ሰዎች ከጓደኞቻቸው ጋር ሲገናኙ ፣ ዮ ፣ ዮ ፣ ዮ (Yoooo) ብለው ደስታቸው ደስ በሚል ዜማ ይገልጻሉ፡፡ እና ከዚያ ሌሎቹ በረጅሙ ዮ ፣ ዮ ፣ ዮ ፣ ዮ ፣ ዮ ፣ ዮ (Yooooooo) ይመልሳሉ! ከዛም በረዥም ሳቅ እርስ በርሳቸው ይተቃቀፋሉ፡፡ ሌላው የበዓሉ አስደሳች ክስተት ግዙፍ የእሳት ቃጠሎ (ደመራ) ማብራት ነው፡፡ በጋሞ መንደር ውስጥ የደመራ መከበር በሌሎች የአገሪቱ ክፍሎች ተመሳሳይ ቀን ጋር የሚገጣጠም እና ከደመራ በዓል አከባበር ጋር በተመሳሳይ ሁኔታ ነው ፣ ክብረ በዓሉ ከእውነተኛው መስቀል ማግኘትን

ከሚያስታውሰው አንድ ቀን በፊት።

❖ የጋሞ ባህል የመስቀል በዓል /ጋዜ ካሳ አዘማመር

## ጋዜ ካሳ/ጫቻ ፡-

**ለምሳሌ፡-** አጨዋቹ የተቀባዮችን ስም እየጠራ መዝሙርን ያወጣል

| አጫዋች | ተቃባዮች |
|---|---|
| ሀ ማሳቃላ ሞኮስ | ሀ ማስቃላ ሞኮስ |
| አሳና ጎባ አባ | ሀ ማስቃላ ሞኮስ |
| ገምበሮና ገታ አሻ | ሀ ማስቃላ ሞኮስ |

እያሉ እጃቸውን እያጨበጨቡና እየተወዛወዙ መስቀሉ ከገባ/ ከቀን አስራ ስድስት ጀምሮ እስከ አስራ አምስት ቀን ድረስ ይጫወታሉ ።

አስራ አምስት ቀን ያህል ከተጫወቱ በኃላ ከዚህ በታች ያለው መዝሙር እየዘመሩ የመስቀል በዓልን አከባቢው/ በሀገር ሽማግለ ተመርቆ የሽኝት ስነ-ስርዓት ይደረጋል፡ ፡

| አጨዋች | ተቃባዮች |
|---|---|
| ሀ ማሳቃላ ሞኮስ | ሀ ማስቃላ ሞይዞስ |
| አሳና ጎባ አባ | ሀ ማስቃላ ሞይዞስ |
| አሳና ጎባ አባ | ሀ ማስቃላ ሞይዞስ |
| ገምበሮና ገታ አሻ | ሀ ማስቃላ ሞይዞስ |

### የቡዱን ስራ

1.መስቀል በዓል ስከበር በአከባቢያችሁ ከሚዘመሩት መዝሙር መካከል አንዱን በመምረጥ በቡዱን ተለማምዳችው አቅርቡ?

## ባህላዊ የሕዝብ መሰብሰቢያ ቦታ

ባህላዊ አደባባይ ለአብዛኛው የደቡብ ህዝቦች የተለያዩ ማኅበራዊ እና ባህላዊ ገጽታዎቻቸውን ለመሰብሰብ እና ለማካፈል የሚገለገሉባቸው ትልቅ ቦታዎች ናቸው። ባህላዊ አደባባዮች የመንደሩ ልዩ የባህል እና አገር በቀል እውቀት አቅም አንዱ ነው።



ምስል 79. ባህላዊ አደባባይ

በዋናነት የአንድ መንደር ነዋሪዎች ግጭቶችን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት የሀገር ሽማግሌዎች የሕዝብ መሰብሰቢያ ቦታ ሆኖ ያገለግላል:: እንዲሁም ለማህበራዊ ፣ ባህላዊ ክብረ በዓላት ፣ ለቅሶ ልምዶች እና ሃይማኖታዊ በዓላት ለማክበር የሚውል ቦታዎች ናቸው::

ከዚህ አንፃር በማህበረሰቦች መካከል ግጭቶች ከተነሱ ባህላዊ የግጭት አፈታት ወይም ድርድር የሚከናወነው በዚህ ቦታ በመንደሩ ሽማግሌዎች ነው:: እነዚህ ቦታ ለመንደሩ ነዋሪዎች አንድነትን ፣ ደስታን ፣ ሰላምን እና ደህንነትን ለረዥም ጊዜ እንዲጠብቁ ትልቅ ትርጉም አለው:: በተጨማሪም በዚያ ቦታ የተከናወነው ባህላዊ እንቅስቃሴ የመንደሩን ነዋሪዎች የቆዩ ባህሎችን ፣ ደንቦችን እና ወጎችን ለቀጣይ ትውልድ በዘላቂነት ለመጠበቅ እና ለማስተላለፍ የበኩላቸውን ሚና ይጫወታሉ::

ለምሳሌ፤- በጋሞ አካባቢ ዱቡሻ ይባላል፤ ጉራጌ አካባቢ ጆፎር ፣ በሀድያ ሀፋ አካባቢ ፣ ከንባታ ጠንባሮ አካባቢ ሀሌቾ ይባላል በየአካባቢያችሁ የተለያየ ስያሜ ሊኖረው ይችላል::

**ለምሳሌ፡-** የግጭት አፈታት ስነ-ዘዴ

ጋላታ እና በተቤሰቦቹ በእርሻ ስራ የሚተዳደሩ ናቸው:: በአንድ ወቅት አሻና ታላቅ ልጁ ዳራ ድንበራቸው ወደ ጋላታ እርሻ ቢያልፉ የጋላታ ልጅ የሆነው ዶሳ ይመለከትና ለቤተሰባቹ ይናገራል::

ጋላታና የጋላታ ቤተሰቦች በጋራ በመሆን የተለያየ ቁሳቁሶችን በመያዝ ለጸብ ሲሄዱ

ሽማግሌዎች ከዱቡሻ ሲመለሱ አይተው ለግጭት እንደምሄዱ አውቀው እርጥብ ሳር በመያዝ ከፊታቸው ይንበረከካሉ፡፡ በባህላቸው ታንፀው ያደጉ ስለሆኑ የያዙትን የጦር መሳሪያዎች በመጣል በሽማግሌ እንዲ ጠየቁ ያደርጋሉ፡፡ ወደ ጉታ በመሄድ ጉዳዩም በሽማግሎች ያመላልሳሉ ያጠያይቃሉ ከዛም ያሳምናሉ፡፡ አሻና ቤተሰቦቹ እንዳጠፉ ይደረሳል ጥፋተኛ እንደሆኑ ተናግረው በማመን ይቅርታ ተጠያይቀው ተቃቅፈው ይታረቃሉ፡፡

### የተግባር ሥራ-3

1. ተማሪዎች ከላይ የተመለከታችሁት ባህላዊ የሕዝብ መሰብሰቢያ ቦታዎች ሥነ-ውበታዊ ዕሴቱን አድንቁ፡፡
2. ኪነንድፍ እና የወረቀት ኮላጅን በመጠቀም ባህላዊ ሕዝብ መሰብሰቢያ ቦታ በጥሩ መልኩ ስሩ፡፡
3. ከላይ የተመለከታችሁት ባህላዊ ሕዝብ መሰብሰቢያ ቦታን የሚመስል ቦታን በትምህርት ቤታችሁ ቅጥር ጊቢ ውስጥ በመምረጥ የግጭት አፈታት ወይም የእርቅ ስርዓት በትወና ጥበብ ስሩ፡፡

## 4.2. የእይታ ጥበባትን በመጠቀም አገር በቀል እውቀቶችን ማድነቅ እና መግለጽ

### መግቢያ

ተማሪዎች በዚህ ክፍለ ትምህርት ውስጥ የእይታ ጥበባትን በመጠቀም አገር በቀል እውቀቶችን ሥነ-ውበታዊ ዕሴት ማድነቅ እና መግለጽ እንዲችሉ ይማራሉ፡፡ በዚህ ዙሪያ የጥበባት ሚና ላቅ ያለ በመሆኑ ተማሪዎች በሚሰሯቸው ስራዎች የራሳቸውን ግንዛቤ ከማሳደግ አልፈው ለሌላው የህብረተሰብ ክፍል ማሳየት እና እውቅና መስጠት ይችሉበታል፡፡ ኪነ-ንድፍ እና ባለቀለም የወረቀት ሞዛይክ በመጠቀም ባህላዊ እና ታሪካዊ ምስሎችን ሰርተው ያሳያሉ፡፡

### አጥጋቢ የችሎታ ደረጃ

- አካባቢያዊ የእይታ ጥበባትን እና በፎቶ አማካኝነት ሰርተው ያቀርባሉ፡፡
- ኪነ-ንድፍ እና ባለቀለም የወረቀት ሞዛይክ በመጠቀም ባህላዊ እና ታሪካዊ ምስሎችን ሰርተው ያሳያሉ፡፡
- በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉ ምሳሌዎችን እና ምልክቶችን ሰርተው ያሳያሉ፡፡


- ▶ አካባቢያዊ የትወና እና የእይታ ጥበባትን በመዝሙር በትያትር ጥበባት፣በተንቀሳቃሽ ምስል እና በፎቶ አማካኝነት ሰርተው ያቀርባሉ::

**የማነቃቂያ ጥያቄ -3**

1. = በአከባቢያችው የሚገኝ የቤት አሰራር ሂደቶችን አብራሩ?

## የዝሆን ቅርፅ ያለው የቀርከሀ ቤት ግንባታ በዶርዜ

ልክ እንደ ሸመናው ሁሉ ፣ የዶርዜ ሰዎች የዝሆን ቅርፅ ያላቸው ቤቶች ለመገንባታ የቀርከሃውን ዛፍ አንድ ላይ ይሸምናሉ፣ ያጣምራሉ::



ምስል 80. የዝሆን ቅርፅ ያለው የቀርከሀ ቤት ግንባታ አሰራር

በዚህ ደረጃ ፣ ቤቱ ከላይ ወደታች የተቀመጠ ቅርጫት ይመስላል:: ከዚያ ፣ በቤቱ ፊት ለፊት በኩል ዞኖ (zono) ተብሎ የሚጠራው የአፍንጫ ቅርጽ ያለው ክፍል ያደርጉ እና ፣ በግራና በቀኝ በኩል ለጭስ ማውጫ የሚያገለግሉ ሁለት ዓይኖችን ያደርጋሉ:: በመጨረሻ ፣ የጣሪያውን ክዳን በቀርከሃ ግንዶች ቅርፊት (ቃዳ) ያስጌጡታል:: በዚህ መንገድ መጨረሻ ላይ የዝሆን ቅርፅ ያለው ቤት ይገነባሉ:: የአፍንጫ ቅርፅ ያለው ክፍል እንግዶች መቀበያ ክፍል እንደ ሆኖ ያገለግላል:: በቤቱ መሃል ላይ ምግብ ለማብሰል ክፍት አለ:: በተጨማሪም በዚህ ዋና ቤት ውስጥ የከብት ማቆያ ፣ የመኝታ ቦታ እና የእህል ማከማቻ ክፍሎች ለብቻቸው ይገኛሉ::

## ከአፈር የተሠሩ ተፈጥሯዊ ሕንፃዎች::

ተማሪዎች ከአሸዋማ አፈር ተጠቅጥቀው የተሠሩ ተፈጥሯዊ ሕንፃዎች

ተመልክታችሁ ታውቃላችሁ፡፡ ጤሣጣ ወይም ኒው ዮርክ ይህ ተፈጥሯዊ መልክዓ ምድር የሚገኝበት ሥፍራ ኮንሶ ይባላል፡፡ ቢነኳቸው ፍርክስክስ የሚሉ የሚመስሉ ነገር ግን ዘመናትን የተሻገሩ መልክዓ-ምድራዊ ስጦታዎች፡፡ ኒው ዮርክ የሚለውን ስያሜ የሰጡት ጎብኚዎች ናቸው፡፡ ልክ እንደ ቤት መስኮት እና በር ያላቸው ዋሻዎች አሉት፡፡ ይህንን ያዩ ጎብኚዎች እኛ ሃገር ያለውን ኒው ዮርክ ይመስላል ብለው በዚያ ሰየሙት፡፡» ጎብኚዎች የሕንፃ ቅርፅ ያላቸው እኒህን የአሸዋ ክምሮችን ሲያዩ 'ይህማ ላሊባላን ይመስላል'፤ ይህኛው ደግሞ ፔንታጎንን በማለት ስያሜ ይሰጧቸዋል፡፡




ምስል 81. ጤሣጣ እና ኒው ዮርክ

## 777 የደረጃ መንገድ በተራራ ላይ

ተማሪዎች የደረጃ መንገድ በተራራ ላይ ተመልክታችሁ ታውቃላችሁ፡፡ ሀምባሪቾ 777 የደረጃ መንገድ በተራራ ላይ የታነፀ የእኛ ዘመን ትውልዶች የፈጠራ ውጤት ነው፡፡ ይህ ስፍራ ከባህር ወለል በላይ 3 ሺህ 58 ሜትር ከፍታ ላይ የታነፀ ነው፡፡ እነዚህ ደረጃዎች ወደ ተራራው ጫፍ የሚያደርሱ መንገድ ናቸው፡፡ ይህ መልክዓ ምድር የሚገኝበት ሥፍራ ከምባታ ጠንባሮ ይባላል፡፡



ምስል 82. ሀምባሪቾ

### የተግባር ሥራ-4

1. ተማሪዎች ይህ ከአሸዋማ አፈር የተሠሩ ተፈጥሯዊ መልክዓ ምድር ሕንፃዎች ያስገርማሉ አይደል፡፡ ተማሪዎች አከባቢያችሁን በትኩረት በመመልከት አካባቢያችሁ ያሉ ተፈጥሯዊ ቦታዎችን ከሌላ ነገርጋ ለማመሳሰል ሞክሩ?
2. የዝሆን ቅርፅ ያለው የቀርከሀ ቤት ሥነ-ውበታዊ ዕሴት በጠበቀ መልኩ አከባቢያችሁ በሚገኙ ቁሳቁሶችን በመጠቀም ሰርታችሁ አሳዩ?

## ከእንሰት ምግብን የማዘጋጀት ሂደት

ኢትዮጵያ ለተለያዩ ሰብሎች መነሻ ከሆኑ አገራት ማዕከላት አንዷ ናት፡፡ ዕንሰት በደቡብ እና በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ደጋማ አካባቢዎች ከሚገኙት ሥር የሰደደ ወይም ተወላጅ የእፅዋት ዝርያዎች አንዱ ነው፡፡ ይህ እንጨት አልባ ተክል ከሙዝ ተክል ጋር ይመሳሰላል ፣ ግን ከሙዝ ዛፍ ይልቅ ረጅምና ወፍራም ነው፡፡ እንደ ሙዝ ፍሬዎችን የማይሰጥ ሥር ሰብል ነው ፣ በዚህም ምክንያት “ሐሰተኛ ሙዝ” ይባላል፡፡

የዚህ ተክል ምርቶች በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች ከፍተኛ የአመጋገብ ጠቀሜታ እና እንደ ጣፋጭ ምግብ ይቆጠራል፡፡ በዚህም በደቡብ እና በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሰዎች በትልልቅ የእርሻ መሬት ወይም በአነስተኛ ጓሮ ቦታቸው ላይ ይተክሉታል፡፡

### የተግባር ሥራ-5

1. ከላይ በተመለከታችሁት መሰረት በአከባቢያችሁ ያሉትን ሀገር በቀል ምግብን የማዘጋጀት ሂደት ሥነ-ውበታዊ ዕሴቱን አድንቁ?
2. በአከባቢያችሁ ያሉትን ሀገር በቀል ምግብን የማዘጋጀት ሂደት በኪነንድፍ በመጠቀም በጥሩ ሁኔታ ስሩ?

## ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ተማሪዎች የትውን እና የዕይታ ጥበብትን በመጠቀም በአከባቢቸው የሚገኙ አገር በቀል እወቀቶችን በመዝሙር ፣ በውዝዋዜ ፣ በትወና እና በእይታ ጥበባት ቀለምን ፣ እርሳስን ፣ ከሰልንና የመሳሰሉትን በመጠቀም ለዕይታ ማስቻል ሲሆን በአከባቢያችን የሚገኙ ቅርሶች መንከባከብ ይጠበቅባቸዋል:: ተማሪዎች ስለ ባህልና ቅርስ የተለያዩ ቁሳቁስ ፣ የልጆች ጨዋታዎች ፣ ባህላዊ አልባሳት እንዲሁም የመዝሙሮችንና የውዝዋዜዎች ግንዛቤ ተሰቷል:: በዚህ ምዕራፍ ዉስጥ ተማሪዎች ለዕይታ ጥበብ የሚጠቀሙበት ፎቶግራፍ ፣ ቅርፃቅርፅ እና የተለያዩ ሙያ በመጠቀም በአከባቢያችን የሚገኙ ባህልንና ቅርስን በስዕል መልክ ቀለምን ፣ እርሳስን፣ከሰልንና የመሳሰሉትን በመጠቀም ለዕይታ ማስቻል ሲሆን በአከባቢያችን የሚገኙ ቅርሶች ግንዛቤ እንድኖር ተደርጓል:: አገር በቀል የባህለዊ ክብረ ባለት ፣ የእርቅ ስርዓትን ፣ የቤት አሰራርን እና በህለዊ መዝሙሮችን ፣ ውዝዋዜዎችን አይነታቸውና አገልግሎታቸው በሰፍው ማስገንዘብ ተችሏል::

## ክለሳ ጥያቄዎች

### ሀ. እውነት ወይም ሀሰት በማለት መልሱ

3. የትውን እና የዕይታ ጥበብ የአንድን አከባቢ አገር በቀል እውቀቶች ልገልፁ አይችሉም::
4. የእጅ ሥራ ምርት የአከባቢን ፣ ባህላዊ ወግ ፣ እና አገር በቀል ዕውቀትን የሚወክል መስህብ ነው::
5. በታሪክ መሠረት ባህላዊ ልብስ ማንኛውም ሰው ሊለብሰው ይችላል?
6. ኒው ዎርክ የምለውን ስያሜ የተሰጠው በአከባብው ሰዎች ነው?
7. የዕይታ ጥበብ የአንድን አከባብ ባህልንና ታርክን ልገልጥ ይችላል?

### ለ. የሚከተሉትን ጥያቄዎችን ትክክል የሆነውን መልስ ምረጡ?

1. ከሚከተሉት ውስጥ የእደ-ጥበብ ሙያ የሆነው የቱ ነው?

ሀ) የሸክላ ስራ
ለ) የሸማ ስራ
ሐ) የቀርከሃ ስራ
መ) ሁሉም

2. በኢትዮጵያ ውስጥ ሙዚቃ የማይዘመርበት ቦታ የት ነው?

ሀ) በሀይማኖት ቦታ
ለ) ባህልና ቱሪዝም
ሐ) ሰርግ ቤት
መ) መልስ የለም

3. ሀምበርቾ መንገድ የደረጃ ብዛት ስንት ነው?

ሀ) 666
ለ) 66
ሐ) 777
መ) 77

## ሐ. የሚከተሉትን ጥያቄዎችን መልሱ

1. በአከባቢያችው በዓላት ስከበር ከሚዘመሩ መዝሙር መካከል አንዱን መርጣችው በአጭሩ ጽፋችሁ አቅርቡ?
2. በአከባቢይችሁ ያለውን የእርቅ አፈታት ሂደትን በዝርዝር አብራሩ?
3. በአከባቢያችው ከምገኙ ከእደ-ጥበብ ሙያዎች ሁለቱን ፃፉ?

# ምዕራፍ አምስት

## 5. የእይታ እና የትወና ጥበባት ከሌሎች የትምህርት ዓይነቶች ጋር ያለው መስተጋብር

### መግቢያ

በዚህ በመጨረሻው ክፍል ምዕራፍ አምስት የስነጥበባት መስተጋብር ዝምድና እና ትግበራ ላይ የሚያተኩር ነው፡፡ በዚህ ክፍል የእይታ እና የትወና ጥበባት እርስ በእርስ እና ከሌሎች ሙያዎች ጋር ያላቸውን መስተጋብር ዝምድና እና ጠቀሜታ የሚታይበት ነው፡፡

በዚህ ምዕራፍ የትውን እና የእይታ ጥበባትን በመጠቀም ጠቃሚ እና ውድ ሀብቶቻችን ከመጠበቅ እና ከመንከባከብ ጋር ያለው መስተጋብር ፣ ዝምድና እና ጠቀሜታ የሚታይበት ነው፡፡ በዚህም ክፍል የጥበባት ሚና በሁሉም ዘርፍ ጠቃሚ መሆኑ የሚፈተሽበት ነው፡፡

ተማሪዎች በለፈው ከአንደኛ እስከ አምስተኛ ክፍል ድረስ የትወና እና የእይታ ጥበባትን በተለያዩ ምዕራፍ እየተከፋፈለ በተግባር ተምራችሁዋል፡፡ በዚህ ክፍል ትምህርት ምዕራፍ ላይ የትወናና የእይታ ጥበብን ከሌሎች ትምህርት አይነቶች ጋር ያለው መስተጋብራዊ፣ ዝምድናና ትግበራ ተምረዉ በማወቅ መሠረታዊ ክሎታቸውን ፣ እውቀታቸውንና ግንዛቤን ያዳብራሉ፡፡ በዚህ ምዕራፍ የሚያተኩረው ስለ ጥንቃቄ፣ ደንነት ፣ አየር ንብረት እና ስርዓተ ፆታ ሲሆን ተማሪዎች የሚኖሩበትን ማህበረሰብ እና አከባቢያቸውን በመገነዘብ ራሱን ሆነ ሌላውን ማህበረሰብ ከተለያዩ በሽታዎች እና ከአደጋ ለመጠበቅ ነው፡፡

ተማሪዎች ቤታቸውንና የትምህርት እና የአከባቢያቸውን ፅዳትና ዉበትን በመጠበቅ ማህበረሰቡን ማገልገል ይችላሉ፡፡

የትራፊክ ምልክቶችን ጠቀሜታን በመገንዘብ የትራፊክ አደጋ መንሴኤዎችንና መከላከያ ዘዴዎችን መተግበር ተገቢ ነው፡፡ የአየር ንብረት በአለማችን በከፍተኛ ሁኔታ ሙቀት እንድጨምር እያደረገ በመሆኑ በዚህ ምክንያት የሚከሰቱ

ድርቅና ርሃብ ስለሚከሰት ይህን ችግር ለመቀነስ እያንዳዱ ማህበረሰብ አረንጓደ ልማትን በማሳደር በመንከባከብ አስፈላጊ ነው፡፡ በተጨማሪ ከኮሮና ቫይረስ ራሱንና ማህበረሰቡን መጠበቅና መከላከያ ዘዴዎችን በአግባቡ በመጠቀም ራሳቸውን እንድከላከሉ ያስፈልጋል፡፡ የኮሮና ህሙማንና እንክብካቤ ማድረግ እንዳለባቸው በመገንዘብ ስለ ኮሮና ገላጭ የሆኑ መዝሙሮችን በመዘመር ለማህበረሰሰቡ ግንዛቤ ትምህርት እንድሰጡ የሚያስችል እውቀት እንድኖራቸው ያደርጋል፡፡

### አጥጋቢ የችሎታ ደረጃ

- የትወን እና የእይታ ጥበባትን ከሌሎች የትምህርት ዓይነቶች ጋር ያለውን እንዲሁም ከወቅቱ አንገብጋቢ ጉዳዮች ጋር መስተጋብራዊ ስራዎችን ሰርቶ ማሳየት፡፡
- ሰርቶ ማሳየት እና ጉብኝት ማከናወን፡፡

### የማነቃቂያ ጥያቄ -1

1. የትውን እና የእይታ ጥበባትን ከሌሎች የትምህርት ዓይነቶች ጋር ያለው መስተጋብር አብራሩ?
2. ጥንድ ጥንድ በመሆን «የአየር ንብረት ለውጥ» ሀሳብ ላይ እየተነጋገራችሁ በዝርዝር አብራሩ?

## 5.1. የትውን እና የእይታ ጥበባትን በመጠቀም ጠቃሚ ሀብቶችን ከመጠበቅ እና ከመንከባከብ ጋር ያለው መስተጋብር

### መግቢያ

በዚህ ክፍለ ትምህርት ውስጥ የተውንና የእይታ ጥበብን በመጠቀም በአከባቢያቸው ያለው ጠቃሚ ሀብቶችን በአገባቡ እንደት መጠበቅና መንከባከብ እንዳለብን ያስረዳል፡፡ በመሆኑ ማህበረሰቡ ሀብቶቻቸውን እንክብካቤና ጥበቃ በማድረግ ከትውልድ ወደ ትዉልድ እንዲተላለፍ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ተማሪዎች በአከባቢያቸው የሚገኙ የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ሀብቶቻቸውን በአግባቡ በመጠበቅና በመንከባከብ ለማህበረሰቡ ግንዛቤ እንዲኖራቸው

በማድረግ በመዝሙር እና በውዝዋዜ በመጠቀም ጠቃሚ ሀብቶችን ማህበረሰቡ እንዲጠብቅ ማስተላለፍ እንዳለባቸው ይታመናል። ስለሆነም በአከባቢያቸው የሚገኙ ማናቸውም ጠቃሚ ሀብቶችን በአግባቡ መጠበቅና መከባከብ አስፈላጊ ስለሆነ ለሀብቶች ልዩ ጥበቃ ማድረግ ትልቅ ሀላፍነት በመሆኑ ሁላችንም ጠቃሚ ሀብቶችን መጠበቅ ይኖርበታል። በዚህ መሠረት ተማሪዎች ከላይ የተዘረዝሩትን ጠቃሚ ሀብቶችን ለመጠበቅ ለመንከባከብ በመዝሙር ፣ በስዕል በተንቀሳቃሽ ምስሎች አማካይነት የራሳቸውን ተሳትፎ በማድረግ ሌሎችንም ማስተማር ይጠበቅባቸዋል።

## አጥጋቢ የችሎታ ደረጃ

- የትውን እና የእይታ ጥበባትን ከሌሎች የትምህርት ዓይነቶች ጋር ያለውን እንዲሁም ከወቅቱ አንገብጋቢ ጉዳዮች ጋር መስተጋብራዊ ስራዎችን መስራት ይችላሉ።
- ሰርቶ ማሳየት እና ጉብኝት ያከናውናሉ።

### የማነቃቂያ ጥያቄ

1. ትውን እና የእይታ ጥበባትን በመጠቀም ጠቃሚ ሀብቶችን ከመጠበቅ እና ከመንከባከብ ጋር ያለው መስተጋብር ከክፍል ጓደኞቻችሁ ጋር ተወያዩ?
2. በትውን እና እይታ ጥበባት ከሳይንስ ትምህርት ጋር ምን እንደሚያገናኛቸው ግለጹ?

## በትውን እና እይታ ጥበባት ከሳይንስ ትምህርት ጋር ዝምድና

የትውን እና እይታ ጥበባት ከምናስበው በላይ በትክክለኛው መንገድ ጥቅም ላይ ሲውል, አንዳንድ ከባድ እና ጠቃሚ የሳይንስ ሀሳቦችን በደንብ ያስተላልፋል። በመደበኛነት ሊታዩ የማይችሉ ረቂቅ ሀሳቦችን ለመቅረጽ እና ተማሪዎች ትርጉም እንዲፈጥሩ ያግዛሉ። ተማሪዎች በሳይንሳዊ ሀሳቦች እንዲወያዩ እና እንዲያመዛዝኑ እድል ይስጡ።

*መምህራንን ተማሪዎችን ያሳትፉ እና ያበረታቱ በማስተማር ውስጥ ፈጠራ!*

*መምህራን ተማሪዎች ምን እንደሚያስቡ እንዲያዩ መርዳት*

በሳይንስ ክፍሎች ውስጥ በትክክል ሊሰሩ የሚችሉ አንዳንድ ምሳሌዎችን ከዚህ በታች እንመልከት።

## የተግባር ሥራ-1

1) ካርድ ላይ ያለሁት ገጸባህሪ - እኔ ማን ነኝ?

ተማሪዎች ካርድ ላይ ገጸባህሪ ተሰጥቷቸዋል እና ከክፍል ፊት ለፊት እንደ ገጸባሪውን ተገባራቶች ተላብሰው የገጸባህሪውን ስም ሳይገልጹ ይተውናሉ::

የክፍል ጓደኞች የገጸባህሪውን ስም ምን እንደሆነ ይገምታሉ::

**ለምሳሌ፡-** ገጸባህሪ - ኮንፒውተር

መረጃ አስቀምጣለሁ ፣ ያስቀመጣችሁትን መረጃ ማየት ስትፈልጉ አሳያለሁ ፣ በበይነህ መበረብ ዓለምን ከዓለም አገናኛለሁ::

የገጸባህሪ ጥራትን ለማሻሻል ለተማሪዎች የዝግጅት ጊዜዎችን አስቀድመው መስጠት የተሻለ ነው::

## 1. ታሪካዊ ተውኔቶች


ተማሪዎች በአንድ የሳይንስ ሊቃውንት ፣ ትሌቶች ፣ የጥበብ ባለ ሙያዎች ፣ ተጽእኖ ፈጣሪ ግለሰቦች ህይወት ገጽታ ዙሪያ የተመሰረተ አጭር ተውኔት ይፈጥራሉ ይህም ለክፍሉ አቅርቡ::

ምሳሌ: ተማሪዎች ስለ ዶክተር አክሊሉ ለማ ፣ አበበ ቢቂላ ፣ አይሌ ገብረ ሥላሴ ፣ አፈወርቅ ተክሌ ፣ ጥላሁን ገሰሰ ፣ ፕሬዝዳንት ሳህለወርቅ ዘውዴ ሌሎችንም ግለሰባች ታሪክ ያቅርቡ::

## የአየር ንብረት

የአየር ንብረት ለውጥ ሙሉ በሙሉ ሰው ሠራሽ ነው ባይባልም ለለውጡ የሰዎች ተግባራዊ እንቅስቃሴዎች ከፍተኛ አስተዋጽኦ አላቸው:: የሕዝብ ቁጥር ሲጨምርና ኢንዲስትሪዎች ሲስፋፉ የኃይል ምንጭ አጠቃቀምና የጥሬ እቃዎች ፍጆታ ይጨምራል:: ይህም በበኩሉ ጎጂ ኬሚካላዊ ነገሮች እንዲመረቱና በአካባቢ አየር ውስጥ እንዲገቡ ምክንያት ይሆናል:: የአየር ንብረት ለውጥን መቀነስ የአየር ንብረት ለውጥ፣ ባልተለመደ መልኩ ምድራችንን እየተፈታተናት የመጣ የዘመናችን የተፈጥሮ አደጋ ነው:: ለውጡ የተፈጥሮ ሚዛንን በማዛባት ፣ የምድራችንን የውኃ ትነት መጠን በከፍተኛ ደረጃ እንዲባባስ አድርጓል::

ተማሪዎች እነዚህ መነሻ ሀሳቦችን በመንተራስ እና በሌሎች ትምህርት አይነቶች ላይ የተማራችሁትን ሀሳቦች በመከለስ በትወና እና በእይታ ጥበባት ለመገለፅ መስራት ትማራላችሁ።




ምስል 84. አየር ንብረቱ የተጎዳ ቦታ የተጠበቀ ቦታ የሚያሳይ



ምስል 85. የአየር ብክለት ስዕል

## የተግባር ሥራ-2

1. የሚከተለውን ሠንጠረዥ መሠረት በማድረግ «ሰው ሠራሽ የአየር ንብረት ለውጥ ምክንያቶችና ውጤቶች» በሚል ርዕስ የተውኔት ድርሰት አላባዊያንን ያሟላ ድርሰት ጻፉ?
2. «ሰው ሠራሽ የአየር ንብረት ለውጥ ምክንያቶችና ውጤቶች» የጻፋችሁት የተውኔት ድርሰት አዘጋጅታችሁ በቡድን በመሆን በትውና አቅርቡ?

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| • የደኖች መጨፍጨፍ<br>• የኢንድስትሪዎችና የተሽከርካሪዎች ልቀት… | • በከባቢ አየር የካርቦን ዳይኦክሳይድ መጠን መጨመር<br>• የጋዞች ይዘት ምጥጥን መዛባት | • ሙቀት መጨመር | • የበረዶ መቅለጥ የውቅያ ሶች ከፍታ መጨመር<br>• የውኃ ትነት መጠን መጨመር | • የአየር ንብረት ለውጥ<br>• ያልተጠበቀ ዝናብና ጎርፍ የመሬት መንቀጥቀጥ |

ሰንጠረዥ 1. የንድፍ ስራ የአየር ብክለትን

ተማሪዎች ከላይ በምትመለክቱት የንድፍ ስራ ከኢንዱስቲሪ የሚወጡ ጭሶች እንዴት ምድራችንን እንደ ሚበከለው እና የሙቀት መጠኗ እየጨመረ እንዳለ በፈጠራዊ በሆነ መልኩ በተለየ አገላለጽ ተስሏል።

## የተግባር ሥራ-3

1) ያለምንም ማመንታት, መደጋገም ወይም ማፈንገጥ ንግግር ማቅረብ!

አንድ ተማሪ ወደ ክፍሉ ፊት ለፊት መጥቶ ስለ አንድ ርዕስ ጉዳይ ያለምንም ማመንታት፣ መደጋገም እና ማፈንገጥ ይናገራል።

**ለምሳሌ:-** ስለ እይታ እና ትወና ጥበባት ፣ ስለ ፎቶሲንተሲስ ፣ ስለ ጤና ፣ ስለ መንገድ ደህንነት ፣ ስለ አካባቢ ጥበቃ በሚናገሩበት ጊዜ ትኩረት ይኑርዎት።

የክፍል ጓደኞች ማመንታት፣ መደጋገም ወይም ልዩነት ካዩ እጃቸውን ወደ ላይ ማድረግ ይችላሉ።

2) ሰው ሠራሽ የአየር ንብረት ለውጥ ጉዳትን እና ከአየር ብክለት ነፃ የሆነን ቦታ የሚያሳይ የራሳችሁን ሀሳብ እና ፈጠራ የሚያሳይ የንድፍ ስዕል ስሩ?

## ደን

ደን ማለት ሰው ሰራሽ ወይም በተፈጥሮ በእፅዋት የተሸፈነ ቦታ ነው። ደን ለሰው ልጆች ከፍተኛ ጠቀሜታ ያለው ሀብት በመሆኑ ሁሉም ሰው ደንን መጠበቅና መንከባከብ ይኖርበታል። ደን ከሌለ የተለያዩ ችግሮች ይከሰታል። ከነእዚህ መካከልም የአየር ንብረት መዛባት ፣ የመሬት መሸርሸር ፣ ዝናብና ውሃ ማጣት እና በአጠቃላይ ደንን በማጣት ምክንያት በአከባቢያችን ድርቅ ስለሚከሰት ለደን በቂ እንክብካቤ እና ጥበቃ መደረግ አለበት። ተማሪዎች ይህን በማወቅ የተማራችዉትን እውቀትና ግንዛቤን በመጠቀም ለማህበረሰቡ ለደን ያለዉ ጠቀሜታ መግለፅ እና እንክብካቤ እንዲያደርጉ በመዝሙር ፣ በውዝዋዜ ፣ በእይታ ጥበብ እና በተለያዩ መንገድ ደንን እንዲጠብቁ ግንዛቤ መስጠት ይጠበቅባቸዋል።



ምስል 86. ደን

## መዝሙር፡- ደኑ ለሕይወቴ

አለሁኝ እኔው ለኔ ደኑ ለሕይወቴ

ብሎም ለወገኔ ለረሃብ መድሐኒቴ

ለህንፃው ለጎጆው ዋልታና ማገሩ

ለእርሻ መሳርያችን ለሞፈር ቀንበሩ

ለሸማኔው እቃ ለቅሉ ለእንዝርቱ

ደንነው መሰረት ደንነው ሕይወቱ

አዝማች

ባህርዛፍ ቀረሮ ዝግባውና ጥዱ

ለአፈር ጥበቃ ይብዛ በመንገዱ

ይሁን ባሕላችን ችግኝን በማፍላት

አፈር መንከባከብ ውሃማ




## የተግባር ሥራ-4

1) ተማሪዎች ከላይ ያለውን መዝሙር ተለማምደው በጋራ እንዲዘምሩ ያድርጉ

**አባይ፡-** የአገራችን ትልቁና ጠቃሚ ሀብት የሆነ ወንዝ ቢሆንም ብዙ አመት ያለ ጥቅም ወደ ሌላ አገር ሲፈስ የቆየ መሆኑን ታሪኮች ይገልፃሉ፡፡ አባይ አገራችን ብቻ ሳይሆን በአህጉራችን ከፍተኛ ዋጋ ያለው ወንዝ ሲሆን በአሁኑ ሰዓት ለአገራችን ጥቅም ላይ ለመዋል እየተገነባ አብዛኛው አልቆ በይገኛል፡፡ ግድቡ ሲጠናቀቅ ለብዙ ሰው የስራ እድል እንደሚፈጥር ፣ የኤሌክትሪክ ጥቅም ፣ ለመስኖ ፣ ለአሳ እርባታ እና ገቢ ማስገኛ እንደሚሆን ይታመናል፡፡

አባይ የሀገራችን ሀብት በመሆኑ ግድቡ ለወደፊት የሚሰጠውን ጥቅም በማመን ሁላችንም በመረዳት ማህበረሰቡም ተረድተው በአንድነት እንዲሰሩ እና ግንዛቤ እንዲኖራቸው በመዝሙርና በእይታ ጥበባት በመጠቀም ማስተማር ይገባናል፡፡



ምስል 87. ዓባይ



ምስል 88. የዓባይ ግድብ

## ለሥርዓተ-ጾታና ትምህርት

የትውና እና የእይታ ጥበባት ማህበራዊ ጉዳዮቻችን ፣ በማህበረሰባችን ውስጥ ያሉትን መልካም

ነገሮችን ለማስተላለፍ እና ለማሳየት እንጠቀምበታለን፡፡

ሁሉም ማህበረሰብ ውስጥ ያሉትን ጎጂ ባህሎች እና የተዛቡ አመለካከቶችን ለመተቸት እና በጥበብ መንገድ አዲስ አስተሳሰቦችን ማዳበር እንዲችል የማድረግ አቅም አለው፡ ፡ ተማሪዎች ስለ ሥርዓተ-ጾታና በሌላ ትምህርት ዓይነቶች ላይ እንደተማራችሁ እና ግንዛቤ እንዳላችሁ ይታመናል፡፡ በዚህ ክፍለ ጊዜ ስለ ሥርዓተ-ጾታ በስዕል ፣ በትወና ትማማራለችሁ፡፡



ምስል 89. ወንድና እና ሴት ልጆች ለሁለት ዓለም ይዘው ያሳያል

ሥርዓተ-ጾታና ጾታ የተለያዩ እሳቤዎች ናቸው። ጾታ በወንድና በሴት መካከል ያለን የተፈጥሮ ልዩነት የሚያሳይ ነው። ሥርዓተ-ጾታ ደግሞ በሰዎች የመኖር ሂደት በማህበረሰቡ አማካይነት ተፈጥሮ ያደገ ብሎም የማኅበረሰቡ ምጣኔ ሀብታዊ ፣ ማኅበራዊና ፖለቲካዊ ለውጥ ሲኖር አብሮ ሊቀየር የሚችል አስተሳሰብ ነው። ስለሆነም የሥርዓተ-ጾታ ጽንሰ ሀሳብ በወንዶችና በሴቶች መካከል ያለውን ያልተመጣጠነ ተሳትፎና ተጠቃሚነት ለመግለጽ ያገለግላል።





ምስል 90. ወንድና እና ሴት ልጆች ቤታቸውን ስራ ተከፋፍለው ሲያጸዱ ያሳያል

የተግባር ሥራ-1

1. የሴቶች ቀን» በሚል ርዕስ የትወና ድርሰት ለመጻፍ የሚያስችሉ ሀሳቦችን አደራጅታችሁ ፃፉ?
2. «የሴቶች ቀን» በሚል ርዕስ የትወና ድርሰት የፃፉትን ድርሰት ለትወና አዘጋጅተው ገጸባህርያትን ተከፋፍለው በትወና አቅርቡ?

## 5.2. የእይታ እና የትወና ጥበባት ከሌሎች የትምህርት ዓይነቶች ጋር ያለው መስተጋብር

### መግቢያ

በዚህ በመጨረሻው ክፍል ምዕራፍ አምስት የስነ-ጥበባት መስተጋብር ዝምድና እና ትግበራ ላይ የሚያተኩር ነው፡፡ በዚህ ክፍል የእይታ እና የትወና ጥበባት እርስ በእርስ እና ከሌሎች ሙያዎች ጋር ያላቸውን መስተጋብር ዝምድና እና ጠቀሜታ የሚታይበት ነው፡፡

በዚህም ክፍል የጥበባት ሚና በሁሉም ዘርፍ ጠቃሚ መሆኑ የሚፈተሽበት ነው፡፡ ትወና ጥበባት የተለያዩ የትምህርት አይነቶችን በትወና ፣ በመዝሙር ፣ በውዝዋዜ ፣ እና በተለያዩ የትወና ጥበባት በማዋዛት ለማስተማር እንጠቀምበታለን፡፡ በዚህ ምዕራፍ የማህበራዊ ሳይንስ ትምህርትን ለማሳየት እና ከትውን ጥበባት ጋር ያለው መስተጋብር እንመለከታለን፡፡ ተማሪዎች ባለፈው ክፍለ ትምህርት ላይ በብዙ ምዕራፍ ተከፋፍለው የትውን እና የእይታ

ጥበብን በሚገባ ተምራችዋል።

በዚህ ክፍለ ትምህርት ላይ ሙዚቃ ከሌሎች ትምህርት አይነቶች ጋር ያለዉ መስተጋብራዊ ዝምድናና ትግበራ በሚገባ መማር ፣ መገንዘብ ፣ መረዳት እና ማወቅ ይገባቸዋል። ተማሪዎች ሙዚቃ ለሌላው ትምህርት ያለው ጠቀሜታ እና ግንኙነቱንም መረዳት አለባቸሁ።

## አጥጋቢ የችሎታ ደረጃ

- የትውን እና የእይታ ጥበባትን ከሌሎች የትምህርት ዓይነቶች ጋር ያለውን እንዲሁም ከወቅቱ አንገብጋቢ ጉዳዮች ጋር መስተጋብራዊ ስራዎችን መስራት።
- ሰርቶ ማሳየት እና ጉብኝት ።
- ሙዚቃ ከሌሎች ትምህርት አይነት ጋር ያለው ዝምድናና ትግበራ ይገልፃሉ።

### የማነቃቂያ ጥያቄ -2

1. ተማሪዎች በአከባቢያችው ለአካል ጉዳተኝነት ሊያጋልጡ የሚችሉ ነገሮችን ተወያዩ?

አካል ጉዳተኝነት ማንኛውም ሰው ሊያጋጥመው የሚችል ተፈጥሮአዊም ሆነ ሰው ሠራሽ አደጋ ውጤት ነው። እንደምናውቀው አካል ጉዳተኝነት የሰው ልጆች አኗኗር አንዱ ገጽታ ነው። አካል ጉዳተኝነት ስላልፈለግነው የሚቀር ሳይሆን፣ ባጋጣሚ የሚመጣ መሆኑን መረዳት ይኖርብናል።

መረጃዎች እንደሚያስረዱት አንድ ቢሊዮን የሚሆኑት ሰዎች አካል ጉዳተኞች ናቸው። አካል ጉዳተኛ የሆኑት የማኅበረሰብ ክፍሎች አካል ጉዳተኛ ካልሆኑት የበለጠ ማኅበራዊና ምጣኔ ሀብትያዊ ችግሮች ያጋጥማቸዋል። በተለያዩ ማኅበራዊ አመለካከቶች የተነሳ የትምህርት ዕድል የሚያገኙት የተወሰኑት ናቸው።

የሥራ ተሳትፏቸውም አናሳ ነው። የአካል ጉዳተኞች የአቅም ውስንነት እንዳለባቸው የሚያምኑት የማኅበረሰብ ክፍሎች ቁጥር ቀላል የሚባል አይደለም። ይህ አመለካከት ግን የተዛባ ነው። የአካል ጉዳተኞች የመማርና የመሥራት እድሉን ካገኙ የአቅም ውስንነት የለባቸውም።


ይህንንም በተግባር ያስመሰከሩ በርካቶች ናቸው። የአካል ጉዳተኞችን በተመለከተ

ያለው የተዛባ ማኅበራዊ አመለካከት የበለጸጉትም ሆነ በማደግ ላይ ያሉት ሀገሮች ችግር ነው።

**የማወያያ ጥያቄ -1**

1. በአካባቢያችው ለአካል ጉዳተኞች እንቅፋት የሆኑ ችግሮችን ዘርዝሩ?
2. እነዚህን ችግሮች የትውን እና የእይታን ጥበባትን በመጠቀም ለመቅረፍና ለአካል ጉዳተኞች የተመቻቹ ለማድረግ ምን መደረግ አለበት?

የለአካል ጉዳተኞች እንቅፋት ከሚሆኑት መካከል የተወሰኑትን የህንጻዎችና የመንገዶች አሠራር፣ የመረጃና የቴክኖሎጂ ተደራሽ ያለመሆን ወዘተ ለአብነት ሊጠቀሱ ይችላሉ። አካል ጉዳተኞች እንደማንኛውም የማኅበረሰብ ክፍል የመማር መብት አላቸው። በመሆኑም ትምህርት ቤቶችና የመማር ማስተማር ሂደቶች ለአካል ጉዳተኞች የተመቻቹ መሆን ይኖራባቸዋል። ከክፍል ውጭ የህንፃዎች መውጫና መግቢያ፣ በክፍል ውስጥ የመቀመጫ ወንበሮች ለአካል ጉዳተኞች በጣም የተመቹ መሆን አለባቸው። የትምህርት አሰጣጡም ልዩነት እንዳይፈጥር ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች እንደየፍላጎታቸው እገዛ የሚያደርግ መሆን ይኖርበታል። መስማት ለተሳናቸው በጽሑፍ ወይም ሊታይ በሚችል የምልክት ቋንቋ፣ ማየት ለተሳናቸው ተማሪዎች ደግሞ መምህራን ወይም ጓደኞቻቸው በማንበብ ሊያግዟቸው ይገባል።






ምስል 91. ክልካይ ምልክቶች




ምስል 92. ክልካይ ምልክቶች



ምስል 93. መረጃ ሰጪ ምልክቶች

### የተግባር ሥራ-6

1. በትምህርት ቤታችሁን ለአካል ጉዳተኞች የተመቻቹ ለማድረግ ገላጭ ምልክቶችን በመስራት በትገቢው ቦታ ለጥፉ?

### የማወያያ ጥያቄ -2

1. ሙዚቃ ከሌሎች ትምህርት ጋር ያለውን ዝምድናና ትግበራ በቡድን ተወያዩ?

ሙዚቃ በመሠረቱ በዚህ አለም ላይ ብዙ ነገሮች ውስጥ ከፍተኛ ሚና የሚጫዎት ነው፡፡ የሰው ልጅ አንድ ነገር ማድነቅ ሲፈልግ ፣ ሲደሰት ፣ ሲያዝን ፣ ሲከፋው ፣ አንድን ነገር ሲጠለው ወይም ሲያፈቅር ፣ የራሱን ባህል ወግ እና ታሪክን የሚያሳወቅበት እና የሌላውንም የሚያውቅበት መንገድ በዋናነት ሙዚቃ በመጠቀም ነው፡፡ የሰው ልጆች ከልጅነታቸው ጀምረው ሙዚቃን መሠረት አድርገው ያድጋል፡፡

ለምሳሌ፡- ልጆች ፊደል መቁጠር ሲጀምሩ (ሀ ሁ… /A B C D …) በዜማ ወይም በሙዚቃ ተደግፎ ነው፡፡ እንድህ የሆነበት ምክንያትም መጀመሪያ ላይ አዕምሯቸው ትምህርትን ለመቀበል ነፃ ይሆናል፡፡ በተጨማሪ በዜማ ሲለሚማሩ የተማሩትን ነገር አይረሱትም፡፡ በዚህ ምክንያት ሙዚቃ ለሌሎች ትምህርት ያለው ጠቀመታ ከፍ ያለ ነው፡፡

በሙዚቃና በሳይንስ መካከል ያለው መስተጋብራዊ ዝምድናና ትግበራ

ከላይ እንዳየነው ሙዚቃ ለሳይንስ ያለው መስተጋብራዊ ዝምድናና ትግበራ ላቅ ያለ በመሆኑ ለማህበረሰቡ ብዙ ነገርን እያስተማረ ቆይቷል ፡፡ ሳይንስ በውስጡ ብዙ ነገር (በሽታ የመከላከለል ዘዴን ፣ የተፈጥሮ ነገርን ፣ የአኗኗር ዘዴን እና የመሳሰሉትን) በዚህ ሁሉ ሳይንስ ከሙዚቃ ጋር በመሆን ማህበረሰቡን በተለያየ መንገድ ያስተምራል ፡፡

መዝሙር፡- ዓለም በሳይንስ ተራመደ

ዓለም በሳይንስ ተራመደ

በጥበብ እንዲኖር ተገደደ

በሂሳብ ስሌቱ አሰላ

ቋንቋን በምሳሌ አብላላ

በስነ ዉበት ፍጥረትን አደነቀ

በምርምር ቀስ በቀስ መጠቀ

እዉቀት ለምልሞ ያብብ

በትምህርት እንዲታይ ስነህዝብ




በዚህ ጊዜ በአለማችን ፣ በአህጉራችን ሆነ በሀገራችን አስፈሪና አስደንጋጭ የሆነው ከኮሮና እና ኤች አይቪ ቫይረስ የትውንና የእይታ ጥበብን በመጠቀም ራሳቸውን እንድጠብቅ በተለያዩ መንገድ ግንዛቤ ተሰቷል። ከኮሮና እና ከኤች አይቪ ቫይረስ ማህበረሰቡ በምን አይነት ሁኔታ ራሱን መከላከል እንዳለባቸው ምልክቶችን በማሳየት ፣ በሙዚቃ እና በትያትር ጥበባት ለማስተማር አይነተኛ ዘዴዎች ናቸው።

ኤድስ እንዳያጠቃን

አስከፊ በሽታ ኤድስ እንዳያጠቃን፤

እኛ ተማሪዎች መጠንቀቅ አለብን፤

ባለም ዙርያ ሁሉ ህዝብን ያስጨነቀው፤

በህክምና ዘርፍ ምንም መፍትሄ ያጣሁ፤

የሰዉ ልጅ ጠላት ቀሳፊው ኤድስ ነው፤/2/

እንከላከለው ዛሬ ነገ ሳንል፤

የሐኪሞች ምክር ሁሉን በመቀበል፤


ጥቁር ነጭ በማይመርጥ ድንበር ማያግደው፤

ህፃን ሽማግሌ ፆታ የማይለየው፤

ሁሉንም ይፈጃል ቀጣፊው በሽታ፤

ካልተጠነቀቅን አይሰጠንም ፋታ፡፡

መዝሙር:- ኤድስ እንዳያጠቃን





እጅን በሳሙና መታጠብ



ባልታጠበ እጅ ፍትን አለመንካት



ርቀትን መጠበቅ



ማስክ ማድረግ



ሳንታይዘር/አልኮል መጠቀም

ምስል 94. ኮሮናን መከላከያ ዘዴዎች

## የተግባር ሥራ-1

1. ከላይ በሙዚቃ መፃፊያ ሰሌዳ ላይ የተፃፈውን መዝሙር ተለማምዳችሁ በጋራ ዘምሩ?
2. ተማሪዎች ከኮርና እና ከኤች አይቪ ቫይረስ ማህበረሰቡ በምን አይነት ሁኔታ ራሱን መከላከል እንዳለባቸው የሚገልፁ ስዕሎችን ምልክቶችን በኪነ-ንድፍ ሰርታችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ?

## ማጠቃለያ

ተማሪዎች በዚህ ምዕራፍ ትምህርት ውስጥ የተካተቱ የአደጋ ከተለያዩ በሽታዎች ራሳችንን መጠበቅ ፣ የአከባቢያቸውን ፅዳት በመጠበቅ ፣ አየር ንብረት እና ስለስርዓተ ፆታ በተመለከተ አውቀውና ክህሎታቸውን አበልፅገው እንዲገኙ ለማድረግ የተለያዩ የመከላከያ ዘዴዎች በመጠቀም ተገባራዊ እንድያደርጉ ጥረት ተደርጓል፡፡ በዚህ ክፍል የሚገኙ ተማሪዎች የራሳቸውን ጤንነት ፣ የግል ንጽህናቸውንና የአከባቢያቸውን ንጽህና በመጠበቅ አደጋን ልያስከት ከሚችሉ ነገሮች ራሳቸሁን እና ማህበረሰቡን መጠንቀቅ እንዳለባቸው ግንዛቤ ተሰተዋቸዋል፡፡ የመከላከያ ዘዴዎችን እና ህሙማንን በመንከባከብ ፣ በመረዳት እና ሀሳቡን በመግለፅ የመንገድ ድህንነትና የኮሮናን ይዘት ለማስተማር በመዝሙር ፣ በንድፍ ፣ በቀለም ቅብ ፣ በጨዋታ ፣ በፎስተርና በፎቶግራፍ በመታገዝ በተገብ ሁኔታ ማስተማሪ እንድቻል እያንዳዱን ይዘት ፣ አጥጋብ ችሎታ ደረጃ ፣ ግባቶችን በመጠቀም የማስተማር ክንዋኔን እና ክትትልና ግምገማ ተጠቅመዋል ትምህርቱ ተግባራዊ ሆኗል ፡፡

## የክለሳ ጥያቄዎች

### የሚከተለውን ጥያቄዎችን እውነት ወይም ሀሰት ብላችሁ መልሱ

1. ጾታ በወንድና በሴት መካከል ያለን የተፈጥሮ አንድነትን የሚያሳይ ነው?
2. በአህጉራችን ሆነ በሀገራችን ከኮሮና ቫይረስ የትውንና የእይታ ጥበብን በመጠቀም ማህበረሰቡ ራሳቸዉን እንድጠብቅ ግንዛበ አልተደረገም?
3. አካል ጉዳተኝነት ማንኛውም ሰው ሊያጋጥመው የሚችል ተፈጥሯዊም ሆነ ሰው ሠራሽ አደጋ ውጤት ነው?
4. የአየር ንብረት ለረዥም ዘመን የዘለቀ አማካይ የአየር ሁኔታን ይመለከታል?
5. ሙዚቃ ከሌሎች ትምህርት አይነት ጋር መስትጋብራዊ ዝምድናና ትግበራ የለውም?

### የሚከተለውን ጥያቄዎችን መልሱ

1. የአየር ንብረት የሚባሉት ምን ምን ናቸው?
2. ለአካል ጉዳተኞች እንቅፋት የሆኑ ነገሮች ዘርዝሩ?
3. ከኮሮና ጋር የተያያዘ አንድ መዝሙር በቡድን ሆናችሁ ዘምሩ?

# 5. ዋቢ መጽሐፍት

1. በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ት/ቢሮ የተዘጋጀ የ1ኛ ክፍል የኤስቴቲክስ ማስተማሪያ መጽሐፍ 1998 ዓ.ም.
2. በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ት/ቢሮ የተዘጋጀ የ2ኛ ክፍል የኤስቴቲክስ ማስተማሪያ መጽሐፍ 1998 ዓ.ም.
3. በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ት/ቢሮ የተዘጋጀ የ3ኛ ክፍል የኤስቴቲክስ ማስተማሪያ መጽሐፍ 1998 ዓ.ም.
4. በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ት/ቢሮ የተዘጋጀ የ4ኛ ክፍል የኤስቴቲክስ ማስተማሪያ መጽሐፍ 1998 ዓ.ም.
5. በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ት/ቢሮ የተዘጋጀ የ5ኛ ክፍል የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት የመምህሩ መምሪያ መጽሐፍ 1997 ዓ.ም.
6. የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ኤስቴቲክስ መማሪያና ማስተማሪያ መጽሐፍ ደረጃ አንድ አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ 2000 ዓ.ም. በኮንሰርን ኢትዮጵያ ትብብር የተዘጋጀ፤
7. በኮንሰርን ኢትዮጵያ የተዘጋጀ የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ኤስቴቲክስ መማሪያና ማስተማሪያ መጽሐፍ ደረጃ ሁለት አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ 2000 ዓ.ም. በኮንሰርን ኢትዮጵያ ትብብር የተዘጋጀ፤
8. በኮንሰርን ኢትዮጵያ የተዘጋጀ የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ኤስቴቲክስ መማሪያና ማስተማሪያ መጽሐፍ ደረጃ ሦስት 2000 ዓ.ም. በኮንሰርን ኢትዮጵያ ትብብር የተዘጋጀ፤